እስረኞቹ በተለያየ ድምፅ ያንኮራፉሉ ፣ ይቃዣሉ ፣ ይባንናሉ ። አንዳንዱ "ውሸት ነው! እኔ አላየሁም! እምላለሁ! ገርፈውኝ ነው! ማንም ይጠየቅ! አልነበርኩም! በግድ እመን ከሆነ እሺ! ታዲያ ምን ሠርቼ ልብላ! — —" ይቃዣል ። ካቦው ቀና ብሎ ሲያይ ከምንዳዬ ጋር ዐይን ላይን ተጋጩ ። አንዱ የሌላውን ሐሳብና ዝግጅት ያወቀ ይመስል ተፈራሩ ። ካቦው ችላ ብሎት ተኛ ።

ከንጋቱ 12 ሰዓት አካባቢ ፣ ሁሉም ተራ በተራ ወደ ሽንት ቤት እየሔደ በፍጥነት ሲመለስ ፣ ምንዳዬና ሠዐረ በገረወይና ሲጠራቀም ያደረውን ሽንት አውጥተው እንዲያፈሱ በፖሊሶች ታዘዙ ። ረፋዱ ላይ ቃላቸውን እንዲሰጡ ወደ ጽ/ቤት ሲወሰዱ ሠዐረ በዚያቹ አጋጣሚ ወደ ቤቱ መልክት ላከ ። ባለቤቱም ሁኔታውን ለንሕድሩ ስትነግር ፣ የምንዳዬ መታሰርም ለሞገስ እምባቸው በስልክ ተነገረ ።

ሞገስና ቀኛዝማች ፣ 5ኛ ፖሊስ ጣቢያ ለመድረስ ጊዜ አልፈጀባቸውም ። በሚያውቁት መንገድና በለመዱት ብልሃት ተሯሩጠው ሁለቱ እስረኞች 48 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ 6ኛ ወረዳ ፍ/ቤት ቀርበው በዋስ እንዲለቀቁ ተደረገ ። ክሱም ከሦስትና ከአራት ቀጠሮ በኋላ በአነስተኛ የገንዘብ ቅጣት ተዘጋ ።

ከዚያች ምሽትና ሁኔታ ጀምሮ የሠዐረና የምንዳዬ ጓደኝነት በይበልጥ ጠበቀ ። ሌሎች የማያሳዩትን የአሠራርና የአጠጋገን ብልሃት በማሳየት ፣ ችሎታውን እንዲያዳብር ረዳው ። ያን የተቀጠረ ሰሞን እየተብረገረገ ሲፈነጣጠቅ ፣ "እንዲያው ምን ጉድ ይሆን?" በማለት የተገረመበትን የመበየጃ ቀላጭ ብረት ፣ ዛሬ እንደ ልጅነቱ የጅራፍ ቀንዲላ ይዞ እንደልቡ እያገላበጠ ሲበይድበት ይገርመዋል ። ያን ፣ "ያንተ ያለህ! የዝግንትል መዓት ፣ ምኑን ከምኑ አቆራኘተው አቆላለፉት" እያለ በተመስጦ ሲመለከተው ስለ ነበረው የመኪና ሞተርም በእጅጉ አወቀ ።

ሠዐረ ፣ የሞተርና የፍሬን ጥገናና እድሳት የተደረገላቸውን መኪናዎች ለመፈተሽ በሚወጣበት ጊዜ ፣ "እሱ ማኪና ብታሽግር ይረዳል" በሚል ሰበብ እየያዘው መሔድ በመጀመሩ ፣ ቀስ—በቀስ መኪና እንዴት እንደሚነዳ ማወቅ ጀመረ ። ከብዙ የፍተሻ ጉዞዎች በኋላም ፣ "ይቺ ማኪና ብትይዛት ምዝዋርዶ ትሽላለህ?" ብሎ ጠየቀው ።

"ዛሬስ አያቅተኝም" አለው በፈገግታ ።



# ምዕራፍ ዐርባ ዘጠኝ

ሽዋርካብሽ ውል በሌለው ቅጥር ወይ በመንፈቅ ወይ ባመት በሚሰጥ አልባሌ ቀሚስና ነጠላ ፣ በእንዲህ ያለ ጊዜ ቀን ይወጣልኛል ብላ ተስፋ በማታደርግበት ሁኔታ መኖር አንገሸገሻት ። ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ስለገዛ ኑሮአቸው ከማውጠንጠን በቀር ፣ እንዲች ብለው እንደ ማያስቡላት ታውቃለች ። በእርግጥም ሴትዮዋ አዲስ አበባ በተዋወቁአቸው ያገራቸው ሰዎች በኩል በሚደርሳቸው ወሬ ፣ ለወይዘሮ ደጅ ይጥኑ ተደርጓል ብለው በሚያስቡት ነገር ሁሉ የሚያንገበግብ ቅናት ስለ ነበረባቸው ፣ ስንኳንስ ለእሷ ፣ ለገዛ ልጆቻቸውም ደንታ ቢስ ሆነዋል።

ሽዋርካብሽ ፣ ተልካም ይሁን ተከትላ በወጣች ቁጥር በምታያቸው የከተማ ሴቶች ሁናቴና ፣ ሌሎች ሠራተኞች ደመወዝ እንደሚከፈላቸውም በማወቋ ፣ "እስተመቼ በነጣ ሳገለግል እኖራለሁ" በማለት ልቧ ሸፍቷል ። መብል መጠጡ እንደልብ በሆነበት ቤት ኑሮዋና ፣ ከእድካሚው የገጠር ሥራ በመገላገሏ አካላቷ ሞልቶ ፣ ደም—ግባቷም ሞቅ ደመቅ ማለት ይዞ ነበር ። አካሏም ቢሆን የሩካቤ ሥጋ ጥያቄ ማቅረብ ከጀመረ ውሎ አድሯል ። ሌላው የዘወትር ችግርዋ ግን ፣ ሐሳቧን የምታካፍለው ሰው በአቅራቢያዋ አለማግኘት ነበር ። ምንዳዬ እንዳመሉ እሱም ቢሆን ቅን ጠባይዋንና ገራገር አቀራረቧን በሚገባ በማወቁ ፣ የቆየ ቂሙን እርግፍ አድርጎ ትቶታል ።

"ኧረ ተው ጋሼ ምንዳ—ኧረ ተው አጨከን? እረ ተው እኔንም አሳልፍልኝ?" ትለዋለች ።

"እኮ ምን ላርግልሽ?—እማረግልሽ እኮ ነው የቸገረኝ?" ይላታል ባዘኔታ ።

"ተው ተየህ ተቤት ንላግለኝ?! ተው አንዱጋ ሥራ አስገባኝ? ተው ግድየለህም ፣ እኔም ሰው እሆንና ዘመድ እሆንህ ይሆናል?"

"ደሞ ደህና እፎይ ያልኩትን ነገር ልትቀሰቅሽብኝ ነው? ወዲት ገባች ቢባልስ ከ?"

"ኧረ ተው ካንጀትህ እውጋ! አንተ ብቻ እሺ በለኝ ፣ እኔ እቅብታለሁ ፣ እሌላ ጋ ሥራ አግኝቼ ሔጃለሁ ብላለች ብላችሁ ንገሩልኝ እላ

ለሁ" እያለች ስለምትጨቀጭቀው፣ችግሯ እየተሰማውና ልመናዋ እየ
ከበደው ሔደ።

በቅርብ ለሚያውቃቸው ሁሉ ነገረላት። ብዙም ሳይቆይ ተሳካ
ላት። ቀስ ብሎ በምስጢር ነገራት። ደስታዋ ከልክ ዐለፈ። መሔዷን
ለጐረቤት ነግራ፣በሹልክታ የምትጠፋባት ዕለት ናፈቀቻት።

በእርሱ ተያዢነት በወር ሰባት ብር ሒሳብ ግርድና ተቀጠረች።
"የኔ ዘመዶች ይኸው ናቸው! አስብቶ አራጅ! ምን ታረግ፣ በር በመ
ለስ፣ጓዳ በጎረስ ለቀኩላት፤ተቀምጦ መብላቱ ሲታክታት እንዴት
ትሁነው? ከተራበ ለጠገበ አዝናለሁ አሉ" አሉ ብለው ወ/ሮ እልፍ—
ይከንዱ ንዴታቸውን ዋጡት።

ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ እንዳይፈሩ ጠባቂ፣እንዳይወሰልቱ ሰባቂ
እንዲሆን በማለት የመጣው ሰውዬም፣ቢጭኑት አጋሰስ፣ቢጋልቡት
ፈረስ ሆኖ እንዲያገለግል አርገው ሴትዮዋ ገሩት። ምንም ከማይደማ
ቸው ከቀኛዝማች ይልቅ፣የሴሎቹ ጉርሻ በጣም ጠቀመው። ሴትዮዋም
የተወሰነ ገንዘብና ችሮታ ከሚዘረጋ አንድ እጅ ይልቅ፣ ያልታሰበ
ሲሳይ ወደሚያመጡ እጆች በስውር ዘወር በማለታቸው የሩካቤ ሥጋና
የአኗኗራቸው ሁኔታ እየተሟላ ብስጭታቸው ቀነሰ።

አቶ ወርቅነህ መዘውርም በሚደረግላቸው የመስተንግዶ ዓይነት
ሁኔታው ስለገባቸው "ጠንቀቅ እያልሽ" በማለት በርቺ የማለት ያህል
ዝም አሏቸው።

ቀኛዝማች የሚሔዱበት ጊዜ ተለይቶ ስለማይታወቅ፣ጥርጣሬና
ሥጋት በማስከተሉ፣'ዘመድ ጥየቃ ብለው ወጣ አሉ' እያስባሉ፣ከሚፈ
ልጓቸው ወንዶች ጋር በቀጠሮ እየሔዱ ጉዳይን አከናውኖ ፍላጐትን
ማሟላት የተሻለ ዘዴ ሆን።

ከዐርባ ዓመት የማይዘለው ዕድሜያቸውና በከተማ የልብስ ቅድ
ያማረበት ምንዳላ አካላቸው የጐልማሶችን ዐይን ለመሳብ በቂ ለዛና
ወዘና ነበረው። በዚህም የተነሣ ቀን—ቀን በሚያመች አካባቢ፣ ማታ
ማታ እገዛ ቤታቸው፣ ስውር የሴት አዳሪነት ኑሮ ጀመሩ። የቀ
ኛዝማች በላይነህ ሚስት የመባል ምኞታቸውንና፣ ባለቤትዮዋን
ከቤት የማፈናቀሉ እልህ፣ በሌላ አዳዲስ ወረትና ዓላማ ተተካ።
ቀኛዝማች ሲሔዱ አባብሰና ደባብሶ መግፈፍን፤ ከቀሩም፣ "እኔ'ንኳ
እንዲህ ያለ ነገር አላውቅም" ካሏቸው ሰዎች መኻል እግር የጣለውን
ተቀብሎ እጅህ ከምን ማለትን ተያያዙት።

ቀኛዝማች እቤታቸው ያጢያጢያሱት የቅናት ረመጥ፣ ከጊዜ ወደ
ጊዜ በአሉባልታ እየገፋ ሲያስቸግራቸው፣ "ምን ዓይነቷ ዝንታለም



የማይገባት ጉድ አገኘችኝ ወንድሜ? ጥላ እንኳ ዘወር ይላል" በማለት
ፊታቸውን ወደ ቅምጣቸው ሲያዞሩ፣እዚያም ቢሆን ሁኔታው እየተለ
ዋወጠ የ'ምነው ጠፉ?' አቀባበል ደረጃ በደረጃ ሟሸሸ። እሳቸው ግን
"ይኸ ቅናት እያረገው ነገር የለ! አዳሜ ለምቦጬን ትዘረጋብኝ ጀመር፤
እስንቱ ልሁን?" ከማለት አላለፉም።

ቀስ በቀስ ግን፣ከጠብ እርግፉና ከመስተንግዶው ማነስ የተነሣ
እያደር ቅሬታ ገባቸው። "ይኸ ነገር እንዴት ነው? እስቲ አንዲት ነገር
ልስማ? እንዲህ በዋዛ አንላቀቅ!" በማለት ጥርጣሬ ቢጤ ዳበሳቸው።
ምንዳዬን እንደ ቀድሞው ቢያምኑትም፣ "እስቲ ሰለል—አድርገህ ና"
የማለቱ ነገር ከበዳቸው።

ጥዋው ደረሳቸው። ባለቤቱ የሚያሳድገው ጥርጣሬ እየገዘፈ
ስለሚሔድ፣ሥር—ሥሩን ሐሳብ አንገላታቸው። በመጨረሻም የገዛ
ጥርጣሬአቸውን እስከ ማመን ደረሱ። ጥርጣሬአቸውን ለማረጋገጥም
ይመጣሉ በሚባሉበት ቀን መቅረትን፣ቀርተዋል በሚባሉበት ሰዓት
ማዘናጋትን ጀመሩ። ያም ሆኖ ከሴትዮዋ ችሎታ በላይ ብልጥ ለመሆ
ንና የጠረጠሩትን ለማረጋገጥ አልሆንላቸውም። በመጨረሻ ግን፣ ከአ
ንድ ሊተገብሩት ከማይቻላቸው ሐሳብ ጋር ተፋጠጡ። ይኸውም ሴት
ዮዋን ወደ ማጀቴ መልሶ መላክ፣ወይም ያስቀመጡትን ጠባቂ መለ
ወጥና፣ከዚያም ወደሚቀጥለው ርምጃ መሸጋገር ነበር። አንድ ቀን፣
ጊዜው የደረሰ መሰላቸውና፣ "እንግዲህ አገር ለምደሻል፣ ጐረቤትም
አፍርተሻል፣ ሰውዬው ምን ያረጋል?" አሉ በቸልታ።

"ምናለ ቢቀመጥ፣እኔን አልከበደኝ፣———አላስቸገረኝ ——
እሱ ለራሱ ——"

"ቢሆንም፣ እንግዲህ እርሱም ወደ ግብርናው ይመለስ። እሱ
የእርሻ ሰው ነው።"

"የደረሰ ልጅ አለው አላልኩኝም ነበር እንዴ? እንዲያው ለምን
አነጋጋሪ አገኘች ብለሁ ነውዒ፣እኔ አስቸገረኝ አላልኩሁ" አሉ ካን
ገት በላይ።

"ለማንኛውም እኔ አነጋግረዋለሁ፣ይሻለኛል ካለ ምን ቸገረኝ"
አሉ ውስጥ—ውስጡን ግን፣ "መስሎሻል" በሚል ስሜት ተንኮላ
ቸውን እየጐነጎኑ።

ያሰቡት አልቀረም። ሰውዬው ወደ ሣር—አምባ እንዲመለስ
ተደረገ። ሆኖም ሁሉም ነገር ከእጃቸው አፈትልኳል። አቶ ወርቅነህ
መዘውር የሰውዬውን ጥቅም ፈላጊነትና የሴትዮዋን አኗኗር ሲከታተሉ

ከቆዩ በኋላ ፡ “የሰማንያ ሚስት አይዶለች ፡ አትከሰስ—አትወቀስ —— ሲቀር ይቀራል” በማለት ስለሴትየዋ የወደፊት ኑሮ ማቀድ ጀመሩ ። ከራሳቸው ጋር የሚያደርጉት የሐሳብ ውጣ—ውረድ ከግላዊ ውሳኔአቸው ላይ እንደ ደረሰም ፡ በጉዳዩ ሞገስ አምባቸውን ተከፋይ አደረጉት። በዕቅዱ ላይ ሰፊ ውይይት ተካሔደበት ። በአቶ ወርቅነህ በኩል የገንዘብ ፡ የቦታና የዕቃ ዝግጅቱ እንደ ተገባደደ ፡ “ምን ይመስልሃል ይኸ ጉዳይ? እኔኮ ቀደም ብዬ እንደ ነገርኩህ ዝግጅቱን እያካሔድኩ ነው። ይህን ያህል ጊዜ የሰው እጅ እያዩ መኖር ቀላል አይምሰልህ ። ከዚህ በላይ እንኳንና ሰው አምላክም አይፈርድባት ። ማንኛውም ነገር መጠን ሊኖረው ይገባል ። እኔ የሷን ንግግር እምኘ ነው እንጂ ፡ ቀድሞውንም ቢሆን ጠርጥሬያለሁ ። አገር—ቤት ድረስ የሔድኩትም ሁኔታቸውን ለማጥናትና እሷን ያስደሰትኩ መስሎኝ ነው ። ሰውዬው ከወዲያ—ወዲህ እያምታቱ መጠቀም ይፈልጋሉ” በማለት ሞገስን አዋዩት ።

“ሰውየው በዚህ ጉዳይ ይስማማሉ ወይ ?”አለ ሞገስ ስለ ራሱም ወዳጅነት እያሰበ ።

“ቢስማሙ ፡ ባይስማሙ ምን ቸገረን ። ታዲያ እስተመቼ በዚህ ዓይነት ትኖራለች? እስከ ዛሬም የሞኝነት ነው ። እንዲህ እንደዋዛ ሲታዩ የዋህ የገጠር ሰው እየመሰሉ ሆዳቸው አይገኝም ። አረንዛ ናቸው ። እኔንማ ስንት ዐውቃለሁ የምለውን ሰውዬ ፡ ደህና አድርገው ነው የተጫወቱብኝ ። ያላስተዋወኳቸው ባለሥልጣን የለም ። ያውስ በቀላሉ መሰለህ ? የታናሽ እህቴ ባለቤት ናቸው እያልኩ ስዋሽ ከርሜ ያለሁ ። አንደዬ ከያዙ በማግሥቱ የማንንም ርዳታ አይሹ ። ዋናው ነገር ግን ፡ እንኳን ራሷን ማስገቢያ አገኘች እንጂ ከእንግዲህ ወዲያስ አይጫወቱባትም ። ስንትና ስንት ዓመት አሞኝተዋታል” አሉ ትምክህትም ተቆርቋሪነትም ባለበት አነጋገር ።

“የሰው ነገር እኮ አይታወቅም— — ምናልባት ይኸን ሲያዩ ቀንተው——” አለ እንደ ቀልድ ።

“ምን እንዳያረጉ ብለህ ነው? የትኛው ሕግ ነው ይህን ዓይነት ነገር እንዲሠሩ የሚፈቅድላቸው? እንኳንና መተናኮል ፡ አፍ አውጥተው አይቃወሙም ። ከተፈራገጡም ይላላጣሉ ። ሠርታ አትኑር የሚል ሕግ ደግሞ የለም ። ቤቱም የተገዛው በስሟ ነው ። ንብረቷ ነው ካሉም ይለይልናል ። በማን እንደሚብስ ይታያል ። ያንኛውን ትዳሬን እፍርሼ እዚሁ እጠቃለላለሁ ካሉም እናያለን ። ያም ቢሆን በሕግ ነው ። ያቺኛዋን ካልፈቱ ይቺኛዋን ማግባት አይቻልም ። ምነው ሕጉን እያወቅኸውም?” አሉ ።

በሴትየዋ አሳበው የሚከፍቱት ቡና ቤት በሐሳባቸው ተቀርጿል ።



ሞገስ ዋዠቀ ። ከወዲያ ከወዲህ ሲገትቱት ታየው ። አቶ ወርቅነህን ካልደገፈ ፡ “ዱሮውንስ የሰው ልጅ ችግሩን ካስወገደ ——” እሰኙቶ እንጉል ግምት እንደሚሰጠው ፡ ከቀኛዝማች ቢርቅ አዲስ የመሠረተው ቅርርብና መዋዋል ስለሚሻከር ግራ ገባው ። ባለቤቱን አማከራት።

“አንተ ለዚህም ለዚያም አትበል ፡ እዚያው እንደፍጥርጥራቸው ። እነሱ ይተዋወቃሉ” አለችው ።

“እኔማ ላንቺ ብዬ ነው እንጂ — — —”

“እንዴት ነው ላንቺ ብዬ ነው ብሎ ነገር? እኔ ደሞ የምን ቤት ነኝ?” አለች በመገረም ።

“እኔ ዝም ስል ሴትየዋ እንዳይቀየሙ ብዬ ነዋ! ዝምድናችሁንም ማየት አለብሽ!”

“ኡኡ! ይኸ ዝምድና ጉድ አፈላብኝ! እኔ በነጻ ሳገለግልና መከራዬን ሳይ ኖርኩዬ ምን ያገኘሁት ነገር አለ? ለኔ ብለህ ልብህን አታክር” አለችው ።

ሞገስ “በሥራ በዛብኝ” ሰበብ ከማማከር ርቆ እግሩን ቢያሳጥርም ፡ አቶ ወርቅነህ መዘውር ግን ፡ በወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ስም በተሰጠ የንግድ ፈቃድ ፡ በግል ውስጣዊ የስምምነት ውል ካዛንቺስ ውስጥ መለስተኛ ሆቴል አስከፈቱ ።

## ምዕራፍ ሃምሳ

ሸዋርካብሽ ካንድም ሁለት ሦስት ቤት ተቀጥራ ስትሠራ ፣ ተያዥ ሆኖ ያስቀጠራትና ፣ ስታጠፋ ወቅሶ ፣ ስትበደል ተከራክሮ አይዞሽ በርቺ የሚላት ያው ምንዳዬ ብቻ ነበር ። እንዳቅምቲ አጠረቃቅማ በገዛችው ልብስ ፣ አለባበሷ እየተሻሻለ ፣ አረማመድና አነጋገሯ እየተ ለወጠ ፣ ሥቃ ስትጫወት ማራኪ ሆነች ። የምንዳዬም ልብ መደንገጥ ጀመረ ። "እንዴት አማረባት እባካችሁ" ይላል እየከጀላት ። የኋላ ኋላማ ዓይኑ መቀላወጥ ፣ ልቡ መናፈቅ ጀመረ ። እሷም ቢሆን ገባት ። እንደ ተንጉ አልቀሩም ። "አሁን ብትቋጥር ምን አባቴ ይውጠኛል፣ ——አውጣኝ ጌታዬ" ይላል ከየግንኙነታቸው በኋላ ።

በመጨረሻ አነስተኛ ቡና ቤት ውስጥ ለቤት ጠራጊነት ፣ ለዕ ቃና ለልብስ አጣቢነት ተቀጠረች ። በየዕለቱ ጧት የቡና ቤቷን ባለቤ ትና ሦስት ሴት አዳሪዎች ቁርስ አብልታና ቡና አጠጥታ ቀሪ ሥራ ዋን ትጀምራለች ። ጥቂት ወራት እንደ ሠራች ፣ በተለያየ የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወንዶች ዐይናቸውን ጣሉባት ። አለፍ ስትል ጉታቿ ፣ ጠጋ ስትል ጉንታይዋ በዛ ። በዚህም ምክንያት 'ይቺ ደህና ገበያ ታስገኛለች' ተብሎ ወደ አሻሻጭነት ተዛወረች ። በሴት አዳሪነትዋ ምክንያት ከብዙ ሰዎች ጋር ተወዳጀች ። ሆቴሎችና ቡና ቤቶች እንዴት እንደሚቀጥሩም ዐወቀች ። በተጨማሪም ስለ አለባበስና አረማመድ ፣ አፈጋገግና አስተ ነጋገድ ፣ ስለ ውድ መጠጦች አሻሻጥና አብሮ ስለ መጋበዝ ፣ ብዙ ወን ዶችን ቀጥሮ ሲያስጠጡ ስለ ማምሸት — ——

ምንዳዬም እጅ—እግራቸው የሚናገር በሚመስል ደላሎች ተተካ ።

*　　*　　*

የወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ቡና ቤት የመከፈት ወሬ ከቀኛዝማች ጆሮ የደረሰው ፣ ጉዳዩ ከተጠናቀቀ በኋላ ነበር ። በነገሩ ክፉኛ ተናደው ሆድ ሆዳቸውን ቢበላቸውም ፣ ብስጭታቸውን ዋጥ አድርገው ፣ "ምነው እኔንስ ቀደም ብላችሁ ብታማክሩኝ ፣ ላወቀበትና ለበረታ ሰውኮ ቀላል መተዳደሪያ አይደለም" በማለት ውስጣቸው ቆስሎ ላያቸው ፈገግ አለ ። "አሁንማ የምቀኝነት ያስመስልብኛል" በማለት መራቁንም

ሆነ መቅረቡን በዘዴ ተያያዙት ። ሆኖም የከሰከሱት ገንዘብና የሰጡት ስጦታ እንገበገባቸው ። ዱሩ ምን ያደርጋል ፣ ከሰው የማያስመልሱትና ተበድያለሁ ብለው የማይሸማገሉት ከንቱ ጉዳይ ሆነ ። ከእንግዲህ ግትርነት ፣ 'ማ አባቱ ይነካታልና' አጉል ድንፋታ ፋይዳ የለውም ። ከተቻለ ሌላ ዘዴ ቀይሶ ከጥቅሙ መካፈል ፣ ወይም የጋራ ባለንብረት ለመሆን መሞከር ነው ። አረረም—መረረም ቀኛዝማች ከሁለት አንዱን መምረጥ ይኖርባቸዋል ። የወ/ሮ እልፍ ይከንዱ መሣቂያና ያገር መሣለቂያ ለመሆንም አይሹ ። እንዲያውም ይህ ጉዳይ እስከ መቼም እንዳይሰማባቸው ይፈልጋሉ ። ከተሸነፉና ከተዋረዱ ፣ ሞቱ መባልን ይመርጣሉ ። ሽንፈታቸውን ማመንም ሆነ መቀበል አይፈልጉም ።

የቀኛዝማች የጥላቻና የበቀል ቀስት ወደ አቶ ወርቅነህ መዘውር ዞረ ።

ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ፣ ለሥራው አዲስ ከመሆናቸው የተነሣ ሁለትና ሦስት መልከ—መልካም ሴቶች እያዘዙ ማሠራቱ ግር ብሏቸው ነበር። ቀኛዝማች በጉዳዩ ተናደው ቢተክኑም ፣ ቅናት እያዳፋ ይወስዳቸዋል ። ሴትዮዋም በሞቀ መስተንግዶ ልባቸውን ይጠልፉና ፣ "ዛሬስ የምታድሩት ከኔ ጋር ነው ፣ ናፍቀሁኛል — ምነው እቴ!" በማለት ይደልሏቸዋል ። ቢውሉም ስለማያድሩ ማታ ወደ ቤታቸው ሲያዘግሙ በንዴት የጋየ ልባቸውን በጉራ ውሃ ያበራርዱና ፣ "ለስሙ ካልሆነ ዛሬም ቢሆን እኔው ነኝ አስተዳዳሪዋ ። መስሏት ነው ፣ ካሳብ ገላገለችኝ እልጎዳችኝም" በማለት ሲጽናኑ ፣ ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ግን ፣ ኑሯቸውን በይሉኝታ የመምራቱን ነገር እየተዉ ፣ ልባቸውን ደንደን ፣ ፍርሃታቸውን ገለል ማድረግ ለመዱ ። ቀኛዝማችም እያደር ጎድን እንደ ተባሉ ገባቸው ። የቀደመው አፈትልኮ የቀረውም ላልቷል ። እሳቸውም ቢሆን ፣ እኒያን ቀድሞ እንደ ሽጉጥና ጠበንጃቸው ሲያዩዋቸው የነበሩትን ሴት ዛሬ ከልመናና ከደጅ ጥናት ባላነሰ ሁኔታ እየተመላለሱ መጠየቁ ሕሊናቸውን ስላቆሰለው ፣ ፊት እንደነሡት ቀላዋጭ ቀስ በቀስ አፈገፈጉ ። ሐሳብና ገንዘባቸውንም ለሁለተኛ ጊዜ ወደሚያደርጉት የፓርላማ ምርጫ ውድድር አዞሩት ።

* * *

ጊዜ እንደ ሙስክ ውሃ እየፈሰሰ ፣ ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደረደሩ —— ልኬለሽ ፣ ዐይኗ ወንድ ሳይቀላውጥና መቀነቷ ሳይላላ፣ የባለቤቷ ዐይን እንደ ናፈቃት ፣

ቸርነት "ለወዳጅም ለጠላትም አንደዩ አምሮበት መጥቶ አንጀቱ በራሰ" እያለ ፤



የወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ነፍስ በቅናት ጠውልጋ በወንድየው ንቀት ብትንገላታም ፣ "ለማባቱ ደስ ይበለው ብዬ ነው አገር ቤት እምገባው? እዚቹ ልጆቼን እያስተማርኩ እቀመጣለሁ ። እልከካ ፣ አላቦካ ፣ ያቀረቡልኝን ጉርስ ፣ ያስቀደዱልኝን ልብስ እያረኩ ያዳሚን አንጀት አጨሳታለሁ" እንዳሉ ፤

ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑም ፣ "እስተዛሬም በመከራ እጦት ተጎድቼ ኖሬያለሁ ። ነዳይ ይመስል የሰው እጅ ስጠብቅ ስንት ዘመን ሆነኝ ። ተንግዲህማ ነግቶልኛል ፣ እያደር ደሞ እቅበታለሁ" እንዳሉ ፤

ላቀች ትዳርዋ ሠምሮና ኑሮዋ ተሟልቶ ሁለተኛ ልጅዋን ወልዳ ስታጠባ ፤

ሞገስ አምባቸው ትዳሩ ተቃንቶ ፣ በቀድሞ ሚስቶቹ ፊት ፣ ከራሱ ቀና ከልቡ ዘና ብሎ ፣ "ከናንተ የምትበልጥ እንጂ የምታንስ አላገባሁ" እያለ ሲኩራራ ፤

አቶ ወርቅነህ መዘውር ፣ "እንዴት እኔ እያለሁ ፣ ባጣ ቆየኝ ሁና ትጠቃለች ፣ ካስቀመጡም የሚያስፈልጋትን ሁሉ ሰጥቶ ነው እንጂ ፣ እገጠርም ፣ እከተማም ሚስታቸውን አቅፈው ይቺን መጫወቻ አረጓት" በሚል ሰበብ ፣ የራሳቸውንም ጥቅም የሚያካብቱበት የሽርክና ቡና ቤት ከፍተው ትርፍ መብላት እንደ ጀመሩ ፤

ሸዋርካብሽ በደማቅ ጨርቅና በብልጭልጭ ጌጣጌጥ አምራ ፣ ካንዱ ቡና ቤት ወደ ሌላ እየተዘዋወረች በመሥራት ፣ አስደሳች መሳይ ኑሮዋን "ምንም ቢሆን ካዛባ ዝቆሽና ተሰው ፊት ሳይሻል አይቀርም፣ የነገን ደሞ አንድዬ ያቅልኛል" ስትል ፤

እፊሣም ፣ ቀኛዝማች ከርሞ ለሚያደርጉት የፓርላማ ምርጫ ውድድር ዝግጅት ፣ ቀደም ሲል ሣር—አምባ ሔደው በነበረበት ወቅት 'እገልግሉ ከልጅ ተነጥቆ መወሰዱን በመግለጽና ፣ ያን ጊዜም ቢሆን ከፊታቸው ገለል ያለው ነገሩ ሳይጣራ ተናደው እንዳያንገላቱት በመፍራት መሆኑን በትሕትና ገልጾ በሽማግሌ በመታረቁ ፣ በሠራው ተንኮል ሳቢያ የመበርገግ ስሜትና ሥጋቱ በጣም ተቃልሎ እንደ ልቡ በመኖር ላይ እንዳለ ፣

ምንዳዬ በደብዳቤ ከሚነገር የናፍቆት ሰላምታና 'በዓይኔ ሥጋ ለመገናኘት ያብቃን' ከሚል የሩቅ ምኞት ፣ "ተንግዲህስ እንደልቤ አይቻቸው እመጣለሁ ፣ ያመት እረፍት ፈቃዴም ተጠራቅሞልኛል" ብሎ የመሔጃውን ዕለት በማሰላሰል ላይ ሳለ ፣ ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ በሕድሩና በሞገስ አምባቸው በኩል እስፈትሸው የጫትን የሠ

ራች ላንድ ሮቨር መኪና ፥ በምንዳዬ ቦጋለ እያስነዱ ቅዳሜ ሰባት ሰዓት ላይ ሚስትና ልጆቻቸውን ይዘው ማጀቴ ከተማ ሲገቡ ገበያተኛው ሁሉ ጉድ አለ ።

ላንድ ሮቨሯ በገበያው መኻል አቋርጣ ወደ ዐጸዳማው የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ግቢ እንደ ገባች ፥ ቀኛዝማችን ለመቀበል በመጡ የሣር— አምባ ሰዎች ተከበበች ። ሰውዬው በስተርጅና የሚዳሩ መስለው ዱብ ሲሉ ፥ የኑሮውን ጣራና ግድግዳ የሚያውቀው ሉሌና ገበሬ ፥ ተጋዥና ጭሰኛ —— ሁሉ ጫማ ለመሳም ተሽቀዳደመ ።

'ለምኔ ብዬ ነው ይኸን ያህል ጎንበስ—ቀና ማለቴ ፥ ከሲሶው አይቀንሱልኝ ከርቦው' የሚለው ልበ—ሙሉ ደግሞ ፥ ክንብንቡን አውርዶ እጅ ይነሣና ፥ ዱላውን በስላች ተክሎ ይመለከታል ።

ቀኛዝማች 'ጋሻ—መከታችሁ እኔ ነኝ'በሚል ስሜት ፥ ካንገታቸው ጠንቀስ ፥ ከፈገግታቸው ነስነስ እያደረጉ ሰላምታ ሲያቀርቡ ፥ አንዳንዶቹን ግን ፥ ያለፈ ውለታቸውን በማስታወስና የወደፊት ድጋፋቸውን ለመቀስቀስ አገላብጠው ሳሟቸው ። ሆድ —ለሆድ ይተዋወቃሉ ።

የወይዘሮ እልፍ — ይከንዱን ጫማ ለመሳም የተግደረደሩና ጢጋ ከበብ ብለው ፥ "እቴዋ ! እቴሜቴ !" እያሉ በአክብሮት ተቀብለው የሳሟቸው ብዙዎች ነበሩ ።

ምንዳዬ ሞተር አጥፍቶና የሚደረገውን ሁሉ አደራርጎ ከመኪና ሲወርድ ፥ እንኳንና እሱ ነው ፥ ይሆናል ብሎ የጠረጠረም አልነበረ ። የነቱስና የብርድ መከላከያ ቆቡን አውልቆ ሁሉንም አያቸው ።

አንዳንዱ ትኩር ብሎ አይቶ ፥ "ይኸ ያ ምንዳዬም አዶል እንዴ ?" ይልና ፥ በሾፌርነቱና በአካላቱ ደልደል—ሞላ ማለት ደግሞ ይጠራጠራል ። አብዛኛዎቹ ዐወቁት ። ፊት ለፊት ካገኛቸው ጋር ሲሳሳም ፥ ላንድ ሮቨሯን ይመለከት ከነበረው ከቸርነት ጋር ዐይን — ላይን ተጋጩ ። ጓደኝነት እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰች ፥ የናፍቆት ፈገግታ እንደ እግረ—ፀሐይ ብርሃን እየደመቀች ፥ ቸርነትና ምንዳዬ ተቃቅፈው ተሳሳሙ—ደስታና ፈገግታ !

"ምንዳም አብሮ ይመጣል ብለው አልነገሩንም እኮ ?"

"አዬ ቸርነት ! ይኸማ እንዴት ይነገራችኋል ? እኔኮ አንድ ተራ ሰው ነኝ ። ስለ እኔ ምን ተብሎ ይነገራል ?!"

"ወይ ነዶ ! እነ አሻጋሪን እማመጣቸውን" አለ ራሱን እየነቀነቀ ።

"ምንም አይደል ፥ አሁን ስሔድ አገኛቸዋለሁ ።"



"አቤት ያቺ ልኬ! ዐይንህን ስታይ እንዴት ትሆነው ይሆን ? ደስታው ነው እሚገላት" ።

"ሁላችሁም ደህና ናችሁ ወይ ?"

"ደህና ነን ! እነ አሻጋሪማ አድገዋል ፥ —— ባየሃቸው ሲያንጉ!"

"በጣም ነበር የናፈኳችሁ! ደግነቱ በጊዜ መግባታችን ፥ ገና ሳይነጋ በ11:00 ነበር ጉዞ የጀመርነው" ብሎ ላንድ ሮቨሯን በፈገግታ አያት።

"የሳቸው መሆንዋ ነው?"

"እዎ የሳቸው ናት !"

"ማ እየነዳላቸው መጡ? ይችላሉ እንዴ ?"

"እሳቸውማ አይችሉም ። እኔ ነኝ የምነዳት ።"

"እስቲ ሙት በለኝ?! በምን ጠደከው ! እንግዲህ አጎሜ ዐይኗ ይቅላ !" አለ ቀስ ብሎ ።

ቀኛዝማች አጃቢዎቻቸውን አስከትለው ከገበያው በስተምራብ ዳርቻ ወደሚገኘው መጠጥ ቤት ገቡ ። በራሱ የተማመነና "ምንም ቢሆን ከሳቸው አላንስም" ባዩ የገጠር ከበርቴ ከቀኛዝማች አጠገብ ፥ ሌላው አቅሙን ዐወቅ ከየቢጤው ጋር እቤትና እደጅ ፈንጠር ጢጋ እያለ ተቀመጠ ። ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ልጆቻቸውን ይዘው ወደ ባለ መጠጥ ቤቷ ጓዳ ገብተዋል ። ምንዳዬ ከጓደኛው ጋር ከነቀኛዝማች አጠገብ በመቀመጡ ብዙዎቹ ሲገረሙ ፥ ቸርነትም ደንግጧል ። ቀኛዝማች ግን ፥ የለመዱት በመሆኑና ከምንዳዬም ጋር የነበራቸው የጌታና የሎሌ ግንኙነት ከስሜት በቀር ባብዛኛቸው በመቋረጡ ፥ ሁለት የተነፋፈቁ ጓደኞች ባንድ ላይ ተቀምጠው ያወራሉ ከሚል ግንዛቤ አልፈው በሌላ ግምት አይመለከቱትም ። ምንዳዬ የማንንም ስሜት አላጤነም ። ቀኛዝማችና አጠገባቸው የተቀመጡት አምስት—ስድስት ሰዎች በሽንጢ— ረጃጂም አፊ—ገላላ መለኪያ ኮኛክ ሲጠጡ ፥ ለምንዳዬ ቀንዶ አረቂ ታዘዘለት ። ለሌሎቹ ጠጅ ተቀዳላቸው ።

"እንዶኔ ቀንዶ ነጭ አረቂ ጠጣ!" አለው ወደ መደርደሪያው እየተመለከተ ።

"ኧረ እኔ ምን ይሆነኝ!? እኔ ይኸንኑ ጠጁን እ፡ጠጣለሁ ፥ ሆ! ለዚሁም ገርሞኛል ። ሰው ጉድ ይለናል ፥ እሳቸውም ደስ አይላቸው" አለ ቀኛዝማችን በጨረፍታ እያየ ።

"የፈለግሁትን ብጋብዝ መብቴ ነው ፥ ግድ የለህም" ።

"እኔ አይሻኝም! ይእርብኝ ምነው የዚህን አገር ሰው ስታቀው" አለው አቀርቅሮ ። አላስገደደውም ።

ሁለት ሰዓት ያህል ካረፉ በኋላ ፣ ለባልና ሚስቱ ፣ እንዲሁም ለልጆቹ በቅሎ ቀርቦላቸው ጉዞ ሲጀምሩ ፣ ወንድማማቾቹ ተፈናጠጡ።

"ምንዳዩ!" አሉ ቀኛዝማች አሽቆልቁለው እያዩ ።

"አቤት!"

"አንተ እኮ ሲደክምህ ውለሃል ፣ ዋቢሁን ከናቱ ጋር ይፈናጠጥና——"

"ኧረ ግድ የለም ! ከነቸርነት ጋር እያወራሁ ይሻለኛል ።"

"በል እንግዲያው በርታ !እኔማ መንገድ ረስተሃል ብዬ ነው።"

ፀሐይ አሽቆልቁላ ከላይ ተራራ አናት ላይ እንደ ደረሰች ማር—እምባ ገቡ ። ከግቢያቸው እንደ ደረሱም ፣ አብሮ የሔደው ሁሉ እንደ ጅራት ተከትሎ ገባ ። በሁለቱ አጥሮች መካከል ፣ ከትላልቆቹ አዳራሾች ጋር ስትነጻጸር ያረጀ የደሃ መሶብ የምትመስል ጎጆ ፣ በሯ መለስ ብሎ ፣ በየጭላንጭሏ ጢሷን ታቡለቀልቃለች ። የልኬለሽና የምንዳዩ ጎጆ ነች ።

ቀኛዝማች አጃቢዎቻቸውን አስከትለው ፣ ባዳራሾቹ መኻል ወደ እልፍኝ ሲያመሩ ፣ ምንዳዩ ፣ ቸርነትና ሌሎች ሦስት ሰዎች ወደ ጎጆይቱ ገንጠል አሉ ። ቸርነት በሩን ሲከፍተው ፣ እነ አሻጋሪ እያጠረና እየረዘመ ከሚንቀለቀለው የእሳት ነበልባል ዳር ተቀምጠው አሹቅ ያወልቡ ነበር ።

ቸርነት "አሻጋሪ ! ምንዳዩ እኮ መጣ! አባታችሁ መጣ!" ሲል ሁለቱም ወደ በሩ ሮጡ ። የምንዳዩ ዐይን ልጆቹ ላይ ተተከለ ። ግር እንዳላቸው አገላብጦ ሳማቸውና ከግራ—ቀኙ ይዟቸው ዐረፍ አለ ።

"እናታችሁ ወዴት ኬደች?" አለ አንደኛው ሰውዬ ።

"አባባ ቀኛማይ ይመጣሉ ብለዋት፣ እትልኡ ቤት ነይ" አለ አሻጋሪ።

ቁመተ ሎጋ የወይን እሸት የመሰለች መልከ—መልካም ጠይም ሴት በፈገግታ ተውባ በሩጫ ስትገባ ፣ ምንዳዩ እጆቹን ዘርግቶ ሲቀበላት ፣ ተጠመጠመችበት ። ጎጆይቱ በደስታና በፍቅር ወገገች ። ልኬለሽ ትይዘው—ትለቀው ጠፋት ። በደስታ ሰከረች ። ወደ ምድጃው ትሔድና ጉልቻውን ነካ—ነካ ፣ እሳቱን ቆስቆስ— ቆስቆስ ፣ ዐይኗን



ወደ ምንዳዩ ወርወር ፣ እንባዋን ጠረግ ፣ ብድግ—ቁጭ ፣ ሔድ—መለስ መላ— ቅጡ ጠፋት ። ጐረቤቶቿ እየመጡ ምንዳዩን ፣ እሷንና ልጆቹን ሳሟቸው ። አንዳንድ ሴቶች ወደ ምድጃውም ፣ ወደ ማጀቱም እያሉ መንጎዳጎድ ጀመሩ ። ጐረቤቶች ያመጡት ጠላ ፣ ሽክናና የዋንዛ ቅጠል እየተወተፈ በገንቦ — በገንቦ ሆኖ በምሰሶው ዙሪያ ተኮለኮለ ፣ እየተጠጣለት ።

ቀኛዝማች የላኩት አንድ እንስራ ጠላ በተከደነበት አንኮላ እየተንከከ ገባ ። ምንዳዩ ደስ አለው ። ቸርነትና ልኬለሽ ገረማቸው ። ጐረቤቶቿ እርስ—በርስ ሲያወሩ ፣ ልኬለሽ ከባለቤቷ ጐን ተቀምጣ ፣ አይቶ በማይጠግብ ዐይን ልቅም አድርጋ አየችው ። ምንም እንኳ ያ የጥንቱ የጢቱ ምንዳዩ ቢሆንም ፣ መልሳ—መላልሳ ስታየው ፣ እየቆየ—እየቆየ ገረማት ። እሱም እንደ ቀኛዝማች የተሾመ መሰላት ። አለባበሱ ፣ አስተያየቱና አነጋገሩ ፣ ጫማና ሰዓቱ አዲስ ስሜት አሳደረባት ። ካንድና ሁለቱ በቀር ጐረቤቶቿ ሁሉ እንደሔዱ ፣ "እንዲያው ለመሆኑ እንዴነህ? ምነው ጥፍት ማለትህ ልጄ?" አለችው ።

"ደህና ነኝ! እልመች ብሎኝ ነው ልኬ! ቢመቸኝማ በናንተ እጨክናለሁ ?"

"እሱስ እውነክን ነው ። የሰው አገር እስቲለምዱትስ ስንትና ስንት አለው! እኛማ ንፍቅ ስትለን ፣ ባይናችን ላይ ስትኬድ ስንቱን ተመኘነው።"

"ችግሩኮ ፣ የዓመት ዕረፍት ፍቃድ በወቅቱ ስለማይሰጡን ነው ። ለመሆኑ ሁለዜ ትዝ እላችኋለሁ?" አለ እየሣቀ ።

"ዋ—አንተ !— ምነው እኛን ሆነህ ባየኸው—አብሶማ ልጆቹ!"

"ምን ይሉኛል?" አለ የትንሹን ራስ እያሻሸ ። ልጆቹ ያባታቸውን ልብስ ፣ ጫማና ሰዓት እየደባበሱ ይመለከታሉ ።

"ነጋ ጠባ ፣ 'አባብዬ መች ይመጣል ፣ አባብዬ ምነው ቀረ' እያሉ ልቤን ሲያወልቁት ባየህ! እኔማ ዋሽቼ የምለው ጥፍት ሲለኝ ፣ ይኸው የፈረደበት ቸርነት የቆጥ—የባጡን ቀበጣጥሮ ዝም ያሰኛቸዋሊ. ካፋቸውም ለይተውህ አያቁ ፣ ——እንዲያው እንዴት ነው ያንተስ ኑሮ?" አለችው ትኩር ብላ እያየች ።

"ደህና ነኝ ። ምንም ችግር የለብኝም።"

"መቼም ከሳቸው ጋ እማደለሁ ብለህ ወረኸት ጥፈህልናል።"

"አዎ ፣ ቢሆንም ርቁ አልራኩ ፣ ብቅ እያልኩ እጠይቃቸዋለሁ ። ለዚህ ሁሉ ያበቃኝ ማ መሰለሽ ?"

"እውነክን ነው ፣ ቀድሞውንም ቢሆን አንተና እሳቸው ኮከባችሁ ግጥም ነው" ብላ ወደ ምድጃዋ ሔደች ። ከዚያም እንጀራ ቀርቦ እንደ ተበላና ቡና እንደ ተጠጣ ጨለመ ።

አረጋሽ ልጅዋን አዝላ እንደመጣች ምንዳዬም የቸርነትን የበኵር ልጅ አቅፎ ሲጫወቱ አመሹ ። ሊተኙ አቅራቢያ ቸርነት ጠመንጃውን ምንዳዬ ትራስጌ አስደግፎለት ወጣ ። ከአዲስ አበባ የወሰደው እንሶላ ፣ በጠፍር አልጋ ቁርበት ላይ ተነጥፎ ፣ ባልና ሚስቱ አዲስ ብርድ ልብስ ደርበው ሲተኙ ፣ ልጆቹም መደባቸው ላይ ለሽ አሉ ።

በማግሥቱ ጧት ከቁርስ በፊት ፣ ምንዳዬ ለባለቤቱና ለልጆቹ ፣ ለቸርነትና ለአረጋሽ የወሰደውን ልብስ ከሻንጣ እያወጣ ሰጣቸውና ለሰባት ወሯ የቸርነት ልጅም በግምት የገዛውን ጥብቆ አለበሳት ። ሁሉም አዳዲስ ለብሰው ሲታዩ ማማራቸው !

መሬት ሞቅ እንዳለም ቸርነት ለጓደኛው መስተንግዶ አንድ ወጠጤ አረደለትና አረጋሽ ሕፃኗን አዝላ ፣ ልኬለሽ ልጆቿን እየላላከች ምሳ ሲሠሩ ፣ ወንዶቹ ጠላቸውን በገንቦ ይዘው ወደ ሰበሰብ ወጡ ።

*　　*　　*

ቀኛዝማች ፣ አረጋሽን በጣም ይወዷታል ። እሷ ያየችና ያወቀችው ንብረት አይጠፋም ፣ አይደፈርም ። እሷ ብቅ ስትል ወሬኛ ወሬውን ፣ አሚተኛ ምላሱን ይሰበስባል ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ግን ፣ እንኳን በድብቅ በግልጽ ቢዝቁ ፣ ያሻቸውን ቢሳደቡና ቢናገሩ ፣ "እሳቸው እንዲህ እየለፉና መከራቸውን እያዩ እሱ ለማንም የማጀቴ ሴት እየዛቀ ሲሰጥ ምን ያርጉ?" በማለት ወሬ ማቀበሏን ከተወችው ብዙ ጊዜ ሆኗታል ። ሴትዮዋ ግን አመስግነዋት አያውቁም ። በጣም እንዲጠሏት ያደረገቻቸው ግን ሸዋርካብሽ ነበረች ። እሷ ቸርነትን ፣ እሱ ግን አረጋሽን በመውደዱ ፣ "እሱም የሷ ቢጤ ያገሊጋይ ልጅ ነው መሰል ፣ በደህናው እንዲህ አልወደዳትም ። ዕድሜ ለኛ ይበል ፣ አቦ! ሲል መጣና ሠለጠነ" ብላ ጠመደችው ። ባረጋሽም ላይ ዘመተችባት ።

ከቁመናዋ አጠር ፣ ከአካሏ ደልደል ብላ ፣ ከጠይምነት ይልቅ ወደ ጥቁረት የምታመዝነው አረጋሽ ፣ ጎረድረድ ያለች ደም—ግባታም ነች ። ቸርነት ሲወዳት አይጣል ነው ። እቆጡ ላይ የተኛ መስሎ አድፍጦ ያመሸና ፣ ሌሊት ጭር ሲልለት ይወርዳል ። ያዳራሹን በር 'ቋ' ሲያደርግ ትከፍትለታለች ። ዶሮ ደጋግሞ ሲጮህ ወደ ቆጡ ይመለሳል ።

"ቀኛዝማች አንድ ቀን ባገኙህና ባሯሯጡልኝ" ሲለው ምንዳዬ ፣



"እኔ የተለየ አልያዝኩ!! እሳቸውስ ማጀቴ ድረስ እሚሔዱት ግሼን ማርያም ሊስሙ መሰለህ? በሱስ አይጨክኑብኝም — ጣምናውን ያቁታል" ይለው ነበር ። በዚህ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ዐለፈ ። ቀኛዝማች ወደ አዲስ አበባ ሔደው ፣ አረጋሽ ያጐቷን ንብረት እየጠበቀች እንደ ልቧ በሆነች ሰሞን ፣ ቸርነትም ቀስ በቀስ ቆጡን ተወና አረጋሽ ዘንድ አዘወተረ ። ወሬውም ከቀኛዝማች ጆሮ ደረሰ ። ተይ ብሎ መከልከል የማይቻል ስለ ሆነባቸው በርጋታ አነጋገሯት ። ባታፍረጠርጠውም ገለጸችላቸው ። "ተያይዘው ከሚኮበልሉ እዚሁ እንዳሻቸው እየሆኑ ያገልግሉ" በማለት ዝም ስላሏት ፈቃዳቸው መሆኑ ገባት ። ቸርነት ቀርባ መጠየቋን እንደሰማ ፣ ኃፍረትም ፍርሃትም ይዞት ነበር ። ግልምጫም ጥላቻም ባለማየቱ ቀለለው ። ቀኛዝማችን አስፈቅዶ ካጥር ውጪ አነስ ያለች ጎጆ ሲቀልስ ሣር አምቦች ጉድ አሉ ። ያን አውርተው ሳይጨርሱ አረጋሽና ቸርነት ጎጆ ወጡ ።

*　　*　　*

ምንዳዬና ቸርነት ጠላቸውን እየጠጡ ሲጫወቱ ፣ "ጥኢት ቀን ትሰነብታላችሁ ፣ ወይስ ቶሎ ትመለሳላችሁ?" ሲል ጠየቀው ።

"አንድ 15 ቀን ያህል ሳንቆይ አንቀርም ፣ እሳቸውማ ብዙ ሥራ አለባቸው"

"ተንግዲህ ወዲያ ደሞ ምን ያረጋሉ?"

"እንደገና እኮ ሊወዳደሩ ነው? በያራት ዓመቱ አይደል! ።"

"ያንተ ያለህ! ገና ነውና አሳራቸው ፣ አሁን ደሞ እንዲህ አስደርግላችኋለሁ ሲሉ ሊከርሙ ነው በለኛ! ያቺ ሁሉ ያሏትኮ አንዷም አልተፈጠመች።"

"ሁሉንም አጠቃልዬ አስፈጽምላችኋለሁ ይላሉዋ!" ብሎ ምንዳዬ ሣቀ ። ከዚያም ስለ አዲስ አበባ ኑሮው አንዳንድ እያለ ሲያጫውተው ፣ ቸርነት እየተከፋም ፣ እየተደሰተም አዳመጠውና ፣ "ያም አለ ፣ ያም አለ አንተ እንደ ምንም እጅህን አውጥተሃል" አለው ። እሱም በበኩሉ ስለ ትዳሩና ስለ ልጁ ፣ ስለ ልኬለሽ ብርታትና ስለ ልጆቹ ሁናቴ ፣ እንዲሁም ስለ አፈሣ አጫወተው ።

"አስቸግሯችሁ ያውቃል እንዴ?" አለ ምንዳዬ ኮስተር ብሎ ።

"አሁንማ ልኩን ዐውቋል! አስቸግራለሁ ቢልስ ማ ይለቀዋል? የሱ ነገር ምን መላ አለው ፣ ሁለዬ አለጉዳዉ ይገባና ሲዝረጠረጥ ይገ

ኛል ። 'በመጡ ቁጥር ከምትሸሽ ፣ ሽማግሌ ልክህ ታረቅ' የሚል ደህና መከሪ አገኘ መሰል ፣ እምና ለሚካኤል እንደ መጡ ፣ ቄስ መንኩሴውን አግተልትሎ ታረቀ ። አሁን ደሞ ፣ ይኸን ሰሞን ሊመጡ ነው ማለትን እንደሰማ ፣ አጥር ሲያጠባብቅና ግቢ ሲጠራርግ ሰነበተ ። እሱ እንደ በግም ፣ እንደ ቀበሮም መኖሩን ያውቅበታል ። ከትላንት ወዲያ ግድም እሚሉት አገር ዘመድ ሞቶበት ሔዶ ነወዪ ፣ ታገኘው ነበር ።" ወሬ እቸው ሳያልቅ ወደ ቤት ገቡና ከተጠሩ የጐረቤት ሰዎች ጋር ተሰባ ስበው ምሳ በሉ ።

ሁለትና ሦስት በደስታ የተሞሉ ቀናት ዐለፉ ።

*   *   *

ቀኛዝማች ፣ የደጋፊዎቻቸውን ቁጥር ለማበራከትና እንደገና በከ ፍተኛ የድምፅ ብልጫ ለመመረጥ ፣ ለመንግሥትና ለምክር ቤት ያላቀ ረቡትን ሐሳብ ያቀረቡ ፣ ልዩ ልዩ ባለሥልጣኖች ያነጋገሩ ፣ ያላሰቡትን አሳሰበው ፣ ያልታቀደውን ያሳቀዱ በማስመሰል ለማሳመንና ለመታመን የወሬና የሐሰት ድራቸውን እያደሩ መዘዋወር በመጀመራቸው ፣ ቸርነ ትና ምንዳዬ ለአንድና ለሁለት ቀን መለያየት ጀመሩ ። የገጠሩን አካ ባቢ አዳርሰው ፣ ፊታቸውን ወደየአካባቢው ከተሞች አዞሩ ።

ከ15 በላይ በማትይዘው ላንድሮቨር ውስጥ ከ20 ሰዎች በላይ ጠበንጃና ዱላቸውን እየያዙ ይታጨቁባታል ። አንዳንዶቹ ከልብ ደጋፊ ዘመድና ወዳጅ ሲሆኑ ፣ ተቀላቅሎ የሚጓዝ አጨብጫቢም አይጠፋ ። እሱም ቢሆን ዋጋ አለው ። ፋይዳውን ስለሚያውቁ ፣ ሲርቅ ጠርተው፣ ሲቀርብ አብልተው ይሸኙታል ። ከዚያ በኋላ ጥቅምና ስማቸውን የሚ ሸከም አጋሰሳቸው ይሆናል ።

ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ካራቆሬ ፣ አጣዬ ፣ ሰንበቴና ሸዋ ሮቢት በሚ ደረገው ጉዞ ላይ ፣ ቸርነት አብሮ እንሒድ ምንዳዬ ቀደም ብሎ ቀኛ ዝማችን ጠይቋቸው ስለነበር ፣ አብረው ሔዱ ። መኪናው ከማጀቴ ተነ ሥቶ በረጂሙ ኮረኮንቻማ ጥርጊያ ሲጓዝ ቸርነት ዐይኑን ከምንዳዬ ላይ ሳይነቅል አስፋልት መንገድ ገቡ ።

ሰውዬውና አጃቢዎቻቸው ፣ ካራቆሬ ፣ አጣዬና ሰንበቴ ወረድ እያሉ የሚጋበዙትን ጋብዘውና የሚሸነግለውን ሸንጋግለው ፣ ተዘነጋግን ባዮችን በተበፋ ጀቧቡነው ወደ ሸዋ ሮቢት አመሩ ። ቢያለፉበት ከተማ ያወ ሩትና ያስወሩት ወሬ ግን ፣ እንዳንዴ ተረቡኛና ተጎራርዶ ፣ ሌላው ተጨማምሮበትና ተኳኩሎ ፣ የጎረሰ አሳምሮ ፣ የጠላ አጉደፍድፎ ያወ



ራል ፣ ያስወራል ። ላንድሮቨሯ ሸዋ ሮቢት እንደ ደረሰች ፣ ቀኛዝማችና አጃቢዎቻቸው በከተማይቱ ውስጥ ወደ ታወቀው ሆቴል ገቡ ። ምንዳዬ ገለል ያለ ቦታ መርጦ ከቸርነት ጋር ተቀመጠ ።

ከጥቂት ዕረፍት በኋላ ፣ የተለመደው የምርጫ ዝግጅት ወሬ በየ ፊናው ቀጠለ ። የተላከባቸው ሰዎች አንድ ወይም ሁለት ሰው እያስ ከተሉ መጡ ። አደራ ተብለው ዘመዶቻቸውን አደራ እንዲሉ ። የመጡ ትም የቆዩትም እየተጋበዙ ፣ እየበሉ ፣ እየጠጡ ፣ የሚያወሩት ወሬ እየተ ሟሟቀ ሐሰትና ጉራ ፣ እንደልብ ሆነ ። አብዛኛው ሰው ከለብታ ወደ ሞቅታ ተሸጋገረ ። ቀኛዝማች ለማሳረጊያ ሦስት ጠርሙዝ ነጭ አረቄ አወረዱ ።

ምንዳዬ ለራሱና ለባልንጀራው ጠቀም አድርጎ አስቀዳ ። የሁሉም ድምፅ ናረ ። ቸርነትም እንደልቡ ማውራት ጀመረ ። ሰዎቹ ሁሉ አን ሰው ታዩት ። ሁለመናው ቀለለው ። ቀኛዝማችን የማፈርና የመፍራት ስሜቱ የተገፈፈ መሰለ ። እሱም ጢጋ ብሎ ቢያዋራቸው ምንም እንደ ማይሉት ተሰማው ። እንዲያውም "እኔ ባረጋሽ በኩል ተዛምጃለሁ ። ምንም ቢሆን ከማንም ባዳ እኔ እበልጣለሁ" አለ በልቡ ። ምንዳዬ ፣ "ረጋ ብለን ነው መጫወት ፣ ቀስ ብለን እናውራ" ቢለውም አልሆነ ለትም ። ነገሩ ስላላማረው ቀስ ብሎ ጠበንጃውን ሊወስድበት ሲል ፣ "ይ — — ይ — ይ — ኸኮ ጓደ — ደ — ደኛዬ ነው! አንተ ነህ! አ — አምጣ!" ብሎ ያዘበት ።

"ልያዝልህ ብዬ ነው እንጂ ፣ እሱማ ያንተ ነው! ማንም አይነካ ብህ ።"

"—እ — እንደሱ ተሆነ — እሺ! ይቺ ቺኮ ገንዳ—ውሃሃሃ—ናት!!" ብሎ ለቀቀለት ። ወዲያው ፎክር—ፎክር ፣ አቅራራ—አቅራራ የሚል ግፊት ተናነቀው ። ሣር—አምባ ያለ መሰለው ። ስሜትና አካሉ እንደ ተዋሐዱ እመር ብሎ ተነሣና ፤

"የእናት ልጅ አምሳያ ፣ የት ይገኛል ባዳ ፣
ቀኝ እጁን የሚሰጥ ፣ አንጀት አራሽ ምንዳ ።
ገንዳ ውሃ ጢሻ በጥይት ሰንጣቂ ፣
አሞታሙ ምንዳ ጓደኛ አስታጣቂ ፣
ሣር—አምባ ላይ ሆኖ ዞን—አምባ አስጨናቂ" ብሎ ሲያቅራራ ፣
ሁሉም ወደ እርሱ አዩ ። ምንዳዬ ቀስ ብሎ በእጁ ስቦ አስቀመጠው ። ቀኛዝማች ስማቸው ባለመነሣቱ ቅር እያላቸው ሣቅ አሉ ።

"ሰከሩ ይሉናል — — እዚሁ ቀስ ብለን እናውራ" አለው ወደ ጆሮው ጠጋ ብሎ ።

"ማባቱ !? ይበሏ! ዕድሜ ላንድ ሰው! ተንግዲህም አንተ አለህ !!" አለና ድንገት ቆመ ።

"አምናና ሐቻምና ፣ ሲፈትሉ ሲገምዱ ፣
መጓዣው ጠፍቷቸው ፣ መሾሚያ ምንገዱ ።
አሉ ሙቱ ሲሉ ፣ — — አጅሬው ገሥግሠህ ፣
እኮራው አናት ላይ እንዳሞራ ቃየህ ፣
አባ ዝናብ ወንዱ ፣ ቆፍጣኔ በላይነህ ።
እርር ድብን ይበል ፣ ጠላት ቁርጡን ይስማ ፣
ሹመቱ የኛ ነው ፣ ለከርሞም ባርላማ" እንዳለም ፣ 'ይበል! ይበል! ለካ! ለካ! — — — ጎሽ!' ጎሽ! የሚል ድምፅ ተሰማ ። ካንጀት ተሥቆ ፣ ከልብ ተጨበጨበ ።

ቸርነት በዚያው ቀጠለ ።

"እንግዲህ ምን ይበል ፣ የዞን አምብ ጓዳ ፣
ወዳጅና ጠላት ፣ ዘመድና ባዳ ፤
አህያ ቀርቅቦ አጋሰስ ሲነዳ ፣
መኪና አግለብላቢው ይኸው መጣ ምንዳ !" ብሎ ሲቀመጥ ሁሉም ተንከተከቱ ። ሌሎች ሁለት ሰዎችም ፎከሩ ።

ቀስ በቀስ ሁሉም ተዳከሞ ፣ አንድ ባንድ ወደየመኝታው አዘገመ ። ምንዳዬና ቸርነት ከሆቴሉ በስተጀርባ ካለው መኝታ ክፍል አደሩ።

በማግሥቱ ማታ ቸርነት ቤት ተሰብስበው ራት ሲበሉ ፣ የትላንትናው ስካርና ቀረርቶ የተነገራቸው ልኬለሽና አረጋሽ ሲንከተከቱ አመሹ ።

ቀኛዝማች በመወዳደሪያ ክልላቸውና ውጪ ፣ በምኑም በምኑም ይጠቅማሉ ብለው ወዳመኑባቸው ሰዎች ሁሉ በበቅሎና በመኪና እየተጓዙ በማነጋገር ፣ እጅ — እጃቸውን ለሚያየው ገንዘብ ፣ ዝምድና ፣ ለሚቢቃው አደራ ፣ ውለታ ለሚጠብቀው ተስፋ ሰጥተው እንዳገባደዱ ፣ ቀሪውን ለሌላ ጊዜ አስተላልፈው ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ተነሡ ።

የምንዳዬም የዓመት ፈቃድ በማለቁ ፣ እሱም ለሥራው ቸኩሏል ። ልኬለሽ ቀኑ ፈጠነባት ። የመለየት ሥጋት በዳበሳት ቁጥር ፈገግታዋ ይጠወልጋል ። ዳግመኛ የሚለያዩባትን ዕለት ክፉኛ ጠላቻት ። ዳሩ ምን ይደረጋል ፣ የቀትር ፀሐይ መጥለቋ ፣ ውብ አበባ መጠውለጓ እንደ ማይቀር ፣ ጠላቻትም ፈራቻት የምንዳዬ መነሻ ቀን ደረሰች ።



"ልኬ?" አላት ምንዳዬ ፣ ለሱዉ መሸኛ የታረደችውን ልበ— ወርቅ ዶሮ ስትገነጣጥል ፣ "ከእንግዲህ ወዲያ እዚህ የምትቆዩት ለተ ወሰነ ጊዜ ነው ። ሦስት ዓመት ሙሉ ተለያይተናል ። አንደዬ'ንኳ ብቅ ብዬ ያላየኋችሁ ፣ ገና ሳልደላደል በማለት ነበር ። እንዳጫወትኩሽ አሠሪዎቻችን የዋዛ ሰዎች አይምሰሉሽ ። አብዛኛውን ጊዜ ጥቃቅን ስሕተት እየፈለጉ ከሥራ ያባርራሉ ። በተለይማ ችሎታው እንደ ነገሩ የሆነውን በቀላሉ ያስወጡታል ። እኔም ከጥሩ ጥሩ ሰዎች ጋር ጠጋ ጠጋ ስላልኩ ነው ብዙ ነገር የተማርኩት ። በዚያ ላይ ለምኑም ፣ ለምኑም አጋርና ዘመድ ያስፈልጋል ። አሁን እንደ ምንም ጥርሴን ነክሼ ራሴን ችያለሁ ። አንደዬ ሚስቴ አንደዬ ልጄቼ እያልኩ ወለም—ዘለም ባበዛማ ኖሮ ፣ ሥራ አይወድም ብለው ያፈናቅሉኝ ነበር ።"

"ኧረ ደግ አረክ! ይኸ ታዲያ የጥላቻ አዶል! አንተም እሰው አገር ሔደህ ከምትንከላፈት ጥሩ አርገሃል ። በሁለት እግር ቆሞ ነው ወግ ማውጋት ። እጅ ያጠረህ ዕለት ማንም እኔ አለሁልህ አይልህም ። ሁሉም አለሁ አለሁ ቢል የምር አይምሰልህ ፣ ሁኔታህን እያዩ ነው ። ያው ዐይንህ ነውዪ ፣ እጅህ አልራቀን ። ችግር ይሉ ነገር ነክቶን አያውቅም ። አሻጋሪም እርፍ ጨብጧል ፣ በያላይ ደሞ ቸርነት እያለ ቤታችን አይቀዘቅዝም ። ለኛ ምናምኒት አታስብ" ብላ ጥንካሬን የሚገልጽ ገጽታ አሳየችው ።

"እኔም አሳቤን ጥዬ የተቀመጥኩት እንደማይቸግራችሁ ስለማውቅ ነው ። ሥጋት ቢኖርብኝማ ኖሮ ፣ መች እንዲህ እንደልቤ እቀመጥ ነበር !።"

ስለ ሌሎች ጉዳዮች በማውራት ላይ እንዳሉ ፣ ቸርነት ገንቦውን በአሻጋሪ አሸከሞ ፣ አረጋሽም ልጅዋን አዝላ ተከታትለው ገቡ ። ሁሉም ሸክናቸውን ጨብጠው በኅብረትና በተናጠል አዳዲስና ትዝታ ነክ ጨዋታ ጀመሩ ። ወሬው እንደ ጣማቸው የልኬለሽ ዶሮ ወጥ በነጭ ጤፍ እንጀራ ታጅባ ቀረበች ። መላ ቤተ—ሰብ ዙሪያውን ከበው ቅር ጥፍጥፍ አደረጓት ። ያን ለታ ማታ ለልጆቹ የተለየ መዓድ አልተሠ ራላቸውም ። ድስቲቱ የታጠበች መስላ ተነሣች ። የኩራዚቱ ላምባ እያለቀ የምድጃው እሳት ላንቃ ሲያጥር ቸርነትና አረጋሽ ወደየቤታ ቸው ሔዱ ። ነገ ጢት ቅርብ ናት ።

ልኬለሽ ጋደም ከማለቷ ሐሳብ ገባት ። ዶሮ ደጋግሞ እንደ ጮኸ ከእንቅልፏ ነቅታ ውሃ ጣደች ። ሲኮክሉ ካደሩት አውራ ዶሮዎች መካከል ምንዳዬ አንዱን ገብስማ አርዶት ተመልሶ ተኛ ። የፀሐይ መውጫ ቀይ አለላ እንደ መሰለ ድስቱ ወረደ ።

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱም ቅቤው ተንጣሎ ሽታው ዙሪያ ገባውን ያወደ የዶሮ ወጥ ሠርተው ፡ ግግሹን ባገልግል ቋጥረውታል ።

ረፋዱ ላይ ቀኛዝማች እንደተለመደው ታጅበው ሲወጡ ፡ ምንዳዩም ባለቤትና ልጆቹን ፡ እንዲሁም አረጋሽን አስከትሎ ብቅ አለ ። ጥቂት እንደ ተጓዙ አረጋሽ አጐቷን ተሰናብታ ወደ ምንዳዩ መለስ አለችና ፡ "እንደዚህ ቀደሙ ጥፍት አትበል ፡ መጣ—መጣ እያልክ ጠይቀኝ" አለችው እንባዋ ተንቆርዞ ።

"ተንግዲህስ እመጣለሁ ፡ እንደተዚህ ቀደሙ አልቆይም" አላት ፈገግ ብሎ ። ከነልጅዋ ስሞ ሲሰናበታት ሆዷ ባባ ።

እኩለ ቀን ላይ ማጀቴ እንደገቡ የቀኛዝማች ኮተት ካህዮች ላይ ተራግፎ ላንድሮቨር ላይ ተጫነና ሰውዬው አጃቢዎቻቸውን አስከትለው በገቢያው መኻል ዐለፉ ።

የማጀቴ ገቢያ ዙሪያውን በልብስና በሸቀጣ—ሸቀጥ ሱቆች ፡ በሻይ ፡ በጠላና በጠጅ ፡ በሥጋና በቡና ቤቶች የተከበበ ሲሆን ፡ ገበያተኛውን ከጉብታ ላይ አሸቀልቁሎ ለተመለከተው ፡ በሰፊ ጉድጓዳ ቦታ የሚርመሰመስ ዝንጉርጉር ፍጥረት ይመስላል ።

ምንዳዩ በኩራትና በላሳይ—ላሳውቅ ስሜት መኪናይቱ ውስጥ ገብቶ ሞተር በመቀስቀስ አስጎራት ። ሞተሩን ሳያጠፋ ወርዶም ኮፈኑን ከፈተና አንዳንድ ነገሮችን አጠባበቀ ። ልኬለሽ እየገረማት ተደሰተች ። ልጆቹም ከናታቸው ጉን ቆመው ፈዘው ያያሉ ።

ቀኛዝማች ተመልሰው ሲመጡ ፡ ምንዳዩ ከፊቱ ፈገግ ፡ ከመንገዱ ገለል ብሎ ተቀበላቸው ። የልኬለሽ ዐይን እንባ አዝሎ የልጆቹ ፊት ተንቀረበበ ።

"እኔ ነኝ ጥፋተኛው ፡ እዚያው ሣር—እምባ ብሰናበትሽ ኖሮ" አላት በማስመሰያ ቁጣ ።

"ምናረኩ? ለምን መጣሽ ብለህ ነው?" አለች አቀርቅራ ።

"መምጣትሽንማ ወድጄዋለሁ ፡ አንቺ ግን ልቅሶሽ በየት — —"

"ግድ የለህም! ፈርቼ መሰለህ? እንኳንና ዛሬ ያኑዬም አልፈራሁ — —"

"ቢሆንም ! እያለቀሱ መሸኘት ጥሩ አይደለም ። እንደማትፈሪማ ዐውቃለሁ" ብሎ ትከሻዋን ያዘና ፡ "ቢቃ! ከእንግዲህ ብንለያይ ለጥቂት ጊዜ ነው" አላት ደርበብ ብሎ ቀዝቀዝ ያለ ፊቷን እያየ ። በመጠኑ ፈገግ አለች ።



ቀኛዝማች ከቤተሰባቸውና ከአምስት ሰዎች ጋር ላንድሮቨሯ ውስጥ ገቡ ። ምንዳዩ ፡ ልኬለሽንና ልጆቹን ፡ እንዲሁም ቸርነትን ስሞ መኪናይቱ ውስጥ ገባ ። መደዳውን ቆመው ካይናቸው እስኪሰወር አዩት ።

ላንድሮቨሯ ካራቆሬ ከተማ እንደ ደረሰች ፡ ቀኛዝማች እህታቸውን ለመሰናበትና በሰበቡም የጀመሩትን የዝና ማስፋፋት ወሬ ለመነስነስ ወደ ወ/ሮ ጌጤነሽ ታፈሰ ቤት ሔዱ ። ሴትዮዋ ወንድማቸውን ለማስደሰትና ወሬውም ባካባቢው እንዲወራላቸው በማሰብ እንግዶቹን እንዲያድሩ ጠየቋቸው ። ተስማሙ ።

ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ወዳጅ ፡ ዘመድ ጥየቃ ፡ ልጆቹ ባልንጀሮቻቸውን ፍለጋ ሲዘዋወሩ ዋሉ ። የወ/ሮ ጌጤነሽና የባለቤታቸው ግብዣ ሲበላና ሲጠጣ ሌሊቱ ተጋመሰ ። በማግሥቱም ረፋዱ ላይ መስተንግዶው ቀጥሎ ጕረቤቶችም ተጋበዙ ።

ከዚያም መኪናይቱ የትም ሳትቆም ዘጠኝ ሰዓት ላይ አዲስ አበባ ደረሰች ። ቡና ተጠጥቶ ጥቂት እንዳረፉ ፡ ቀኛዝማች አብረዋቸው የመጡትን እንግዶች 'ከተማ ላስጐብኛችሁ' ብለው ወደ ካዛንቺስ ይዘዋቸው ገሠገሡ ።

ቀኛዝማች ካንገታቸው ቀና ፡ ካረጋገጣቸው ኮራ ብለው ወደ ይፋት ቡና ቤት ሲገቡ ፡ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ዳሌአቸውን አቅፎ ቂጣቸውን እንደ ትልቅ ወታቦ ካድበለበለው ደጋናማ የብረት ወንበር ላይ ተቀምጠው ፡ ካንድ ወንድ ጋር እየተሣሣቁ ይዝናኑ ነበር ። ድንገት ስለ ተደረሰባቸው ሴትዮዋ ደንገጥ ሲሉ ፡ ቀኛዝማች ነደዳቸው ። ሆኖም ልብ ያላሉ መስለው ፡ ምንዳዩንና እንግዶቹን አስከትለው ወደ ውስጥ ዘለቁ ። ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ፈጠን ብለው ተከተሏቸው ።

"ምነው ቶሎ እመለሳለሁ ብለሁ ፡ ይህን ያክል ጥፍት ማለትሁ ?" እያሉ ከመኝታ ክፍላቸው ፊት ለፊት ያለውን በር ከፍተው አስገቧቸው ። ከመኝታ ቤታቸው ጋር የተያያዘው ይህ የሰበሰብ ክፍል ፡ የእንግዳ መቀበያ ሲሆን ፡ ከቡና ቤቱ ጀርባ ዐሥር ርምጃ ያህል ወደኋላ ፈቅ ይላል ። መኻል ላይ አጠር ብሎ ልከኛ ስፋት ያለው ጠረጴዛና ስድስት ወንበሮች ተደርድረዋል ። ከውጪ የመኝታ ቤቱ በር የተጋረደበት ጌጠኛ መጋረጃ ረዝሞ ዘርፉ ወለል ያስሳል ።

ቀኛዝማች ፡ የተቀዳላቸውን ዊስኪ ፡ ሌሎቹ የቀረበላቸውን ቢራ እየጠጡ ስለ ውሏቸው ሲያወሩ ፡ ሴትዮዋም ደንበኞቻቸውን ሸኝተው ተቀላቀሉ ። የወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ የመስተንግዶ መዐድ ቀርቦ ከተበላና

የማይቀረው ቡና ከተጠጣ በኋላ ፣ ቀኛዝማች በባለቤትነት ስሜት ያስመጡት መጠጥ ቀርቦ ሁሉም ተጋበዘ ።

ሴትዮዋ በአዲሱ የኑሮ ምቾት የተሞናደለ ገላቸውንና በዘመኑ የልብስ ስፌት ቅድ ፣ ያማረበትን ሙንድልድል አካላቸውን እያገላበጡ ከወዲያ—ወዲህ ሲሉ ፣ የቀኛዝማች ዐይን አብሮ ተንከራተተ ። ስሜታቸው ቋምጦ ዐይናቸው የባከነበትን ገላ አግኝተው እስኪረኩም አቅበጠበጣቸው ።



# ምዕራፍ ሃምሳ አንድ

ሁሉም ጋ ተንጧል ።

ቀኑ ቢለያይም ፣ ያልሰማና ያላወቀ አልነበረም ። ቀኛዝማችም ልባቸው ተኮማትሮ አንጀታቸው ጨሷል ። ከትላልቅ ከተሞች እስከ ፣ ትናንሽ መንደሮች ፤ ከአነስተኛዋ የገጠር ት/ቤት እስከ ዩኒቨርስቲ ፣ ከተራ ጭቃ ሹም እስከ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፣ ከሞያሌው ተራ ወታደር ቃሮራ እስከሚገኘው የጦር ሠራዊት ጀኔራል ፣ ከሠፈር ቀጥቃጭ ፣ እስከ ብረታ—ብረት አቅላጭ የፋብሪካ ሠራተኛ ፣ ከደሃ ገበሬ እስከ ባለ ብዙ ጋሻ የመሬት ከበርቴ ፤ ከጣሳ ጠላ ቸርቻሪ መበለት እስከ አስመጪና ላኪ ቱጃር ነጋዴ! ሁሉም ሰምቷል! ዐውቋል ።

በይፋ የሚቃወሙ ፤ ውስጥ ውስጡን የሚያጉረመርሙ ፣ ላምላካቸው የሚነግሩ ፣ ተደብቀው የሚመክሩ ፣ ተይዘው የሚታሰሩ ፣ ተሰብስበው የሚታጎሩ — — — እዚህ — — እዚያ — — — የትም — — — አዲስ አበባ — — — ደሴ — — — ጂማ ——————በየአምባው ——— በየስርጓጉጡ ፣ — — ከራስ ደጀን ተራራ — — — እስከ ዳሎል ዘብጥ ።

ሁሉም ጋ ተንጧል ። የከፋውም ፣ የደላውም — ሁሉም በያለበት "እህ?" ማለት ይዟል ።

"ሰዉ ዘንድሮ ጤናም የለው! 'ሥልጣናችሁን ልቀቁ ፣ ርስታችሁን ተነጠቁ' ይል ጀመር!" አሉ ቀኛዝማች ፣ ዐልፎ ዐልፎ የሚያዩትንና በየመኳንንቱ አካባቢ የሚሰሙትን ይዘው ። ሁሉም ያበደና የሸፈተ መስላቸው ። ዐልፎ ዐልፎ ቢናደዱም ፣ "ትልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ" እያሉ ይንቁታል ።

እና ሁሉም በጊዜ መስኖ ፈሰሰ — የፈራም የተባም ባማሹ እየታመሰ ።

ቀኛዝማች ፣ ምንዳዬ ፣ ቸርነት ፣ አፈሣ ፣ አቶ ወርቅነህ ፣ ወ/ሮ ዶጅ—ይጥኑ ፣ ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ፣ ልኬለሽ ፣ አረጋሽ ፣ ላቀች ፣ ሸዋርካብሽ ፣ አስካደች ፣ ሞገስ አምባቸው ፣ መምሬ ተክለጊዮርጊስ ፣ ሠዐረ ፤ ሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ ፤ አማረ ንጋቱ ፣ ዋሲሁን ፣ እርም አይቀሬ ፣ ሚካኤል ፣ ጊዮርጊስ ፣ ሃጃ — ፈጅ ፣ አዲስ አበባ ፣ ማጀቴ ፣ ዞን አምባ ፣ ሣር—አምባ ፣

ደብተራ ፣ ጠንቋይ ፣ ዘማዊ ፣ ዋልጌ ፣ ሠራተኛ ፣ ገበሬ ፣ ወታደር ፣ ተማሪ ፣
ሁሉም ታመሰ ። በጊዜ መስኖ እየፈሰሰ! ተናነቀ ፣ ላይላቀቁ ።

ቀኛዝማች ‘ሰው በድያለሁ ፣ ኃጢአት ሠርቻለሁ’ ብለው ባያም
ኑም ፣ “ሳናውቅ በስሕተት ፣ ስናውቅ በድፍረት የሠራነውን ኃጢአት
ይቅር ይበለን” እየተባለ የሚነገረው በዘፈቀደና በከንቱ አይደለም
በማለት ፣ የየዕለቱ ጸሎትና ይቅር በለኝ አቤቱታቸው ፣ ያለፈውን ኃጢ
አት ሁሉ የሚደመስስላቸው ስለሚመስላቸው ፣ የሠሩትን ሠርተውና
የበደሉትን ቢበድሉም የንጹሕነት ስሜት ይሰማቸዋል ። ይህ የብዙ
ዎቹ ቢጤዎቻቸው ባሕሪ ነው ።

አንድ ቀን እንደ ተለመደው ማለዳ ተነሥተው ፣ ሰበሰቡ ላይ የጸ
ሎት መጽሐፋቸውን ሲያነቡ ፤

“ትክክለኛ አገዛዝ እንዲህ አይደለም! ከዘር ማንዘር የወረደ ፣
ጂኒ ቁልቋል ፣ በእግዚአብሔር የተሠየምኩ እያሉ ማወናበድ ያታላዮች
ሥራ ነው! ኢድየትስ! የይሁዳ ዝሆን ፣ የሰሎሞን ወርንጭላ! እያሉ
ባገር ላይ መጋለብ! — — ባስታርድስ! ተዝቢ አይደለም! ዘመድ !
አልጋ! ዙፋን! ቱጋን! ቢሽቲያ! እናቱን! ቢፈልግ እኔ እበቃዋለሁ!
ሶኖ ኢዮ አቻዮ ዲ ፌሮ!” እያለ የሚጮህ ድምፅ ይሰሙና ፣ ንባባቸ
ውን ያቋርጣሉ ። አላስችል ስላላቸውም ፣ የአጥሩን በር ከፍተው ብቅ
ይላሉ ።

ዳለቻ ኮት ለብሶ ፣ ካኪ ሱሪ የታጠቀ ፣ የሸሚዙ አዝራሮች ተበ
ጥሰው ፣ ደረቱ የተገለጠ ፣ ረዘም ያለ ጸጉረ እንጭብር ወንዳወንድ
ወጣት ፣ ባዶ እግሩን ጐዳናው መሐል ቆሟል ።

“እኔ ደሃ መስሎኝ ነበር ። ለካ ይኸ ሰው እብድ ነውና! እንዲህ
እንደ ልቡ ዘውድና ንጉሥ ሲሳደብ እንዴት ዝም አሉት!” አሉና
ስለ ዘውዱና ንጉሡ ተናደዱ ።

“ጨቋኝና ግፈኛ ሁሉ ቀበሮ ነው ። ቀበሮ በግ ትበላለች ። እነሱ
ሰው ይበላሉ! ጆቦች! ሞንስተርስ! እናታቸውን! እኛ እናስብላችኋ
ለን ፣ እኛ እናውቅላችኋለን እያሉ ያታልላሉ! ‘ግሬት ቶከርስ አር
ግሬት ላየርስ’ አለ ያ ፈረንጅ! አብሮት ያለው ሁሉ ቀፈታም ነው ።
ቦርጫቸውም በሰዎች ነፍስ ተሞልታለች! ነፍሶቹ ሲፈራገጡ ይታዩ
ኛል! ጉሮሯቸውን አንቄ አስተፋቸዋለሁ! እኔ ሮኪ ማርሲያኖ! ‘ሰዎች
ይወዱሃል የምንልህ እኛ ነን እንጂ ፣ ሕዝቦችስ ሞትህን ይመኛሉ
አይሉትም!’ የይሁዳ አንበሳ አንተ ንጉሣችን እየተባለ ይዘመራላ!
ዐፈር—ድሜ! ሕዝቦች የሚያጨበጭቡልህና እልል የሚሉልህ ሳይወዱና



ሳያውቁ ነው በሉት! ላላላ! ቡም! — — ቡቡቡቡም! ነግሬሻለሁ ፣
ፍቅር ይዞኛል! የራሷ ጉዳይ !”

“የሲቀ—መላኩ ያለህ! ዛሬስ ምኑን አሰማኸኝ! የእብዶች ማሰ
ሪያና ማከሚያ አለ እየተባለ እንዴት ዝም ይሉታል!” ብለው እየተ
ናደዱ ወደ ቤት ገቡ ። ንዴቱ ሳይበርድላቸው ዋሉ ።

ከዚያን ቀን በኋላ ፣ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች አዩት ። ስድብና ዘለ
ፋው እያናደዳቸውም ከፉኛ ጠሉት ። መኖሪያው ባቅራቢያቸው ስለ
ነበር ፣ “የኪራይ ቤት ምን የማያመጣው ጉድ አለ!? ከእብዱ ያከራዮቹ
ከነዘመዶቹ ነበር ወስዶ ማሰር” አሉ ተናደው ። ቀስ ብለው ነገሩን
ሲያጣሩ ፣ በአእምሮ ሕመም ምክንያት ትምህርቱን ያቋረጠ የዩኒቨር
ስቲ ተማሪ መሆኑን ዐወቁ ።

“ቢሆን ነው! ሌላ ሰው እንዲህ አጥንት የሚሰብር ነገር አይና
ገርም ። እዚያስ ሥር ሥሩን ስንትና ስንት መዘዘኛ አለ አሉ ። ወይ ነዶ!”
ብለው ትክን አሉ ። የሚሰሙና የሚያዩት እያደር በዛ ። አብዲል ከተ
ባለው ተማሪ ሰምተው የጠሉትንና የተናደዱበትን ነገር ፣ ከጤነኛ
ሰዎችም አንደበት ፣ ለየት ባለና በተለባበሰ መልክ መስማት ጀመሩ ።
አንዳንድ የምክር ቤት እንደራሴዎችም ፣ ውስጥ—ውስጡን በግልጽ ፣
ባደባባይ ግን ፣ በዘዴ ፣ የአገዛዙን ሁኔታዎችና ስልት እየነቀፉና እያጥ
ላሉ እንደሚናገሩ እያደር ታወቃቸው ። መሻሻልና መለወጥ አለበት
የሚባለው ሁሉ ከነከናቸው ። ከሚወዱት የሚጠሉት በዛ ።

በየጊዜው ስለ ገጠር መሬት ፣ ጭሰኛና ባለርስት ፣ አሠሪና ሠራተኛ
ጉዳይ ፣ እሳቸው መጠንና ባሕሪውን የማያውቁት ዲሞክራሲ ፣ ነጻነት ፣
መጻፍ ፣ መናገር መሰብሰብ ፣ መደራጀት የሚባሉ ጉዳዮች በዙባቸው።

ሠልፍ — አቤቱታ — እምቢታ — ሽብር — ግድያ — እስራት —
ስደት — ሞት — ሙብት — ፍትሕ — ርትዕ — ለውጥ ፣ ለውጥ!! እዚህም
— እዚያም — የትም!

ቀኛዝማች እየናቁና እያጥላሉ ፣ ቻላ ሲሉ ፣ ጊዜ ፣ እንደ መስኖ ውሃ
ፈሰሰ ፣ ሁሉም እየታመሰ ።

# ምዕራፍ ሃምሳ ሁለት

ትንሽ የእሳት ፍንጣሪና — — —ገሥጋሽ ማዕበል

ልደታ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ለዕለተ ሰንበት ጸሎት የተሰበሰቡት ምዕመናን ፣ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥና ውጪ ፣ ወጋግራውን ፣ ግንቡን ፣ ዛፉን ፣ ምርኩዝና መቋሚያ እየተደገፉ ፣ ሰሚ ለሚሉት መልአክ ጸሎትና ልመናቸውን ያቀርቡ ነበር ።

አንዳንዶቹ አንጋጠውና አቀርቅረው ፣ ሌሎች በቁማቸው ወዳንድ ወገን ዝልስና ዘምበል ብለው ፣ ቢቃላቸው እያነበነቡ ወይም ከመጻሕፍት እያነበቡ ይጸልያሉ ። ሁሉም ከየራሱ ምኞትና ችግር አኳያ በተለያየ የሕሊና ምጥቀት ወደ ወሰን የለሹ ሰማየ—ሰማያት ቃለ ጸሎቱን ይልካል ።

የማለዳዋ ፀሐይ ገና ለጋ ስለ ነበረች አየሩ ለብ አላለም ። ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የካህናት ቅዳሴና ዝማሬ ፣ ከውጪ ቆማጦች ፣ ዐይነ—ስውራን ፣ መፃጉአን ፣ ሽባዎች ፣ ደንቆሮዎች ፣ ወዘተ . . . በተለያየ የልመና ዜማና ቃና የዕለቱን ታቦት እየጠሩ ይለምናሉ ። ዐይነ—ስውሩን ቆማጣው እየመራው ፣ ሽባውን ዲዳው እየተሸከመው እየዞሩ ፣ እየቆሙ ፣ እየተንፏቀቁና በሽታ ያለበትን ገላቸውን እያሳዩ ። ድህነት ፣ ሕመም ፣ እጦት ፣ ረኃብና እርዛት! ከሰማይም ከሰውም ይለምናሉ ።

ካህናቱ ወደ ሰንበቴ ቤት ሔዱ ። የቸኮሉ ምዕመናንም ወደየቤታቸው ።

መስበኪያው ማማ ላይ አንድ በብረት ዘንግ መስቀላቸው ላይ ትንሽ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያበቱ ፣ ከወዝ—ጠገብ ቡናማ ቆዳ ልብሳቸው ሥር ደረታቸው ላይ ካምስት ዙር በላይ ሰንሰለት የታጠቁ ፣ የተለያየ መጠን ባላቸው ማኅደሮች መጻሕፍት ያነገቱ ፣ ትልቅ የነሐስ መስቀል ደረታቸው ላይ ያንጠለጠሉና ፣ ዐፈር ከሚመስለው ቆባቸው ሥር ጥቀርሻ የጠገበ ቁጥርጥር ገመድ የሚመስል ረጂም ጸጉራቸው አንገትና ትከሻቸው ላይ የሚንከባለል ፣ መጫሚያ የለሽ ባሕታዊ ቆመው ይሰብካሉ ።

"ሰማይና መሬት ያልፋል ! ቅዱስ ቃሉ ግን አያልፍም ! የዚህ ዓለም ማንኛውም ሀብትና ንብረት ፣ ዕውቀትና ጥበብ ሁሉ ፣ ጠፊና

ረጋፊ ነው ። ዘልዓለም የሚኖርና የነበረ ፣ በረከተ—ጸጋና ረድኤቱ የማያልቅና የማይነጥፍ ፈጣሪ ኩሉ ዓለም አምላካችን ብቻ ነው ። እግዚአብሔርን በንጹሕና በትሑት ልብ ልንቀርበውና ልናመሰግነው ሲገባ ፣ አብዛኛዎቻችን ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንመጣውና ቃለ እግዚአብሔርን የምንሰማው ግን ፣ በቂም በቀል ተሞልተን ፣ በሐሰትና በተንኮል ፡ እንዲሁም በልዩ ልዩ ኃጢአት ተጠምደን ነው ። የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት የማይፈጽምና የማያከብር ሰው ወደዚህ ቦታ በመምጣቱ ብቻ ከኃጢአቱ ሊነጻና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም” እያሉ በሞቀ ስሜትና ተመስጦ ሲሰብኩ ፣ አንዳንድ በዚያም ሆነ በሌላ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሞልቶላቸው የማይገኙ ፣ ፊተ—መጣጣ ፣ አካለ—ጥንክር ፣ አረማመደ ፈጣን ሰዎች በማማው ዙሪያ ወደ ተሰበሰቡት ሰዎች ጠጋ ፣ ቆም ይሉና ወደ ሌላ አቅጣጫ ይሔዳሉ ። ልብ ብሎ የሚያያቸው አልነበረም ።

ባሕታዊው ፡ “በዚህ ዘመን ያለን ሰዎች እንጠንቀቅ! ልብሰ—ነፍሳችን ተቀዶ ፡ ግርማ ሞገሳችን ተገፏል ። ባይታየንም ነፍሳችን ተራቁታለች ። በዝሙት ረክሰናል ። እግዚአብሔር የኛ ነው ፣ እኛ ግን የእርሱ አንሆንም ብለናል ። ዓለም የተፈጠረችው ለኛ ነው ፣ የምናጣው ነገር የለም” ሲሉ —

“ቸሩ መድኃኔ ዓለም አላማርርህም ፣
ይብስ ታመጣለህ አንተ ግድ የለህም” እያለ ይለምናል አንድ ለማኝ ።

በዚያው ማማ በኩል ቀልባቸው የተጣደፈ ፣ መዳፈ—ሸካራ ሰዎች ፡ ወዳንድ አቅጣጫ ይጓዛሉ ። ሰባኪው ሲሰብኩ ፣ ልዩ ልዩ ለማኞች በተለያየ ግጥምና ዜማ ይለምናሉ ። ካህናትና ዲያቆናት ፣ ደጀ—ሰላም ውስጥ ፍትፍታቸውን እየዋጡ ፣ ዳቧቸውን እየጎመጡና ጠላቸውን እየጠጡ ያወካሉ ። ጭላጭና ፍርፋሪ ጠባቂ ለማኞች ወደ በሩ ለመጠጋት ይጣላሉ ። ከውጪ በጎዳናው ላይ የሚያማምሩ ልዩ ልዩ አቶሞቢሎች ይፈስሳሉ ።

በማማው አጠገብ እያለፉ የሔዱት ሰዎች ፣ ከቤተ ክርስቲያኑ በስተደቡብ አጥሩን ተግነው እንደ ተቀመጡ ፣ ከመካከላቸው ሁለት ሰዎች ተነሥተው ፣ ወደ ተቀመጡት ሰዎች እያዩ ቆሙ ። ሰዎቹ አንዱን የሚያውቁት ሲሆን ፣ ሌላው ግን እንግዳ ነበር ። አንዳንዶቹ የት እንዳዩት ግር ቢላቸውም ፣ ያዩት— ያዩት መሰሏቸዋል ። ቁመቱ ልከኛ ፣ ቀይዳማና ዐይኑ ጎላ—ጎላ ያለ ፣ ፊቱ ደርባባ ፣ የደስ ደስ ያለው ሲሆን ፣ አብሮት የቆመው ጓደኛቸው ብዙዎቹ የሚወዱና የሚያምኑት ፣ ስለ ሠራተኞች ጉዳትና በደል የሚቆረቆር በመሆኑ እየወደዱ ያከብሩታል ።



ባሕታዊው ፣ “ሥጋችንን ከልክ ባለፈ ምቾትና ድሎት ማንፈላሰስ አይገባም ። አካላችን በጾምና በጸሎት መገሠፅና መቀጣት ይገባዋል ። ይህን ባናደርግ ግን ፣ መንፈሳችን እንደ አለት ጠጥሮ ፣ የፈጣሪን ትዕዛዝ አልቀበል ይላል ። ይህም ከዘለዓለማዊ ሕይወት ወደ ዘለዓለማዊ ሞት ያደርሰናል” ሲሉ ፣

“የተከበራችሁ ወንድሞቼ” አለ አማረ ንጋቱ ። “እኛ እዚህ ዛሬ የተሰበሰብነው ለሌላ ጉዳይ ሳይሆን ፣ አንድ እኛኑ የሚጠቅመንንና እስበሳችን የምንረዳዳበትን ነገር ለማቋቋም ነው” ሲል ፣ ተቀምጠው የሚያዩት ሰዎች ስሜት ነቃ አለ ። አማረ ንጋቱ የሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ ጋራዥ የመኪና ሞተር አዳሽና ጠጋኝ ነው ።

“ሰው ሁልጊዜ ነዋሪ አይደለም ። እንደ እንጨት ተሰባሪ ነው ። ጧት በደህና ወጥተን ፣ ማታ በደህና ፣ እንመለስ አንመለስ ማረጋገጥ አንችልም ። በተለይም የእኛ ሥራ ከብረታ ብረት ጋር መታገል በመሆኑ ያልታሰበ አደጋ ይበዛበታል ። ያው ሁልጊዜ የምናየውና የምናውቀው ነው ። ይኸ ለሁላችንም አዲስ ነገር አይደለም ። ስንቶቹ ባልንጀሮቻችን በየጊዜው አደጋ እያጋጠማቸው አካለ ጐደሎ ሲሆኑ ፣ ከኛ ያገኙት ምንም ርዳታ የለም ። በቁማችን ካልተረዳዳንና ካልተሳሰብን ደግሞ ፣ የኛ አብሮ መሥራት ምን ፋይዳ አለው ? ዋጋ የለውም ። በየቦታው የሚገኙ እንደኛ ያሉ ሠራተኞች እስበሳቸው እየተረዳዱ ዛሬ የትናየት ደርሰዋል ። እኛም ከዛሬው ከበረታንና ካሰብንበት ፣ ከሌሎቹ አናንስም ። ምንም የሚያቅተን ነገር የለም ። እኛ እንኳ ቢያቅተን አይዟችሁ በርቱ የሚለን አይታጣም ። ታዲያ አልሳካ እያለንና እኛም ያዝ ለቀቅ እያደረግነው ብዙ ጊዜ አለፈ እንጂ ፣ አንዳንዶቻችን ታሰብንበት ውሎ አድሯል ። ዛሬ ስንቶቹ ናቸው እንዲህ በዕድርና በትናንሽ መዋጮ እየጀመሩ ለስንትና ስንት ቁም—ነገር የበቁት ። ይኸው እስተ ዛሬ ስንት ዓመት ሙሉ አብረን ስንሠራ ፣ ዘመድ ቢሞትን እንረዳዳ ፣ እንዲህ ያለ ወንድማችን አደጋ አጋጥሞታልና እንዲህ እናርግለት አንል ። የያዝናትን ብቻ ስሙኒም ትሁን አራት ፍራንክ ግፋ ቢል ሽልንግና ብር—ብር ጣል ጣል አርገን መሰስ ነው ። ታዲያ ለእንዲህ ያለው ጊዜ ደህና ዕድር ፡ ደህና ማበር ቢኖረን በየወሩ የምንከፍላትን እየከፈልን ፣ አደጋ በመጣ ጊዜ ኮርተን እንረዳዳበት ነበር ። ለሰጪውም ለተቀባዩም ደስ ይላል ። እና ጉዳታችንን እኛ እናውቀዋለን ። እኛ ለኛው ካልበረታንና አይዞህ—አይዞህ ካልተባባልን ማንም አይዟችሁ ፣ በርቱ የሚለን የለም ። ወደ መርካቶም ፣ ወደ ጉለሌም ፣ ወደ ጨርቆስም ፣ ወደ ተክለ ሃይማኖትም የሚገኙት ሁሉ ፣ ቀስ በቀስ እንዴት እንዴት ያለ ማበርና መረዳጃ አቋቁመዋል ። እኛ ብቻ ነን የቀረነው ። ሕጉ ተጽፎ ወጥቶልናል ። ንግግር አበዛሁባችሁ መሰል ? ዛሬ እንግዲህ

እዚህ የተሰበሰብንበት ዋናው ነገር ይኸው ነው” ብሎ እነስ ያለ መዝገብና ሌሎች ወረቀቶች ማገላበጥ ሲጀምር ፣ በጸጥታ ሲያዳምጡ የቆዩት የካርሎ ቤርናርዲኒ ጋራዥ ሠራተኞች መንሾካሾክ ጀመሩ ።

የማማው ላይ ባሕታዊ ፣ “የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ሳይፈጽሙ ፣ መንግሥተ ሰማያትን መመኘት ከንቱነት ነው ። ልብ አርጉ! ምፅአቱ መቃረቡንና የተነገረው ትንቢት ሁሉ መፈጸሙን አስታውሱ! ካለፈ በኋላ ቢያለቅሱና ቢትከነከኑ ፣ ዕርባና የለውም” እያሉ መስቀላቸውን ከፍ አድርገው ሲያወዛውዙ ፣ ሁሉም በጭንቀት ያያቸዋል ።

ከአማረ ንጋቱ ጐን የቆመው እንግዳ ፣ “አንዳንዶቻችሁ ታውቁኛላችሁ ፣ ደስታ ፋንታዬ እባላለሁ ። ጓደኛችሁ የተናገረውን ሁሉ ሰምታችኋል ። አንድ በጣም ጠቃሚ የሆነ ቁም ነገር ነው የነገራችሁ ። ሠራተኞች ጥንካሬ የሚያገኙት አንድነት ኖሯቸው ማኅበር ሲመሠርቱ ነው ። ማንኛውም ሰው ብቻውን መሥራትና መኖር አይችልም ። ሲሠራም ሆነ ሲኖር በችግርም ሆነ በደስታ ወቅት የሚረዳውና አይዞህ የሚለው ሰው ያስፈልገዋል ። በርታ ካሉት ይጠነክራል ፣ ‘ድር ቢያብር አንበሳ ያስር’ ይባል የለ፣ መተባበርን የመሰለ ታላቅ ቁም ነገር የለም ። በተለይም ለሠራተኞች ። አንድን ዝሆን ለየብቻችን ታግለን ለማሸነፍም ሆነ ገፍትረን ለመጣል አንችልም ። ከያቅጣጫው ተባብረን ከዘረጠጥነው ግን እንጥለዋለን ። የሠራተኞችም አንድነት በዚሁ ሊመሰል ይችላል ። ከተባበርን እንኳንና አንድ ተራ ዝሆን ግዙፍ ተራራ እንገፈትራለን ። ቢሆንም ነገሩ እንዳነጋገሩ ቀላል ላይሆን ይችላል ። ዋናው ነገር ግን ፣ ልባዊ ፈቃድና እውነተኛ ጽኑ ዓላማ ነው ። ታዲያ ዛሬ እደራጅተን ያላጠናከርነው ነገር ፣ ነገ ሊደርስልንና አለኝታ ሊሆነን አይችልም ። ዛሬ በወጉ ያልመሠረቱትና ተባብረው ያልገነቡት ቤት ፣ ነገ መኖሪያና መግቢያ ሊሆን አይችልም ። እና ከአንድነት የበለጠ ነገር የለም ። በተለይም ለሠራተኞች ። ልባችን አንድ መሆን አለበት ። ሞተን ዐውሬ ቢበላን አንሰማም ። በቁማችን እየሰማን ቀስ በቀስ ልሰውና ግጠው የሚጨርሱን ግን አሉ ። በኛ ጉልበትና ሕይወት ይኖራሉ ። እየቦጨቁና እየነጩ እንዳይጨርሱን ፣ በአንድነት ቆመን መከላከል አለብን ። ሰው ራሱ የሰው ልጅ ጠላት መሆን የለበትም ። እኛ ሰዎችን ማስተማር ፣ ማረም ፣ እንደኛም ጥረውና ግረው በላባቸው እንዲኖሩ ማድረግ እንጂ ፣ አሸንፈንም ቢሆን ማሲቃየት ፣ ፍትሕ ማሳጣትና መግደል የለብንም ። የኛ የሠራተኞች ዓላማ ሰውን ሰው አይዝረፈው ፣ ያንዱን ሕይወት ሌላው አይዋጠው መሆን አለበት ። ሰው ለሰው የሚያስብ መሆን አለበት ። ዛሬ የምታቋቁሙት ማኅበር የሥራና የኑሯችሁ ዋስትና ነው ። የመብታችሁም ማስከበሪያና ማረጋገጫ ይሆናል ። በሥራ ላይ ብዙ ችግር ይገጥማችኋል ። መሰበር ፣ መታወር ፣ አካለ



ጎደሎ መሆን ፣ ከሥራ መባረር ሊያጋጥም ይችላል ። ለዚህ ሁሉ መድኀ ማኅበር ነው ። ለወደፊቱ በሰፊው እንነጋገርበታለን ። ዛሬ ግን ፣ አንድ ቁም ነገር ያለው ጉዳይ ፈጽማችሁ መሔድ አለባችሁ ። ‘ብዙ ካወራ ጥቂት የሠራ’ ይባል የለ?” አለ ።

ሰዎቹ እርስ በርስ ተያዩ ። አንዳንዶቹ ግር ቢላቸውም ፣ ብዙዎቹ የሔዱበት ጉዳይ ወለል ብሎ ታያቸው ።

ባሕታዊው ፣ “በዚህ ፍቅርና ሰላም በጠፋበት በአሁኑ ዘመን ፣ በዚህ አረጋውያንና አብያተ ክርስቲያናት በተናቁበት ዘመን ፣ መጠንቀቅና ለአምላካችን መገዛት አለብን ። በዚህች የኃጢአት ጥሻ በሆነች ዓለም ያለው ነገር ሁሉ ያልፋል ፣ ይረግፋል ” ብለው መስቀላቸውን ከፍ ሲያደርጉ ፣ ሁሉም ለየራሱ እየሠጋ እንጋጡና አቀርቅሮ አየ ።

አማረ ንጋቱ ፣ “ለመሆኑ እንደኛ የተበደለና የተጨቆነ ማን አለ? ዛሬ ሁሉም በያለበት በማኅበር እየተደራጀ ነው ። እምና ከሥራ የተባረረው ጓደኛችን አበራ ወርዶፋ ይኸው እስተዛሬ ፍርድ አጥቶ ይንከራተታል ። ቤተሰቦቹ ይበሉና ይጠጡት አጥተው ፣ ትልቁ ልጁ ኩሊ ፣ ትንሹ ሊስትሮ ሆነዋል ። ሚስቱም ብትሆን የሰው ቤት እንጀራ ጋጋሪ ሆናለች ። ዘነበና እስገዶምም ፣ ከዛሬ ነገ ይፈጸምላችኋል እየተባሉ እንዲሁ እየተንገላቱ ነው ። እንግዲህ ይህ ሁሉ የኛ ቀደም ብሎ አለመተባበርና በርትተን ማበር አለማቋቋማችን ነው እንጂ ፣ በማበራችን እንከራከርላቸው ነበር ። እንደ ተነገረን ዛሬ አንድ ነገር ፈጽመን መሔድ አለብን” ሲል የሁሉም ስሜት ተነካ ።

አንድ የብየዳ ክፍል ሠራተኛ ተነሡና ፣ “መቼም ተዚህ የበለጠ ጥሩ ነገር የለም ። ይኸ የኔ ቢጤው ሠራተኛ ስንትና ስንት ችግር ይደርስበታል ። ተቆጥሮ ማለቂያም የለው ። ተዚህ ቀደም ተሦስት አራተዬ በላይ ከሥራ ሲያባርሩኝ ፣ አንድ ደህና ረዳት በማጣቴ ከስሼ ፣ ብወጣ—ብወርድ በምን አቅሜ ልቻላቸው? ብዬ ብዬ ሲያቅተኝ እርም ብዬ ተውኩት ። ይሁን ካላችሁ እኔ ደስ ይለኛል ፣ ያገ ለቀቅ ግን ጥሩ አይደለም ። ያስጠቃናል እንጂ አይጠቅመንም ። ኩተጀመረ አይቀር ጠበቅ ነው ። ሥር—ሥሩን ቶሎ ቶሎ መበርታት ነው ። አለያ ባይሆን መር ይሻላል ። እኔ በበኩሌ ወድጄዋለሁ ። ሌሎቻችሁም እንዲህ ያለውን መልካም ነገር እምትጠሉት አይመስለኝ” ብለው ሲቀመጡ ፣ ሁሉም የድጋፍና የደስታ ጣቅ ጣቁ ። ልቦች ተገናኙ ። ሌሎችም ተናገሩ ።

ከወደ ዳር የተቀመጠው ምንዳዬም ፣ ጉዳዩን ቀደም ሲል ሠበረ ከነገረው ነገር ጋር እያገናዘበ በመጠኑ ገባው ። ‘ተሆነልንማ መረዳዳትን የመሰለ ምን ጥሩ ነገር አለ’ አለ በሐሳቡ ።

የሠራተኛ ማኅበር ማቋቋማቸውን ለመሸፈን ሲባል ፣ በዕድር ስም የተዘጋጀው ሦስት ገጽ ውስጠ—ደንብ በእንግዳው ሰውዬ ተነብቦ እንዳበቃ ፣ ተሰብሳቢዎቹ ‘የሠራተኛ ማኅበር አባላት መመዝገቢያ ቅጽ’ በሚል ሌላ ወረቀት ላይ እየተመዘገቡ ፈረሙ ።

ባሕታዊውም ፣ “ዛሬ በዚህች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የምትገኙ ምዕመናን ፣ አርጅተው ለፈራረሱና ተጀምረው ለቀሩ የገጠር አብያተ ክርስትያናት ማሰሪያና ማደሻ የሚሆን የየችሎታችሁን ያህል ትረዱ ዘንድ በቤዛይተ ዓለም ስም እለምናችኋለሁ” ብለው ከማማው ላይ ወረዱ ።

አማረ ንጋቱ ፣ የሠራተኛ ማኅበር አደራጁ ፣ ሠዐረ ፣ ምንዳዬና ሌሎች ሁለት ሠራተኞች አብረው ከግቢ ሲወጡ ፣ እንግዳው ሰውዬ “ይኽ የዛሬው የመጀመሪያችን ነው ። ማንኛውም ነገር ሲወጠን አድካሚ መሆኑ የታወቀ ነው ። በተለይም ተደራጅተው የማያውቁ ሠራተኞችን ማደራጀት አስቸጋሪ ነው” አላቸው ። ወደ ሜክሲኮ አደባባይ በማዝገም ላይ ሳሉም ፣ ስለ አሠሪዎች ልዩ ልዩ ባሕሪ ፣ ስለ ሕግና መብት ፣ ስለ ባለሥልጣኖችና ፍርድ ቤቶች ሁኔታ ፣ ባጭር ባጭሩ ገለጸላቸው ። አደባባዩን አቋርጠው ወደ ባቡር ማቢያ በሚያስኬደው ጎዳና ጥቂት እንደ ተጓዙ ፣ አናቱ ላይ ‘የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማኅበር’ የሚል ጽሑፍ ከተለጠፈበት አነስተኛ ባለ ሁለት ፎቅ ሕንፃ ገቡ ።

አዳራሹ ውስጥ ሠላሳ ያህል ለሚሆኑ የሠራተኛ ማኅበራት ተወካዮች ፣ አባላትን ስለ ማበራከትና ስለ ጋራ ስምምነት ጥቅምና አቀራረብ ፣ ስለ ክስ አመሠራረትና ክርክር ፣ ከሥራ የታገዱ አባላትን ስለ መርዳት ፣ የጽሑፍና የቃል ገለጻ ትምህርት ሲሰጣቸው ስለ ነበር ፣ እነ ምንዳዬም በዚያው ተካፈሉ ። አያሌ ሠራተኛ ነክ ጉዳዮችን ያካተተ መጽሔትም ታደለ ። መግቢያውን ሲያነቡ ፣

“እየኽ ፣ ማታ—ማታ ምምሃራችን አሁን ቁሩብ ጠቀመን” አለው ሠዐረ ።

“እውነክን ነው ፣ ይኽው እኔም ደህና አንዳንዱን እያገጣጠምኩ ማንበብ ለመድኩ” አለ ምንዳዬ ።

“እኔኮ ረሳሁ እምበር ሀገረይ ሳለሁ ፣ እንዳ ቄስ ተምሬ ነበርኩ።”

“እኔስ ምናምኒት አልተማርኩም ፣ ደሞ ይህን ያህል ሙያ።”

“የሚመጣ ያለ ጊዜ እነዚ ማኅበር ሠራተኞሽ ሚያስተምሩ ያለ ቤት ትምህርቲ ገብተን እናኛሽላል ፣ እነሱ ቸርተፊክ ይሰጣሉ።”



“እንግዲህማ ምኔ ሞኝ ነው ። ግድ የለህም ጉዳዩ ሁሉ እየገባኝ ነው።”

ትምህርቱ ተጠናቆ ፣ እነ ምንዳዬ ተጨማሪ መጽሔቶች ተሰጥተዋቸው ሲወጡ ፣ ‘ለካ ሁሉም በያለበት አንጀቱ አሯልና! ወይ መሰንበት ! ቆየት ስልማ ገና ብዙ ብዙ ነገር እሰማለሁ’ አለ በልቡ ። ከዋል—አደርም ጉዳዩ ስለ ገባው ፣ ስለ ወዳጅና ጠላት ምንነት የነበረው ግንዛቤ መለወጥ ጀመረ ።

ጊዜ እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰ ፣ ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደረደሩ — — ምንዳዬ ቦጋለና ሠዐረ ተስፋ ጋብር በኢ.ሠ.አ.ማ. አማካይነት ሠንጋ ተራ በሚገኘው ንግድ ሥራ ት/ቤት ይሰጥ የነበረውን መሠረተ ትምህርት ተከታትለው ቀደም ሲል በግል የተማሩትን ካሻሻሉ በኋላ ፣ ታኅሣሥ 15 ቀን 1962 ከ5,025 ሠራተኞች ጋር ‘ከማይምነት ነጻ’ የሚል የምስክር ወረቀት ተቀበሉ ።

## ምዕራፍ ሃምሳ ሦስት

ቀኛዝማች ፣ በመወዳደሪያ ክልላቸው ውስጥ ፣ ከድሆች ጭራሮ በር እስከ ሀብታሞች ልግ ማንቃ ፣ ከቤተ ክርስቲያን ደጀ—ሰላም እስከ ጋለሞታ ጓዳ ፣ ከተራ መሸታ እስከ አካባቢው ትልቅ ቡና ቤት ፣ ዓርማቸው ተለጥፎና ዝናቸው አድጎ ፣ ያልሠሩት ሥራ ተጋንኖ ተወርቷል ። ዐልፎ ዐልፎ ፣ "ኤዲያ!ቢመረጡ ባይመረጡ ፣ ለኛ ምን ሲፈይዱልን ነው ? ያው በገሌ አለች ድመት" ቢባልም ፤

"ደሞ ዛሬም ፣ በበሬ ተምሳሌት መመጣቱ ለምን ይሆን? እያረሳችሁ ወዲህ በሉት ለማለት ይሆን? እንዲህ አረግላችኋለሁ ፣ እፈጥምላችኋለሁ እየተባለ ሲቦተለክብን ተክረመና ፣ ያው ለራሳቸው ቁና—ቁና ብር ቲዝቁብን ከረሙዱ ፣ ለኛ ምን ጥብ ያለልን ነገር አለ? እኛ መችአጣነውና ዓመት የለፋንበትን ይገፋፍፉንና ባንድ ቀን መብል እንደልላችሁ ይሉናል" ቢሉም ፤

"ዘንድሮማ አፍ—ለቆባቸዋል ፣ ያንን ለምድ እሚያክል ኮቶግራፋቸውን እየበሬአችን ግንባር ላይ ሊለጥፉት ጥኢት ነው የኸራቸው ! የኛ አገር ሹሞች እያ ሸዋ እሚሉ አገር ደርሰው ቲመጡ ይብስባቸቸዋል!" ቢባልም ፣ ቀኛዝማች ከምክር ቤት አባላት በሰሙት የንግግር ልምድና ፣ ከልዩ ልዩ ሰዎች ጋር በተገናኙ ቁጥር በቀሰሙት አንዳንድ የአነጋገር ፈሊጥ በመጠቀም ፣ አጠር ወይም ረዘም ያለ ንግግር በማድረግ ፣ የአብዛኛውን ተራ ሰው ቀልብ በተስፋ ቃላት ሸነጋግለው ፣ በድጋሚ የሕግ መምሪያ ምግር ቤት አባል ሆነው ከተመረጡ ስምንት ወራት አልፈዋል ።

የጉዳዩ መሳካት ብዙዎቹን የቀኛዝማች ዘመዶችና ደጋፊዎች ያረካ ቢሆንም ፣ በተለይ ግን ፣ "አሁን ከኔ ሌላ ማንን ፈጥረሃል ? ምቀኞቼን ሁሉ ጠራርገህ ለዚህ አበቃኸኝ ፣ እስቲ አሁን ያንተን ውለታ በምን ይመልሷል" ያሉትን ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱን ፣ በምርጫው ወቅት ባሳየው ትጋትና በአረጋሽ በኩል በቋጠራት የሥጋ ዝምድና ሰበብ አንድ ጥማድ የሚያውል ማሳ የተሰጠው ቸርነትንና ፣ በወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ግፊትና በእርሱም አባባል የተሰበረ ስሙን ለማደስ ባደረገው መሯሯጥና ባሳየው ትሕትና ከቸርነት እኩል ማሳ የተፈቀደለትን አፈሣን ፣ የምርጫው ውጤት በጣም አስደስቷቸው ነበር ።

* * *

የሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ ጋራዥ ሠራተኞች "የ16ቱ የተሽከርካሪ ሕይወት ማደሻ ሠራተኞች አጠቃላይ ማኅበር" አባል መሆናቸው ከተረጋገጠ ጀምሮ ዋና አሳባሪና ቀስቃሽ ናቸው በተባሉት ላይ ፡ ልዩ ልዩ ክትትልና ትኩረት ማድረግ ተዘወተረ ።

አሠሪው የሥራ ተቆጣጣሪና ደጋፊዎቹን እያስተባበረ የራሱን ጐራ ሲያጠናክር ፣ ሠራተኞቹን ከፋፍሎ ትግላቸውን ለማዳከም ግብግቡን ተያያዘው ። እርስ በርስ እንዳይተማመኑም በተለያየ ዘዴና ሁኔታ ፣ ለተወሰኑ ሠራተኞች የማታለያ ደመወዝ ጭማሪና ጉርሻ ፣ የተጠራቀመ የዓመት ፈቃድና ክፍያ በመስጠት ፣ እንዲሁም ከመደበኛው የሥራ ሰዓት ውጪ መርጦ በማሠራት ፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በማድረግና አንዱን ጠርቶ ሞቅ ያለ ሰላምታ በመስጠትና ምክር ቢጤ ነገር ሹክ በማለት ፣ ደመወዝ የሚከፈልበት የሦስትና አራት ቀናት ልዩ ፈቃድ በመፍቀድ ሠራተኞቹን ለመነጣጠል የሚያደርገው ጥረት ተጧጧፈ ። በማኅበሩ ውስጥ እልቅና አላቸው የሚባሉትን ተጠሪዎች እንደ ጥፋተኛና ወንጀለኛ በመቁጠር በሚገኘው አጋጣሚ ሁሉ መቅጣትና መግቢያ—መውጫያቸውን ተከታትሎ ማጥቃትና ማስጠቃት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ተዶለተ ። ዱልቱ ሐሳብ ሆኖ አልቀረም ። ካርሎ ከውስጥ ቀበሮዎችና ከውጪ መሰሪዎች ጋር መክሮ የማስበርገጊያና የመቀጣጫ ኃይሉን በማኅበሩ ተጠሪዎች ላይ ለመሰንዘር ቆርጦ ተነሣ ።

የሠራተኛው ማኅበር ተጠሪዎችም ፣ በድብቅ እየተሰበሰቡ የአባላቱን አንድነትና ጥንካሬ ለማሳደግ የማስተማሩን ሥራ በሰፊው ተያያዙት ። ምንጊዜም መተማመኛቸው መማማል ነበር ።

የሁለቱ ጐራዎች ፍጥጫ በግልጽና በስውር ተጋጋመ ።

ሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ ፣ ሕድሩንና ሌሎች ሁለት የሠራተኛ ተቆጣጣሪዎቹን አስከትሎ ፣ ከባለሥልጣኖች ጋር በመመሳጠር ፣ የሠራተኞችን የመብት ጥያቄ ለማንተት የታወቀ ጠበቃ ቀጠረ ። ጠበቃው ከልዩ ልዩ ድርጅቶች የተባረሩ ሠራተኞችን አቤቱታና ይግባኝ በቀጠሮ በማራዘም ፣ ሠራተኞቹ ተንገላተው እንዲንበረከኩና ሌሎቹም የነሱን ችግር አይተው በማኅበሩም ሆነ በራሳቸው ላይ እምነትና ተስፋ እንዲያጡ ፣ ከሹማምንቱ ጋር በሚተበትበው ተንኮል ከፍ ያለ ትምክህትና ትዕቢት የሚሰማው ሰው ነው ።

አቶ አበራ ሺጉልቴ የሲኞር ካርሎ ወኪል ነገረ ፈጅ ከሆነ ጀምሮ በተለመደ የማሸመቂያ ስልቱ እየተጠቀመ ፣ ሠራተኞቹ በእነ



ማን መሪነት የትና ሥቼ እንደ ተደራጁ ፣ ቀንደኛ አስተባባሪዎች እነማን እንደሆኑ ፣ ከዋናው የሠራተኞች ማኅበር ጽሕፈት ቤት እስከ ሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በዘረጋው የብር መረብ ተጠቅሞ አንድ ባንድ ደረሰበት ።

ይህንኑ አድራጎቱን የተረዱ የማኅበሩ ተጠሪዎችም የተንኮል ገመዱን ለመበጣጠስ የተባበረ ጥረት ጀመሩ ። ትንቅንቁ ከረረ ። የሠራተኛው ማኅበር ለሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ የጋራ ስምምነት ውል ጥያቄ አቀርቦ ከብዙ ውጣ—ውረድና ውዝግብ በኋላ ድርድሩ ተጀመረ።

ይብስ ተካረሩ!

የሠራተኞቹ የመሥራት ፍላጐት በመቀነሱም የድርጅቱ ገቢ አሽቆለቆለ ። የድርድሩ ሥነ ሥርዓት ተጣሰ ፣ ሕጋዊ ግዴታ ተፋለሰ ተባለ ። ጠበቃው ብርዑን ፣ ሠራተኞቹ ክንዳቸውን አነሡ ።

አቶ አበራ ሺጉልቴ ፡ "ማኅበሩ ፣ የጋራ ስምምነት በሚካሔድበት ወቅት ሕገ—ወጥ ድርጊት በመፈጸሙ በድርጅቱ ላይ ከፍ ያለ ኪሣራ አድርሷል" በማለት ክስ መሠረተ ። ከዚያም አሠሪው ቀስቱን አነጣጠረ ። አማረ ንጋቱና ሠዐረ ተስፋ ጋብር ዲላማ ውስጥ ገቡ ። ጠበቃው ፡ "ሥራቸውን ተግተው ባለመሥራታቸውና ሙሉ ችሎታና ኃይላቸውን በሥራ ላይ ባለማዋላቸው ፣ በድርጅቱ ላይ ከፍ ያለ ኪሣራና በደል ከማድረሳቸውም በላይ የተጀመረውን የጋራ ስምምነት ውል በሥራ ማቀዝቀዝ አስገድደው ማፋጠን ስለሚፈልጉና ድርጅታዊ ሰላም ስለነሱ ከሥራ ታግደዋል" በማለት ያቀረበው ጽሑፍ በሲኞር ካርሎ ተፈርሞ ለሁለቱ የማኅበር ተጠሪዎች ተሰጣቸው ።

እናም እየተጢያጢያሰ ጊዜ እንደ መስኖ ውሃ ፈሰሰ———

አቶ አበራ ሺጉልቴ ፣ መሠሪ ችሎታውን ፣ የሠራተኞቹ ማኅበር የአንድነት ጥንካሬውን የሚያሳዩበት የመጨረሻ ትንቅንቅ ወቅት ደረሰ ። ግብግቡ ጦፈ ። ሠራተኞቹ መሣሪያ ማሰናከል ፣ ሥራ መዘፍዘፍና ማበላሸት ሲቀጥሉ ፣ ድርጅቱም ከጊዜ ፣ ደቂቃን ፣ ከሰበብ ብረትዛግ ወረዛን ፣ በመቆጣጠር መቅጣት ጀመረ ። እነ አማረም ክስ መሠረቱ።

በቀጠሮው ዕለት ጧት ፣ እነ አማረ አሠሪና ሠራተኛ ማስማሚያ ክፍል ፊት ለፊት ከተሰበሰቡት አዳዲስና ግልቱ ቢጤዎቻቸው ጋር አብረው ቆሙ ። ሠራተኞች ከየትም ይምጡ ከየት ብሶትና በደላቸውን ይወያያሉ ። ቋዛሚያቸው ተመሳሳይ ፣ ማንቋቸው አንድ ነው ። የማስማሚያ ክፍሉ ቢሮዎች ተራ በተራ ሲከፈቱ የከሳሾቹ ወሬ ይቀንስና ቀልባቸው ወደየተቀጠሩበት ቢሮ ይዞራል ። ያረጀ የመጥሪያ

ወረቀትና የተቀዳደደ ማመልከቻ አያጡም ። በቃል ከማብራራት ማመልከቻ ማቅረብ ይቀናቸዋል ። አንድና ሁለት ሆነው ወደየተቀጠሩበት ቢሮ ይጠጉና በሩን በቀስታ ያንኳኳሉ ። እየፈሩ ። በዝግታ ከፍተው አንገታቸውን ብቅ ያደርጉና በተደጋጋሚ እጅ ይነሣሉ ። ቀስ ብለውም ይገቡና በሩን በዝግታ ይዘጉታል ፣ ወይም ከፊት እንዳለ ይተዉታል ። ማን ወይም እነማን መሆናቸው በቀላሉ ይታወቃል ። ነገር አያበዙም ባጭሩ ይጠይቃሉ ። ባንዲት ቃል ይመለስላቸዋል ። አሠሪዎች ምንጊዜም ዘግይተውና ተዝናንተው ስለሚደርሱ ፣ ወይም እንደማይመጡ በስልክ ስለሚገልጹ "ጠብቅ" የተለመደ መልስ ነው ።

ሠራተኞቹ ማስማሚያ ክፍል ፊት ለፊት ሲሰበሰቡ ፣ "እኛን ማን ከሰው ቆጥሮን! ጉዳዩ የሚያልቀው ማታ ማታ" ይላል አንዱ ።

"እኛ ከዛሬ ነገ ይፈጸምልናል እያልን ስንንገላታ እነእጅሬ በስልክ ይፈጸሙታል" — ይመልሳል ሌላው ።

"ዘመድና ጉቦ እያለ በየት? ከኛ ምን ይገኛል? ያው ተባይ ነው!" ሲል ሌላኛው ፣ "ተባይዋም የመሔጃ እጦት ነው! ማን አባቷ ያስጠጋታል! ሁሉም የሚመዘምዙት እኛኑ ነው ። እዚህ የታጐሩትስ ምን ሲጠቅሙን" ይላል ።

"እኔ አንዲት ነገር ሳይፈጸምልኝ በቀጠሮ ብቻ ይኸው መንፈቅ አለፈኝ! የዛሬን አይቼ መኻል አናቱን ብዬው የመጣው ይመጣል!"

"ከሆነስ እሱን ብቻ አይደለም ፣ እዚህ ከተወሸቁትም ጨመር ማድረግ ነው ።"

እልፍ—እዕላፍ የመከራ ሮሮ! የጭቆናና የግፍ ዓይነት! የአቤቱታ ክምርና የቀጠሮ ርዝማኔ ፣ ብስጭት ፣ ንዴት ፣ በቀል ፣ ዛቻ! ዐልፎ ዐልፎ ግን ፣ ስለ ትክክለኛ አሠራርና ውሳኔ የአስማሚ ስምና የቢሮ ቁጥር ተጠቅሶ ይነገራል ።

የቀጠሮ ሰዓት ካለፈ በኋላ ፣ እንደ ቅቤ ቅል የወዙና ብስል ሙዝ የመሰሉ ፣ ትከሻቸው ያበጠ ቀፈታሞች የፈለጉትን ቢሮ ከፍተው ወይም አየት አድርገው ሲመለሱ ደንታ የላቸውም ። ከየትም ይምጡ ከየት ፣ ሠራተኞች ያውቋቸዋል ። እናም ደማቸው ይፈላል ።

ከናፍራቸው የቀለመ ፣ ጸጉራቸው በልዩ ልዩ ጥቅልና ብትን ሥራ የተበጀ ጉንጩ ትንቡክቡክ ፣ ዐይነ ገብ ኩንስንስ ሴቶች ፣ ማራኪ ልብስ ለብሰው እየተረገረጉ ልብን ከሚቀማ ፈገግታ ጋር ወደየቢሮው ሲገቡ ፣ ጉዳያቸው ተሳክቶና ጥያቄአቸው ተሟልቶ ይመለሳሉ ። በአቤት ባይ ሠራተኞች አርጌ ጫማ ሽታ ፣ በባዶ ሆድ ትንፋሽና የላብ ጠረን



የሚበረዘው የቢሮ አየር ፣ በወይዛዝርቱ ልዩ ልዩ ሽቶና ቅባት ሲከለስ አቅለሸላሽ ፣ ቅይጥይጥ ሽታ ይፈጥራል ።

በክርክር ጊዜ አሠሪዎች እንደልብ ተዝናንተው በረጂም ንግግር ሐሳባቸውን ሲገልጹ ፣ ሠራተኞች ግን ባጭሯ ተናግረው ዝም ይላሉ ። ስለ ጉዳያቸው የሚነገረውን ሐሰት ፣ የተደበቀውንም እውነት ያውቁታል ። የሕጉ ደባ እስከሚገባቸው በነጋሪት ጋዜጣው ያምናሉ ።

በክርክር ወቅት ሠራተኞች ቶሎ ይናደዳሉ ፤ ባንድ የጋራ አቤቱታ ተሰብስበው ካገቡ ተራ ሳይጠብቁ የታያቸውን ይናገራሉ ። ይኸኔ አንዳንድ አስማሚዎች የአሠሪዎችን ሁኔታ ይገመግሙና ፣ "ባለንብረቶቹ ምን ያርጉ ? እዚህ ሕግ ፊት እንዲህ የሆናችሁ ፣ እዚያማ እንዴት ልትሆኑ ነው ? በማኅበር ያደራጃችሁ ክፍል ምንድነው የሚያስተምራችሁ ? ባለድርጅቶቹን እንዴት ማነ ር እንዳለባችሁ አያስተምሯችሁም ማለት ነው ?" ሲሉ ፣ ሠራተኞቹ አዝማሚያው ቢገባቸውም ዝም ይላሉ ።

"አዬ ጌታዬ! ይኸማ በቀላሉ ነው! ምነው አንድ ቀን በኔ ኪሣራ ብቅ ብለው አሠራርና አኳኋናቸውን ባዩልኝ ። ትዕዛዝ እሚባል ነገር አይቀበሉም ። ጭቅጭቁን ትታችሁ ሥራችሁን ሥሩ ካልንማ ፣ ጉድ ይፈላብናል ። እኛ እኮ የበደለን ሕጉ ነው ። በሆነ ባልሆነው ሲከሱ መጥሪያ ትሰጧቸዋላችሁ ። መብታቸውን መቼ ከለከልን ። የበጠበጠን ደግሞ ይኸ ማኅበር እሚባል ነገር ነው ። ቢጠቅማቸው እኮ ምንም አል ነበረም ። የማይደረገውን እናደርጋለን ፣ የማይገኘውን እናስገኛለን እያሉ በርትታችሁ በጥብጡ ይሏቸዋል መሰል ይኸው እንደምታዩት ያፋጁናል" ይላል አሠሪው ።

* * *

አማረ ንጋቱና ሠዐረ ተስፋ ጋብር ፣ ከነገር በላቹ ጠበቃና ከሴኖር ካርሎ ብር ጋር ትግል ገጥመው አያሌ ወራት ከተንገላቱ በኋላ ፣ "ድርጅቱ ሠራተኞቹን ከሥራ ያገዳቸው ፣ በማስረጃ በተረጋገጠ ጥፋትና የዲስፕሊን ጉድለት ሳይሆን ፣ የተጀመረውን የጋራ ስምምነት ለማንተት ከሥነ ሥርዓቱ ውል ውጪ የተፈጸመ ድርጊት በመሆኑ ፣ አለአግባብ ከሥራ ከታገዱበት ጊዜ አንሥቶ የነበረው ደመወዛቸው ተከፍሏቸው ወደ መደበኛ ሥራቸው እንዲመለሱ እንዲደረግ" ተብሎ በማስማሚያ ክፍል በመወሰኑ ፣ ድርጅቱ ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የይግባኝ አቤቱታ አቀረበ ።

ቦርዱ ሁለት ወራት ሙሉ ጉዳዩን መርምሮ ከሳሽና ተከሳሽ እንዲቀርቡ አድርጎ ፣ ማኅበሩ ከአንድ ወር በኋላ መልሱን እንዲያቀርብ

ግልባጭ ሲሰጠው ፣ አማረ ንጋቱ ፣ "ቀጠሮው ረዘመብን" ብሎ ለአምስቱ ዳኞች የቃል አቤቱታ አቀረበ ። እንደ ድብኝት የተድበለበለው የመኻል ዳኛ ፣

"የቀጠሮውን ጊዜ ማሳጠርም ሆነ ማስረዘም የኛ ሥራ ነው ። የት እንዳለህ ማወቅ አለብህ! እዚያ ድርጅቱን ስታስቸግሩ ትኖሩና እዚህ ደግሞ አላሠራም ትላላችሁ! ያስገደዳችሁ የለም! ቀጠሮ ረዘመብን ካላችሁ ክርክሩን መተው ትችላላችሁ ። ተስማምታችሁ ሥሩ ሲሏችሁ ታስቸግሩና — —" ብሎ በክፉ ዐይን አየው ።

ከችሎት ሲወጡ ጠበቃው በደስታ ሲፈግ ፣ እነ አማረ ንጋቱ ተከኑ ።

"እነዚህ ግፈኞች ምን አሏችሁ?" አለ "የተባበሩት የእንጨት ሥራ ሠራተኞች ማኅበር" መሪ ።

"ያው ቀጠሮ ነው ፣ ነገር ማጓተት ፣ ሌላማ ምን ሲረዱ !" አለ አማረ ዐይኑን ጕልጉሎ ።

"ዱሮስ ከአራት ለአንድ ምን ይገኛል?" አለ ሌላ የሠራተኛ ማኅበር መሪ ።

"አራት ለአንድ ደሞ ማለት ምን ማለት ነው?" አለ አንዱ ቀገርሞ ።

"ዳኞቹን አላየኻቸውም እንዴ? አምስት እኮ ናቸው ፣ ሦስቱ የመንግሥት ፣ አንዱ የአሠሪዎች ወኪል ሲሆኑ ፣ አንዱ ደግሞ የኢ.ሠ.አ.ማ. ተወካይ ነው ። በኛ ላይ ቅንጣት ጥፋት ሲገኝ ከነዛ ሕጋቾው ጋር ይረባረቡብናል ።"

ክርክሩ በቀጠሮ እየተራዘመ ተወሳሰበ ። አብዛኛዎቹ የካርሎ ቤርናርዲኒ ሠራተኞች እነ አማረን እስከ መጨረሻው ለመርዳት ወሰኑ። አራት ሠራተኞች ግን ፣ ውስጥ—ውስጡን እየተደለሉ ሲያፈገፍጉ ፣ ሁለቱ ደግሞ በገዛ ፈቃዳቸው ከማኅበሩ እንደወጡ በጽሑፍ ገልጸው ለድርጅቱ በግልባጭ እንዳስታወቁ ፣ የካርሎ አቸፍቻፊዎች በደስታ ተፍነከነኩ ።



## ምዕራፍ ሃምሳ አራት

ሸዋርካብሽ በምታገኘው ገቢ የተለያዩ ልብሶችንና ርካሽ ብልጭልጭ ጌጣጌጦችን ፣ ተራ ሽቶና ቅባቶችን እየገዛች ፣ ከቢጤዎቿ ጋር በመፎካከር የልታይ—ልታይ ኑሮዋን ተያይዛዋለች ። አረማመድዋ ፣ አነጋገርና ቅልጥፍናዋ ፣ እንዲሁም ወንድን አሣሥቆ የመግፈፍ ችሎታዋ ፣ ከሷ ቀደም ብለው ከጀመሩት ሴተኛ አዳሪዎች በለጠ ።

አጠር ባለ ቀሚስ ጭን ማጋለጥን ፣ ወዳጆቿ ሲመጡ መኩነስነስን ፣ ጠቀም ሳለ ክፍያ ማድላትን ፣ በቀላሉ ዐወቀችበት ። በአልጋ ላይ ችሎታዋም ቢሆን "እ—እ—እ— የዋዛ አይደለችም" የሚሏት በዙ ። በዚህም የተነሣ የለየላት ወረተኛ ሆነች ።

ወይዘሮ ደጅ ይጥኑም ባሳባቸው አዳሪ ፣ አፍጣጭና ገልማጭ የሌለበት ኑሮ ፣ በመጀመራቸው አነጠነጡ ።

ቀኛዝማችም ፣ በአቶ ወርቅነህ መዘውር ደባና ትብተባ ፣ እያደር ወደ ውጪ እየተገፈተሩ መውጣታቸውን ቢያውቁም ፣ ትዝታቸው ሲጫርና በፍትወት ሲቃጠሉ ሰተት ብለው ገብተው አበራር ደው መውጣቱን ስለ ለመዱት ፣ "እኔ ምን አታገለኝ ፣ የጕዱኝ መስሏቸው ጠቀሙኝ ። ቀድሞውንስ ቢሆን ለየትኛው ርስቷና ጉልቷ ነበር ልፋቴ? ታሳብ ዳን ሲለኝ ነው" እያሉ ራሳቸውን ደለሉት ።

ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ ፣ ከቡና ቤቱና በስተጀርባ ካሉት አምስት የመኝታ ክፍሎች የሚያገኙት ዕለታዊ ገቢ የልብ—ልብ ሰጣቸው ። ሁለቱም ልባቸው እየተራራቀ ፣ የየራሳቸውን የጥቅም ጕዳና መደልደል ቀጠሉ ።

* * *

ምንዳዬ ፣ ለነአማረ ከሚያዋጣው ወርኃዊ መዋጮና በግሉ ለሠዐረ ከሚሰጠው አነስተኛ ድጎማ በላይ ፣ የሠራተኛ ማኅበርን ምንነት እየተገነዘበ በመምጣቱ ፣ እነማንን ትቶ ፣ እነ ማንን እንደሚከተል ጠንቅቆ ዐወቀ ። በሠራተኞቹ ጉዳይ ከልብ የመሳተፉ ወሬ በመሰማቱም ፣ አሠሪው ባይነ—ቁራኛ ያየው ጀመር ። እንዲያውም ስለ አመጣጡና አቀጣጠሩ ፣ ባሉባልታና በአሚታ በመተንኳኮስ በነገር ወጋጉት ። አልበረገገም ። ይልቁንም ቅንና ለሠራተኛ ተቆርቋሪ መስለው

ሠራተኛን እርስ በርሱ እያናከሱ የራሳቸውን ኑሮ የሚገነቡ አሠሪዎች እንዳሉ ለይቶ በማወቁ ፣ ብስጭቱ ጥላቻን ዘራ ።

"ለካ የገጠሩ ርኩቻና ተንኮል እዚህም አለና? እዚያ ገበሬው በመሬት እየተናቆረ ይፋጃል ፣ እዚህ ደግሞ የጣጣውና የሸሩ ብዛት!" አለ ተገርሞ ።

ብዙም ሳይቆይ የድርጅቱ ቀበት ወደ ምንዳዬ ዞረ ።

ሲኞር ካርሎ እንደ ታዛቢ ፣ ሕድሩና ጠበቃው ዋና ተናጋሪ ሆነው ምንዳዬን ቢሮ ውስጥ ሲያነጋግሩት ፣ "አንተሳ ዳህና ሰው አልነበር ካም ፣ ማኅበር ግባ ኢሉ ማን መኽረካ?" አለው ሕድሩ ።

"ለዚህ ደሞ ምን ምክር ያሻዋል ፣ እኔው ነኝ ፈቅጄ የገባሁት።"

"ምን የሚጠቅመካ ነገር አገኘኽ? ሞኝነትካ ነው!"

"መስሎህ ነው ፣ በመጀመሪያ የሚያታልል አዚም አለበት ። ምንም የሚያደርግልህ ነገር የለም ። እስክታየውና እስክታውቀው ነው። ያልሞከረው የለም ። ዋል—አደር ብለህ ምን ብሎ ነበር ትላለህ" አለ ጠበቃው በትምክህት ።

"እኔስ ባየውና ብሞክረው ምን አለበት? እናንተን ምን ይጎዳ ችኋል?" አለ ለስለስ ብሎ ።

"ለአንቴ ነው የ ሚጎዳህ ያለ እንጂ ለእኛማ ምንም አይትጎዳን።"

"ነገሩን ቀደም ብለህ እንድታውቀው ብለን ነው እንጂ ፣ ተጠ ቃሚና ተጎጂውንማ ወደፊት ታየዋለህ ። አብዛኛውን ጊዜ እንዳንተ ያሉትን የዋህና ትጉህ ሠራተኞች ከሥራችሁ ለማፈናቀል ሲሉ ፣ በማኅበር ስም ይሰበስቡና በገንዘባችሁ ይጠቀሙበታል ። ሥራ ሳይሆን ነገር የ ሚወዱ ሰዎች የ ሚኖሩት በእናንተ እጅ ነው ። እነሱ ለሚለፈ ልፉት ከንቱ ቃላትና ተስፋ እናንተ ላባችሁን እያንጠፈጠፋችሁ ትከፍ ሏቸዋላችሁ ። የማይገኘውን ይገኛል እያሉ ፣ በምኞትና በግዙፍ ተስፋ እንደ ከብት ይነዷችኋል ። ሠራተኛ ሲባል የዋህ ነው ። የማይሆነውን ሁሉ ይሆናል በማለት አይዟችሁ ፣ አይዟችሁ ይሏችሁና ከደህና እንጀ ራችሁ ላይ ያፈናቅሏችኋል ። ስትቸገሩ ግን መለስ ብሎ የ ሚያያችሁና የሚያስታውሳችሁ የለም ። የማናውቅ አይምሰልህ ፣ ብዙ ብዙ ነገር እናውቃለን ። በየሥርቻውና በየጓዳው እየሰበሰቡ ሲሰብኳችሁማ ፣ ገደ ሉን ሜዳ ፣ ድንጋዩን ዳቦ ያስመስሉታል ። ከሰማይ በታች ያለው ሁሉ የናንተ ነው ይሏችኋል ። ይኸን አትክደኝም ። እጅግ የ ሚያሳዝነው ደግሞ ፣ እንዳንተ ዓይነቱን የትልቅ ሰው ወገን እየደለሉ ሲያታልሏ



ችሁ ነው ። ሌላው እንኳ ከየትም የመጣ ብራሪ ነው ። ምን ሰው አለ ባቸው ። ቢቸግር ነው ። ይኸን አንተም ታውቀዋለህ ፣ መናገር አይገባ ኝም ። የሆነ ሆኖ ፣ 'ምነው ቀድሞውኑ በቀረብኝ' እያሉ የኋላ ኋላ ከመ ጸጸት ፣ ካሁኑ መጠንቀቅና በማኅበር ስም ከሚያወናብዱ ሰዎች መራቅ ሳይሻልህ አይቀርም ። እኔ በወንድምነቴ ልምክርህ ብዬ ነው" አለ አቶ አበራ ሺጉልቴ ።

"አሁን ምን አርግ ነው እምትሉኝ? ምን አጠፋሁ? ሥራዬን አላጓደልኩ?" አለ በርጋታ ።

"ሥራህ ብታጓድልሞ ካልእ ብዙ ነገር ያጋጥመካ ነበረ ። የምታ ደርጉ ያላሽሁ መጥፎ ነገር ሁሉ እኛ እናውቃል ። አንተ ዝም ኢልካ ሥራሕካ ብትሠራ ጥሩ ነበረ ። ሌሎሽ ያጋጠማቸው ያለ ሁሉ አይተ ሃል ሙሽ? እኔ እንዳንተ ሳለሁ ቀደም አይቸዋሎሁ ። አይትታለልላ ሸው ። ኩሉ ሰው ለራእሱ ነው የሚጠቅም የሚፈልግ ። አንቴ ዶሞ ብዙ ታውቃል ። ስለዚ ብትሐስበሉ ይሻላል ። በተለዪ እሳቸው ሲኞር ካርሎ ከቀኝዝማቲ ጋር ስለሚያውቁ ያለ ተአግሠዋል ። አንድ ሠራሕ ተኛ ከሥራሕ ቢወጣ እሱ ኖው የሚጎዳ እምበር ፣ እሳቸው ሲኞር ካርሎ ዋላ ሐንቲ አይሆንም" ብሎ ወደ ሰውዬው ሲመለከት ፣ ፈረንጁ ጠቅላላ ጉዳዩ የገባው ለመምሰል ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ።

ይህ በሆነ በሳምንቱ ቀኛዝማች ከጠበቃውና ከሕድሩ የሰሙትን አሉባልታና ስሞታ ሁሉ አንድ ባንድ ነገሩት ።

"እርስዎም ለምን ማኅበር ገባህ ነው እሚሉኝ?" አለ ምንዳዬ በለዘብታ ።

"አዎ! ምን ያረግልሃል? አትሥራ ብሎ የከለከለህ የለ! ምን ችግር ደረሰብህና ከማንም ጋጠ—ወጥ አድመኛ ጋር ታብራለህ?"

"ይኸኮ አድማ አይደለም ። መብታችንን ለመጠየቅ ያክል እንጂ ለሌላ አይምሰልዎ።"

"መች አጣሁት ? ከኔ የተረፈ ነው ! የትኛው መብትህ ተጓደለ ? ዋ አለማወቅና አዙሮ አለማየት ፣ እስኪ ራስክን መለስ ብለህ እየው ! ለዚህ ሁሉ የደረስከውኮ በማኅበር አይደለም ። አንተ የራስህ መብት ካልተነካና አትሠራም ብለው ካልከለከሉህ ፣ ስለ ሌላው ምን ዶለህ ? ፈረንጁ ደግ ሰው በመሆኑ ነውዪ ፣ በገዛ ንብረቱ አላሠራም ቢል ማን ይከለክለዋል ። ሰው ደሞ ጥቅም ላለውና ለሚያስመሰግን ነገር ቢደክም ጥሩ ነው ።"

"አሄሄ! አርስዎ የማያውቁት ስንትና ስንት ችግር አለ ። እኔም የገባኝ ቀስ—በቀስ ነው ። አሁን በቅርቡ ነው ዐይኔን መግለጥ የጀመርኩት ። አብዛኛውን ጊዜ አሠሪዎች የሚያቀርቡት ስሞታ ሐሰት ነው ። ሌት ተቀን ቢግጡን ደስታቸው ነው ። በእኛ ጉልበት እየከበሩና እየተዝናኑ ፣ እኛ የምናቀርባት ትንሽ ጥያቄ ግን ፣ ከመጠን በላይ ታንገፈግፋቸዋለች ። በተጨማሪም — — —"

"ደሞዛችሁን በወቅቱ ይከፍሏችሁ የለም ወይ?" አሉት ድንገት አቋርጠው ።

"እሱማ የት ይቀራል! ግን ምን ዋጋ አለው ፣ የሚከፍሉን በድካማችን መጠን አይደለም ። በዚያ ላይ በፈለጉ ጊዜ ከሥራ ቢያባርሩንና ቢቀጡን ማን ይከለክላቸዋል ። ሕጉ እንደሁ ለይስሙላ ነው ሲሉ ሰምቻለሁ ። ባለሀብት በመሆናቸው ብቻ በጣም ይበድሉናል ።"

"እሱማ አስወጣችሁኝ ብሎ ጠብ የታል? አንድ ሰው ከገዛ ርስቱ ላይ ጭሰኛውን ቢነቅል ፣ ሎሌውን ከገዛ ቤቱ ቢያባርር ማን ይከለክለዋል? በድሎም ከሆነ ወቃሹም ፣ ከሳሹም እግዚአብሔር ብቻ ነው ። ፈረንጁም ቢሆን እጁ ሰቶ አይማታ—አይጋረፍ እንጂ ፣ በገዛ ንብረቱ ያሻውን ቢያሠራና ባያሠራ ማን ይከለክለዋል? ይኸማ አጉል ነገር ነው ። ያጠፋ ሠራተኛ ደሞ ከሥራ ይባረር ቢባል አግባብ ነው ።"

"እኛ ደግሞ የምንለው ፣ የጉልበታችንን ዋጋ ክፈሉን ፣ በሆነ ባልሆነው ከሥራ አታባሩን ነው ። እንዳላችሁና እንዳዘዛችሁማ አላዋጣም ። መብታችን በሕጉ መሠረት ይጠበቅልን ነው ። ለዚያውም ሕጉ የሚያደላው ለነሱ ነው አሉ" አለ ያለ ፍርሃት ።

"እንዲህ ነችና በላይነህ! በዚህ አያያዝማ እነሱም እንዳሉት ዋና ተከራካሪ ሆነሃል ። እኔ ላንተ ይበጅሃል ብዬ ነውዬ አለያ ከሥራ ያስወጡሃል ፣ ዐርፈህ ብትቀመጥ ይሻልሃል ፣ ይኸ አለጉዳይህ አለሁ — አለሁ አያዋጣም ። ከምታስወቅሰኝ ሥራውን ለቀህ ሌላጋ ብትቀጠር ጥሩ ነው" አሉ ቅር በመሰኘት ።

"ግድ የለም ፣ እርስዎን የሚያስነካ ጉዳይ አይደለም ። እነሱም እርስዎ ዘንድ ለምን እንደ መጡ ገብቶኛል ። ለማንኛውም እኔ ጠቃሚዬን አላጣውም ። ከባልንጀሮቼ ጋር እመክርበታለሁ ። ወይ ሕጉ— ወይ የሚለየው ይለየናል ። እነሱ ስንቱን ሰው እየበደሉ ፣ አንዲት ቃል የመለሱላቸው እንደሁ እገር ይያዝልን ይላሉ ።"

"እኔ ከዚህ በላይ ዐላውቅም ፣ በተረፈ አንተ ታውቃለህ ። ትዕግሥትን የመሰለ ነገር የለም ። ይኸው የሕዝቡንም ሁኔታ እያየኸው



ነው ። አሁንማ ሥርዓት እያጣና መንግሥትን እያስቸገረ ነው ። ተማሪዎቹ በማያገባቸው ጉዳይ እየገቡ አገር እናብጥ ይላሉ ። እናንተም ነገር—ነገር ሸቷችኋል ፣ የምር አይምሰልህ! ንጉሥ ቻይና ታጋሽ ነው ። ችሎ ችሎ እጁን ያነሣ ዕለት ግን ፣ ሁሉም እውሃ የገባች ዐይጥ ይሆናል ። እስከዚያው ግን ፣ እግዚአብሔር በፍጡሩ ላይ እንደማይጨክን ሁሉ ፣ ንጉሥም በሕዝቡ ላይ አይጨክንም ። ባጭሩ ልንገርህ ፣ መንግሥት እንኳን የሚደረገውንና የሚታሰበውን ያውቃል ። 'ስትቆርስ ገበታህን ፣ ስትራመድ መንገድህን እይ' የሚሉ ምክር እንዴት ጥሩ ምክር መሰለህ! ከሚያብዱ ጋር ማበድ የለብህም ። ልክህን ብታውቅ ይበጅሃል ። 'እንጣሪያ—ላንጣሪያ ቢደጋገፍ ተያይዞ ዘፍ' ሲባልም አልሰማህ መሰል ። ከልክስክሶች ጋር አትዋል ። እኔ ሁሉንም ነገር ዐውቀዋለሁ ። ምን ስንሠራ እንውል መሰለህ? ተስማምቶና ተግባብቶ መኖር እንጂ ፣ ከባለቤትና ካሳዳሪ ጋር እልህ መያያዝ ተገቢ አይደለም ። የሚጠቅምህን አንተ ታውቃለህ ፣ ማየት ያለብህ ደግሞ የዛሬውን ብቻ ሳይሆን የትላንቱንም ጭምር ነው ።"

በልቡ 'ምን አነታረከኝ' ብሎ ዝም አለ ።

የቀኛዝማችን ሐሳብ እያሰላሰለው በሔደ ቁጥር ምክራቸው ሁሉ አልጥምህ አለው ። ከሲኞር ካርሎ ጋር አንድ ሆኑበት ።

ከብዙ የማኅበር ተጠሪዎች ጋር በመተዋወቁ ፣ አንዳንድ የሠራተኛ ጉዳይ ችግሮችና መነሻቸው እየገባው ሔደ ። ወዳጅና ጠላት ፣ ጭካኔና ርኅራኄ ፣ ምን እንደሆኑ ይገባው ጀመር ። ቀስ በቀስም የራሱን አመለካከትና ግንዛቤ አዳበረ ። ቀኛዝማች ዘንድ በሔደ ቁጥር አስተሳሰባቸው እየተራራቀና እየተፃረረ ፣ ወሬአቸው ሁሉ የገጠር ትዝታ ብቻ ሆነ ።

የነአማረ ክርክር ከዓመት ከመንፈቅ በላይ ሲጓተት ቆይቶ ፣ "ሠራተኞቹ በሥራቸው ላይ አድርሰዋል ስለ ተባለው በደል በማስረጃ የተደገፈ ጥፋት ባለመቅረቡ ፣ ከሥራ የታገዱት ያላንዳች ሕጋዊ መንሥዔ መሆኑ ተረጋግጧል ። ነገር ግን ፣ በማኅበር ምሥረታ ምክንያት እንዲታገዱ ተደርጓል ተብሎ የቀረበው አቤቱታ አንዳችም ማረጋገጫ አልተገኘለትም ። ቦርዱ ከግራ—ቀኝ የቀረበለትን የመከራከሪያ ነጥቦች አንድ ባንድ መርምሯል ። ስለዚህም ክሱ ላስማሚ ክፍል ከቀረበበትና እንዲሁም ይግባኙ ለቦርዱ ጽ/ቤት ከደረሰበት ዕለት አንሥቶ የነበረው ደመወዛቸውና ሌላም ሕጋዊ ጥቅማቸው ሁሉ ተጠብቆ ወደ መደበኛ ሥራቸው እንዲመለሱ ይደረግ" የሚል ውሳኔ ተሰጠ ። አሠሪው በውሳኔው ሲከፋ ፣ አማረ ንጋቱ ፣ ሠዐረ ተስፋ ጋብርና እንዲሁም የማኅበሩ አባላት ገና በተግባር ባልተተረጐመው የወረቀት ላይ ድል ፈነደቁ ።

ሆኖም ፣ አፈጻጸሙ በአዳዲስ ምክንያትና የቢሮ ስልት ተንተተ። ንዋይ ከሕግ በላይ ፣ ፍትሕ ከጥቅም ግርጌ ዋሉ ። የኋላ—ኋላም ፣ "ሁለቱ ሰዎች ወደ ሥራ ገበታቸው ቢመለሱ ፣ ሌሎች ሠራተኞችን በስውር እያሳደሙ ሥራ ስለሚያዳክሙ ፣ ከድርጅቱ ውጪ ቆይተው ደመወዛቸውን ቦርዱ ጽ/ቤት ድረስ እየቀረቡ ይቀበሉ" በሚል የአሠሪ አቤቱታ ፣ የቀድሞው ውሳኔ በሌላ የጎዳ ችሎት ተገዝግዞ ጉዳዩ እንደገና ተዳፍኖ ተድበሰበሰ ። ሠራተኞቹ በደላቸውን ለማሰማት ወደ ልዩ ልዩ ባለሥልጣኖች ቢቀርቡም ፣ ሕሊናቸውን ሸንግሎ ፣ ቅስማቸውን የሚሰብር እንጂ ፣ ተስፋቸውን የሚያለመልም ሹም አጡ ። እየመሸ ሲነጋ ፣ ለማይገኝ ፍትሕ ፍለጋ — — —



# ምዕራፍ ሃምሳ አምስት

ምንዳዬ ፣ ካንድም ሁለት ሦስቴ በመመላለሱ ፣ ከቅዳሜ ገበያተኛ ጋር ወደ ሣር—አምባ ሲሻገር እንደ በፊቱ ብዙ ሰው አጀብ—ከበብ አላደረገውም ነበር ። ልኬለሽ እንደ ምኞቷ ሴት ልጅ ወልዳ ማጥባት ከጀመረች ሦስት ወር አልፏታል ። ዛሬም ደስ አላት ። አመሻሽ ላይ ከቆላ የገባው ቸርነት የባልንጀራውን መምጣት ሰምቶ ከነባለቤቱ ሲሔድ ፣ የነምንዳዬ ጎጆ በሚዋደዱ ሰዎች ሣቅና ፈገግታ ተሞላች ። በተከታታይ ሦስት ቀናት እስከ ውድቅት እያወሩ ናፍቆታቸውን ተወጡ ።

* * *

"ይኸው እስከዛሬ ድረስ ተለያይተን ኖርን ፣ ከእንግዲህ ብቻሽን መቀመጥ የለብሽም ። ከዚህ ቀደም ስንት ዓመት ተንገላታሽ ፣ መምሬ ተክለ ጎርጊስ እንኳ 'ለሁሉም ጊዜ አለው' እሚሏት ጥሩ ፈሊጥ አለቻቸው" አላት ፀሐይ እየሞቁ ሲያወሩ ።

"እረ እኔ አልተንገላታሁም ፣ ምን ጐሎብኝ ምን አጥቼ! ስለኔ አትጨነቅ ።"

"አሁንማ ደህና ራሴን ችያለሁ ፣ ትላንትም ከትላንት ወዲያም አጫውቸሻለሁ ፣ ከእንግዲህ እዚህ አትኖሪም — —"

"ወዴት እንሔዳለን?"

"አዲሳባ!"

"መገን ያንተ ነገር! ቤቱን ለማን ጥዬው?"

"የትኛውን ቤት ልኬ? ቤታችንማ ዞን አምባ ፈርሶ ቀረ! ይህ እኮ ሳባ ዐይኔና ደግበረሊላ አይደለም ። ይኽ የመቆረር አገር ነው ፣ የመቆያ ቤታችን ነው ።"

"እኔ እኮ እምልህ ፣ ፍየሎቹ ፣ አህያውና በሮቹስ?"

• "ግድየለሽም ሁሉም ቀላል ነው ፣ ፍየሎቹን እቤቶችሽ ጋ ዞን አምባ እንልካቸዋለን ፣ በሮቹም ይሸጣሉ ፣ ሌላ ምን አለ ? ይኸው ነው ።"

አላት እየማቀ ፡፡ ተወያይተው እንዳበቁ ፣ ፍየሎቹ ለሷ ቤተሰቦችና ለሟቹ እኅቱ ሚስት ፣ አህያው ለመምሬ ተክለ ጊዮርጊስ እንዲሰጡ ተስማሙ ፡፡

ይህንኑ ጉዳይ ማምሻውን ለቸርነት ነገረው ፡፡ መርዶ የሰማ ያህል ደንግጦ ፣ ክው ብሎ አቀረቀረ ፡፡ ለብዙ ጊዜ ከተለየውና ደረስ መለስ ከሚለው ከምንዳዬ ይልቅ ፣ ከልኬለሽና ከነአሻጋሪ የመለየቱ ነገር መንፈሱን አስጨንቆ ነፍሱን አሽቆጠቆጣት ፡፡ ለጥቃትና ለብቸኝነት የተጋለጠ መሰለው ፡፡ ልቡ አና ሆነች ፡፡ ቀና ብሎ ፊት ለፊቱን በትዝዝ ብሎ አየና ፣

“ባንደዬ አታራቁተኝ! አሻጋሪን እንኳ ተውልኝ?”

“እንዴት አርጌ ልተውልህ? ብተውልህ ደስ ይለኝ ነበር ፡፡ ትምህርት ቤት መግባት ስላለበት ——”

“ቢሆንም ፣ ባይሆንኳ የዘንድሮን — ምን ይጎዳ ልቅር ?” አለና አቀረቀረ ፡፡

ምንዳዬ ፣ ጥያቄውን በልዩ ልዩ መልክ አገላብጦ አየው ፡፡ ባንድ በኩል እጅግ የሚወደውን የበኩር ልጁን ትቶ መሔድ በጣም ሲከብደው ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ልኬለሽ ይህን ጥያቄ ብትቃወም ፣ “አንቺ ምን አገባሽ” ሊላት እንደማይገባ በማሰብ ነፍሱ ተዋከበች ፡፡ ክልኬላም ቸርነትን በጣም እንደሚያስከፋው ታየው ፡፡ በተጨማሪም አሻጋሪ ብቻውን ከናት አባቱ ተለይቶ እንደሚቀር ሲነገረው ፣ አሻፈረኝ ቢል ምን ማድረግ እንደሚቻል በማውጠንጠን መላ ቅጡ ጠፋው ፡፡ መንፈሱ በልጁ ፣ በባለቤቱና በጓደኛው መካከል ቆማ ተንገላታች ፡፡ አውጥቶና አውርዶ ወሰነ ፡፡

የቸርነትን ትከሻ ያዝ አደረገና ፣ “እሺ በል ይቅርልህ —— ሐሳብህ ገብቶኛል ፣ እንዳንለያይ ብለህ ነው ፤ አንለያይም ፡፡ ልጁ ኖረም አልኖረ አንለያይም” አለው ፊቱ በፈገግታ ደምቆ ፡፡ ቸርነትን ደስታ አፈነው ፡፡ የማይለካ የደስታ መጠን ፡፡ በሣቅ ፣ በፈገግታ ፡ በፍንደቃ ፣ በዝምታ ሳይቀር የሚገለጽ ፡፡ ምን ብሎ እንደሚመልስለት ጠፋውና በዝምታ ትኩር ብሎ አየው ፡፡ ልቦናቸው ተግባብቷል ፡፡

ምንዳዬ ይህንኑ ለልኬለሽ ገለጸላት ፡፡ ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኖ አገኘው ፡፡ “አይሆንሚ እሚሆን ቢሆንስ እስከ ዘለቄታውም ቢሆን ቅር አይለኝ” አለችው ፡፡ ለልጁም የመደሊያና አፉን የማስያዣ ልብስ ተገዛለትና ፣ “ሚያዝያና ግንቦትን እንዲሁም ክረምትን ከቸርነት ጋር ቆይቶ መስከረም ሲጠባ እሱም ወደ አዲስ አበባ እንደሚሔድ በለዘብታ ተነገረው ፡፡ ቢባባም ‘እሺ’ አለ ፡፡ ደስ አላቸው ፡፡



ምንዳዬና ቸርነት ካብ ሥላሴ መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ቤት ደርሰው ሲመለሱ ፣ የበሬዎቹ ጉዳይ ተነሣና ፣ “እነዚህን በሬዎች ልሸጣቸው ነው ፡፡ ምን ያህል ያወጣሉ?” አለ ምንዳዬ ፡፡

“የነዚህ ዓይነቱ ጥሩ የርሻ በሬዎች ደህና ዋጋ ያወጣሉ” አለ ቸርነት ፡፡ በዋጋው ግምት ተግባቡ ፡፡

በመጨረሻም ፣ ቸርነት የበሬዎቹን ዋጋ እጁ ሲሞላለት ቀስ በቀስ እንዲከፍለው ተስማሙ ፡፡

“የጠበንጃውስ?” አለ ቸርነት ድንገት ትዝ ብሎት ፡፡

“ጠበንጃውማ ውዴታዬ ነው ፤ በየቀኑ አብረን እንድንውል ፣ እንዳንለያይ ብዬ ሰጥቸሃለሁ” አለው ፡፡

ምንዳዬ ገና ከአዲስ አበባ ሲነሣ ስለ ጎጆው ጉዳይ ለቀኛዝማች ነግሯቸው ስለነበር ፣ ቸርነት እርሱ ቤት ገብቶ እንዲኖር በመፍቀዳቸው ቤቱን ከነሙሉ ቅራቅንቦው ተወለት ፡፡

ሁለቱ ቤተሰቦች በከፊል የሚለያዩባት ዕለት ደረሰች ፡፡ ማጀቴ ወርደው ዓለማቸውን አዩ ፡፡ አረጋሽ የመረጠችው ሻሽና የሱዳን ሽቶ ተገዛላት ፡፡ በማግሥቱ ከሰዓት በኋላ ልኬለሽ ከነልጆቿ ጐላ ሠፈር እንደ ደረሰችም ፣ የምንዳዬ ጐረቤቶች ሞቅ ባለ መስተንግዶ ተቀበሏት፡፡

# ምዕራፍ ሃምሳ ስድስት

ቀኛዝማች ፣ በገንዘብ ኃይልና በሰው ድጋፍ ፣ ከባለሥልጣን ወደ ባለሥልጣንና ከመኳንንት ወደ መኳንንት መሸጋገርንና ያጉርሰኝ ላጉርስህን ዘዴ አሳምረው ካወቁበት ውለው አድረዋል ። ከርስቱም ከቤቱም ከጨባበጡ በኋላ ፣ በተለይ ሹመት የማግኘቱ ጉጉት እንቅልፍ ስለ ነሣቸው ፣ ጊዜና ገንዘባቸውን ወደዚያው አዞሩት ። ምኞታቸው አልመከነም ። የአንዱን ዕውቅ ባለሥልጣን ጠንካራ ክንድ ጨበጡ ። ከትርምሱ መኻል ሽቅብ ስቦ አወጣቸው ። መሰላሉና ክንዱ ቀላል አልነበረም ። ከዙፋኑ አቅራቢያ ቆመው ፣ የንጉሡን ዘርፍ እንደነኩ ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ በንጉሠ—ነገሥቱ መልካም ፈቃድና ትዕዛዝ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል እንዲሆኑ ሲሾሙ ፣ የደስደሱ ግብዣ ያዲስ አበባ ወዳጆቻቸውን አንበሸበሸ ፣ ማጀቱና ሣር አምባ ላይ ዓለም አለፈች ።

ጊዜ እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰ — — ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደረደሩ — — —

ተማሪዎች ፣ በየጊዜው በስድስትና ባራት ኪሎ አካባቢ በሚያደርጉት ሰልፍ ፣ እንዲሁም አቤቱታ ይሁን ትዕዛዝ ያለየለት የጽሑፍ ሰሌዳ ተሸክመው ፣ የሚያሰሙት ንግግርና የሚወረውሩት ድንጋይ ቀኛዝማችን እጅግ አበሳጫቸው ። አንዳንድ ቀን ሁኔታውን ሲያናንቁ፣

"እሄሄ! አሁን ይኸ ሁሉ እምቡር—እምቡር የት ለመድረስ ይሆን? ወጉ እንዳይቀር ነው ። ሲባል ተሰምቷል መሰል" ይሉና ፣ የተናደዱ ዕለት ደግሞ ፣

"ኧረ ወዲያልኝ ! ንጉሡም ችላ—ችላውን ያበዙታል ፣ ያዳሜን ስድ አደግ ወዲያ ቅርምርም ማድረጋቸውን ጥለው ፣ ጥጃ ይመስል ባርጩሜ ሲያስገርፉ ይውላሉ" በማለት ያማርራሉ ። ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ለምን ከረር ያለ ርምጃ እንደማይወስዱም ይገረማሉ ። ራሳቸው የባለሥልጣንነት ስሜት ሲሰማቸው ደግሞ ለሰሚ የሚዘገንን የቅጣት ዓይነት ያስባሉ ። ነገሩ ረገብ ሲል ደግሞ ፣ ሁኔታውን እንደ ጨረባ ሠርግና እንደ ማቲ ሁካታ ይቆጥሩታል ።

በተለያዩ ከተሞች የተደረጉ የተቃውሞ ዐመፆችን ለማዳፈን የተወሰዱ ርምጃዎችን ሲሰሙ ደግሞ ፣ "እንዲህ ነውዴ ፣ አሁን ጥሩ

አደረጉ ፣ ጥጋብ በዛ! እነሱን ብቻ አልነበር ፣ በርቱ በርቱ እያሉ የሚቆሰቁሷቸውንም ሰብስቦ ወህኒ መክተት ነበር ። ያላሳብ እየበሉ ይማራሉ ምን ያርጉ ?” ይላሉ ።

አንዳንድ ሰዎች ስለ ተማሪዎችና ሠራተኞች ፣ እንዲሁም በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች ስለ ተደረጉ የገበሬዎች እንቅስቃሴ አሥጊነት ሲወያዩ ፣ ቀኛዝማች ጉዳዩንና ሰዎቹን በመናቅ ሁኔታውን ያንኳስሱታል ። አልፈው ተርፈውም ሰዎቹን እንደፈሪ ይቆጥሯቸዋል ።

* * *

ምንዳዬ ፣ የማኅበሩ ምክትል ተጠሪ ሆኖ ከተመረጠ ጀምሮ የሚደርስበት ቅጣት እየበዛ በመሔዱ ፣ ሕሊናው ለዓመፅ ፣ እጁ ለስንዘራ ተዘጋጀ ። ያቺ በየጊዜው የምትቋረጠው የማታ ትምህርቱም ከ፫ኛ ክፍል እልፍ ባለማለቷ ከማመልከቻ ጸፉልኝ አላዳነችውም ። ሆኖም በብዙ የሠራተኛ ጉዳይ ስብሰባዎች በመካፈሉና ልምድ ካላቸው የማኅበር መሪዎችም ጋር በመተዋወቁ ፣ የመከራከር ችሎታው ዳበረ ። ዋናው የማኅበር ተጠሪ በማይኖርበት ወቅት ፣ ማኅበሩን ወክሎ ለክርክር ሲሔድ ፣ እንዴት ብሎ እንደሚከራከርና ምን ቢሉት ምን መልስ እንደሚሰጥ በቅድሚያ ይማከርና ፣ ከዋናው ጽ/ቤት የተጻፈውን አቤቱታ ወይም መልስ ይዞ ይሔዳል ።

በክርክሩ ወቅት ፣ የጉዳዩ አዝማሚያ አላምርህ ሲለው ደሙ ይፈላና ፣ “እንዲህ ተሁኖስ አይዘለቅም ። ይኸማ ሲነፍሩ መኖር ነው ። ለዚህ መዳኒቱ ጥይት ነበር ፣ ወይ ነዶ! ምን ያረጋል” ይላል ብቻውን ።

ያም ሆነ ይህ ፣ ንዴቱን የሚያበርድና ብስጭቱን የሚቀንስለት ነገር አልተገኘም ። እንዲያውም ከሚያውቀው ግፍ የከፋና ካየው መከራ የባሰ የደረሰባቸው ሠራተኞች እንዳሉ ተገነዘበ ። በሌላ አካባቢ የሚደረገው ድርጊት ሲገርመውና ሲቆጨው ፣ እዚያው አጠገቡ ያለው ሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ ፣ የተማመነውን ተማምኖ በተጨማሪ ሦስት ሠራተኞችን ከሥራ አባረረ ።

ምንዳዬ በንዴት ቢል አለ ። ዞሮ—ዞሮ ግን ፣ ያው አቤቱታና ክስ በመሆኑ ፣ እንደ ተለመደው ክሱን መሠረተ ። ቀጠሮ በቀጠሮ ላይ ፣ ምስክር በማስረጃ ላይ እየተደራረበ ቀኑ ተንተተ ። በግሉ ሲያሰላስልም ሆነ ከቢጤዎቹ ጋር ሲያወራ ፣ የወሬው መወጠኛና መቋጠሪያ ሠራተኞች ማስማሚያ ክፍል ፣ ቀነ ቀጠሮና ሰዓት ፣ ያለ በቂ ምክንያትና ማስረጃ ፣ የጋራ ስምምነት ውል ፣ ሕግ ፣ አድልዎ ፣ ጉቦ ፣ ነገረ ፈጅ ፣—— የሚሉት ጉዳዮች ሆኑ ። ወጣም ወረደ ,



ሦስቱ ሠራተኞች በጥፋተኝነት ከሥራ መባረራቸውን የሚገልጽ የጽሑፍ ውሳኔ የደረሰው ዕለት ሁለመናው ነደደ ። የውሳኔውን ወረቀት ይዞ በቀጥታ ወደ ቤቱ በመሔድ ጋደም አለ ። ቢያስብ ቢያሰላስል ምንም አልታየው ። ሐሳቡ ከንፎ—ከንፎ በበቀል ላይ ይደመደማል ። ግን በምኑ ! ካርሎንና የካርሎን ተባባሪዎች ፣ በገንዘብና በስጦታ የደለላቸውን ሰዎች ሁሉ በጥርሱ አይነክሳቸው ፣ በጥላቻ ብቻ አይገላቸው ። በሐሳቡ ብዙ ነገር ታየው ።

ሐሳቡ የትዝታውን ጎዳይ ይዞ ሲከንፍ ፣ አገሩ ዞን አምባ ገባ ። አያሌ ዓመታት ወደኋላ ተመልሶ በርስት ግጭት ምክንያት የደረሰበት ነገር ሁሉ በዐይን — ሕሊና ታየው ። አንድ የነደደው ተቆርቋሪ ዘመዱ ፣ ድግስ ላይ ፣

“እረሱት ያን መሬት እንደቦይ እንደቦይ ፣

አባትዬው ቢሞት ልጅየው የለም ወይ?” ብሎ በነገር የወጋው ትውስ አለው ። ምንዳዬን አባባሉ ቢገባውም ፣ ለጊዜው ጥርሱን ነክሶ ዝም አለ ።

“ይወለድና ጫማ ሰፋፊ

ያባቱን መሬት ወሰን አስገፊ” ይለዋል ሰውየው መልሶ ።

እንደገና ዝም ለማለት ግን አልቻለም ። ከሰውዬው ጋር መጣላት አህያውን ፈርቶ ዳውላውን ይሆንበትና ፣

እየጤስ ባፉ ይሚሻል እንስራ ፣
መቼ ይጠፋኛል የምሠራው ሥራ ፣

ተው በለው ምከረው መካሪም የለው ወይ ፣
እንግዲህ ዝም በለው ተወው ይፈንግጠው ፣

አጥንቱ ይገኛል ጀቢራ ሲግጠው ፣
እምቢ ቃለ ፣ ጠቡን ተወደደው ፣

በዲሞፍተር ጥይት ወገቡን ጉረደው” ብሎ ይመልሳል ።

አንድ ራቅ ያለ ዝምድና የነበረው ሰው ፣ የምንዳዬን አባት መሬት ፣ “አያቴ ገዝቶት ስለነበር ፣ ወይ ገንዘቡን መልሱልኝ አለበለዚያም መሬቱን ልቀቁ ። ቀድሞውኑም የያዛችሁት በጉልበት ነው” በማለት ይከሳቸዋል ። የምንዳዬ አባትም ፣ መሬቱ የከሳሽ አያት ያለመሆኑን ማስረጃና ነቃሽ አቅርበው ይረታሉ ። ከሳሽ ማመን ይሳነዋል ። የምንዳዬ አባት ጤና እያጡና አቅም እያነሳቸው ሲሔድ ፣ “በጉልበት የተነጠቀ ርስት የሚመለሰው በጉልበት ነው” ይልና ፣ እሱ ራሱ

በገመተው ክልሎ ይነጥቃቸዋል ። በጉልበት የማይቋቋሙት ፣ በሕግ የማ
ያቸንፉት ሲሆንባቸው ጊዜ ፣ ሽማግሌ ይልኩበታል ። አልተቀመሰም ።
እንደ ጨሱና እንዳረሩ ይሞታሉ ።

ምንዳዬ ፣ ከልጅነቱ ጀምሮ አካለ መጠን እስከ ደረሰ ድረስ ይህን
ታሪክ ከሥር—ከመሠረቱ ልቅም አድርጎ ያውቀዋል ። መሬቱን አሻ
ግሮ ባየ ቁጥር ብድሩን ለመመለስ ይዳዳዋል ። አልቀረም ፣ ለወጉ ያህል
ያገር ሽማግሌ ልኮ ያስጠይቀዋል ። ሽማግሌዎቹን ፣ "አፋችሁን አታ
ጥፉ" ብሎ ይመልስና ፣ እሱንም በሸውከኛ ያስጠነቅቀዋል ። ምንዳዬ
ግን ፣ እስቲ ላስጨርሰው በሚል ሐሳብ ፣ ሰው አማክሮና ምስክር ቆጥሮ
ይከስሰዋል ። ሕጉ ተዛብቶ ፣ ሥነ ሥርዐቱ ተጣቶ ፣ ሰውዬው ለመንግ
ሥት የገበረበት ዘመን ተሰልቶ ፣ በተጨማሪም ገንዘብና ወገን ተረባ
ርበውበት ምንዳዬ ተቀጥቶ ተረታ ። ከዚያ በኋላ እንቅልፍ ያጣል ።
ነገሩን ከሥር ከመሠረቱ ሲያጣራ ፣ የምንዳዬ አያት አቶ ባሕሩ ቦለድ
ከነበረው መሬታቸው ላይ ሦስት ጥማድ የሚያውል ለም መሬት በች
ግር ምክንያት ለ፫ ዓመት ያስይዙና ብድር ይገባሉ ። ዕዳቸውን በጊዜው
ከከፈሉ መሬታቸውን ሊያገኙ ፣ ጊዜው ካለፈ አጠፌታ ሊከፍሉ ይስማ
ማሉ ። ጊዜው ያልፍባቸዋል ። አምስተኛው ዓመት ላይ አጠፌታ ከፍ
ለው መሬታቸውን ያስለቅቃሉ ። ሰውዬው ግን ፣ ያለበትን ዕዳ ለወደ
ፊት ሊከፍለኝ ሥግነቱን አይቼ መለስኩለት እያለ ያስወራል ። ነገሩ
ካባት ለልጅ ፣ ከልጅ ለልጅ—ልጅ ይተላለፋል ። ምንዳዬ ይኸን ሁሉ
በሚገባ ያውቃልና ፣ የመጣው ይምጣ ብሎ ቆርጦ ይነሣል ። ከወዲያ
ወዲህ ብሎ መሣሪያ ገዛ ። አልቸኮለም ። ረጋ ብሎ የቀድሞ ዳር ድን
በሩን ካጣራ በኋላ፣ ከሰው መሬት አንዲት ጋት ሳይነካ ፣ ያባቴ ነው
የሚለውን መሬት በጠራራ ፀሐይ አረሰው ። ጠብ አበቀለ ። ዱላ
ተማዞና ዳኛ ፊት ቀርበ ዳግመኛ ተቀጣ ።

ምንዳዬ ፣ በዘራው ሰብል ላይ እሳት ለቀቁበት ። አንድ አለ ።
የእርሻ ወራት ጠብቀው ዐይኑ እያዬ አረሱበት ። ሁለት አለ ። ያረሱ
ትን መሬት መልሶ አረሰና ዘራበት ። ቡቃያውን ከብት ለቀቁበት ።
ሦስት አለ ። አጠናቀቀ ። ወሰነ ። ችላ ያለና የተረታ መስሎ ዝም አለና
አንድ ዓመት አሳለፈ ። ወኔ ሲያደራጅና ሐሞቱን ሲጻጥር ቆይቶ ፣
የበቀሉን በትር አነሣ ። አባቱን እንገላቶ እሱንም ያሰቃየውን ሰውዬ
መከታተል ጀመረ ። ሲወጣ መውጫውን ፣ ሲመለስ መግቢያውን አጠና።
ቀኑ ተቃረበ ።

አንድ ቀን ያኛው ባዶ እጁን ፣ ምንዳዬ ከነጠበንጃው ይገናኛሉ ።
ምንዳዬ ባዶ እጁን የሆነ ሰው ላለመግደል ፣ ያኛው ምን አባቱ እንዳያ
ረገኝ በሚል ንቀት ይተላለፋሉ ። ያ ቀን ሌላ ቀን ተካ ። ሰውዬው



በነምንዳዬ መሬት ላይ በሮቹን ጠምዶ ሲያርስ ፣ ምንዳዬ ከተፍ
ይላል ። ጠበንጃውን ይዞ ወደሱ ሲመጣ በመመልከቱ ፣ ያመጣውን
ሁኔታ ገምቶ ጠበንጃውን ለማንሣት ወደ ድንበሩ ይሮጣል ። ምንዳዬ
ይገሠግሣል ። ጠበንጃውን አንሥቶ መለስ ሲል ምንዳዬ አጠገቡ ደር
ሷል ። ሰውዬው ፋታ ሳይሰጥ ይተኩሳል ። ቀድሞ በመደንገጡ ይስተ
ዋል ።

ምንዳዬ ፣ አከታትሎ በሁለት ጥይት ደረቱ ላይ ይመታዋል ።
ባካባቢው የነበሩ ገበሬዎችና እረኞች እያዩ የሰውዬውን መሣሪያ
ገፍፎ እየፎከረ ዱር ይገባል ። የተከተለም ፣ ያስጣለም አልነበረም ።
ከያለበት ኡኡታው ይቀልጣል ። ምንዳዬ ጫካ—ጫካውንና ሸለቆ—
ሸለቆውን እየመረጠ ዞን አምባን አሽቆልቁሎ ከሚያይበት ጉብታ
ላይ ሲወጣ ፣ መንደሩ ተሸብሯል ። የሟቹ ሬሣ በቃሬዛ ወደ ቤቱ ሲገባ ፣
ዘመድ አዝማድ ሲላቀስ ፣ ሰው ከወዲያ ወዲህ ሲመላለስ ወለል ብሎ
ይታየዋል ። መሸ ። የልቡ ቢደርስም ንዴቱ አልበረደም ። በውስጡ
አንድ ጥርጣሬና ሥጋት ይላወሳል ። ከቶ ምንም ቢሆን ፣ መሆኑ ስለ
ማይቀር ፣ ንዴትና ቁጭት አያቃልሉትም ። ስለዚህም ራሱን ነቅንቆ
ከመተከዝ ሌላ የሚያደርገው ነገር አልነበረም ። የፈራው አልቀረም ።
የሟች ወገኖች የምንዳዬን አጐት ፣ ያባቱን ታናሽ ወንድም ገድለው
ቤታቸውን ካቃጠሉ በኋላ ፣ የሱንም ጎጆ አጋዩዋት ።

ምንዳዬ የትም አድሮ የትም ከዋለ በኋላ ፣ በሦስተኛው ቀን
መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ቤት ካብ ሥላሴ ገብቶ ፣ የሆነውን ሁሉ ነገ
ራቸው ። ቢድብቅ ወጣ ገባ ሲል ሰነበተና በመጨረሻም ነገሩ በእርቅ
እስኪያልቅ ድረስ ለጊዜው መኮይ እሚባል አገር ከሽፍቶች ጋር
እንዲቀላቀል አማከሩት ። አላቅማማም ። ከሟቹ የገፈፈውን ጠበንጃ
አስቀርተው ፣ እሱን በምስጢር ከሰው ጋር ወደ ሽፍቶቹ ሠፈር
ሰደዱት ።

ነገሩ እስኪበርድና ሐዘኑ እስኪረሳሳ እየተባለ አንድ ዐመት አለፈ።
ከዚያ በኋላ መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ደህና ደህና አስታራቂ ሽማግሌ
ማፈላለግ ጀመሩ ። ቀሳውስትና መነኮሳት ካካባቢው አብያተ ክርስቲ
ያናት ፣ ሌሎች ሽማግሌዎች ከዚያው ከዞን አምባና ፣ ቀኛዝማች ስላል
ተመቻቸው በሳቸው ምትክ የላኳቸውን የወረዳውን ጸሐፊና ዳኛውን
ይዘው ሽምግልናቸውን ተያያዙት ። የገዳይ ወገን ሽማግሌዎች መስቀ
ላቸውን አስቀድመው ፣ ቄስ መነኩሴአቸውን አስከትለው ፣ የወረዳውን
ጸሐፊና ዳኛ ተግነው ፣ የምንዳዬን ሁለት እህቶች ፣ ያባቱን ታናሽ እህት
አክስቱን ፣ የልኬለሽን አባት (አማቱን) እንዲሁም በሐዘን የተቆራ
መዱ እናቱን ይዘው ሽምግልና ሲጀምሩ ፣ በሟች በኩል ፣ ሚስቱና

ልጆቹ ፣ እህትና ወንድሞቹ ፣ ዘመድ አዝማድ በተገኙበት የመታረቂያ ሐሳቡና ልመና እጅግ በሚያስፈራ ሁኔታ ረጋና ቀዝቀዝ ባለ ስሜት ፣ ቃለ እግዚአብሔር እየተጠቀሰ ፣ ተረትና ምሳሌ እየተነገረ ፣ ልማድና ባህል እየተዘከረ ፣ ሰይጣን እየተወገዘና እየተረገመ ፣ ቢርቅም የዘመዳሞች መገዳደል ዞሮ—ዞሮ የሁሉም ጉዳትና ሐዘን መሆኑ በመራር ቃላት እየተነገረ ፣ የመጀመሪያው ቀን ሽምግልና ተከናወነ ። በባህላዊ ወጉና በሀገር ልማዱ ፣ በተላኩት ሽማግሌዎች ልመናና ምክር ፣ ተማፅኖ ፣ የቅዱስ መጻሕፍት ጥቅስ ፣ ባካባቢው ባላቸው ክብርና ተሰሚነት የተነካ የሚች ወገኖች የመታረቅ አዝማሚያ አሳዩ ።

በዳግመኛው ቀን ቀጠሮ ገዳይ በሽማግሌዎቹ ታጅቦና አንገቱን ሰብሮ ሽምግልናው ቦታ ተገኘ ። ሽማግሌዎቹ ተራ በተራ ረዘም ያለ የማግባቢያና የማስታረቂያ ፣ ቂምን የመፋቂያና እርቅን የማጠናከሪያ ንግግሮች አደረጉ ። የሚች ወገኖች እያንገራገሩቸውና ጭስስ ብለው የመረረ ንግግር አደረጉ ። የገዳይ ወገኖች ላልተውና ረግበው ፣ አጥፍተናል ፣ በድለናል ብለው ቀረቡ ። የምንዳዬ አጐትም እንደ ማካካሻ ተቆጥረው ፣ በሞታቸው የሽምግልናውን ግብግብ አቃለሉ ። እሺታው ሲሟላ የሽማግሌዎቹ ፊት በደስታ ፈካ ።

ከዚያ በኋላ ፣ እርቁን በስምምነት ማገዳደብ ሲሆን ፣ ለደም ዋጋ የሚከፈለውን ወጀ ፣ ምንዳዬ አገሩን ለቆ እንዲሔድና የመኖሪያ ክልል እንዲከለልለት (አገር እንዲቆረርለት) የሚለው ጉዳይ ሲነሣ ፣ ዱላ ቀረሽ ክርክርና ንትርክ ተካሔደ ። የሚች ወገኖች ፣ የሚች ጠበንጃ እንዲመለስላቸው ፣ ወጀ አንድ ሺ ብር እንዲከፈላቸው ፣ ለገዳይ ራቅ ያለ አገር እንዲቆረርለት አጥብቀው ጠየቁ ። የገዳይ ወገኖች የሚቹን ጠበንጃ ለመመለስ ሲስማሙ ፣ የደም ማድረቂያው ክፍያ ግን ፣ እንደበዛባቸውና ፣ ቂሙን ለመፋቅና ጥላቻውን ለማስቀረትም ለገዳይ የሚቆረርለት አገር በጣም እንዳይርቅ ተማፀኑ ።

ሽማግሌዎቹ አውጥተውና አውርደው ፣ ሁለቱንም ወገኖች በየተራ እያገለሉ መክረውና ወቅሰው ፣ ሲያስፈልግም ገሥፀው ሲያስማሙ ፣ የሚቹን ጠበንጃ ለማስመለስ ፣ ያጋደላቸው መሬት የመያዣ ገንዘብ ተጣርቶ የሚች ወገኖች እንዲወስዱና ወጀም አምስት መቶ ብር እንዲቀበሉ ፣ ምንዳዬም ከጃራ ወዲያ ማዶ ወደ ጎምዛ ውስጥ እንዲኖርና ጃራን እንዳይሻገር አገር በመቆረር የማስማሚያ ሐሳብ አቀረቡ ።

የሚች ወገኖች ፣ ሌላ ሌላውን ሲቀበሉ ፣ የተቆረረለትን አገር ክፉኛ ተቃወሙ ። በመምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ጥያቄ በቀኛዝማች በላይነህ አለመመቸት ምክንያት ከማጀቴ የሔዱት የወረዳው ጸሐፊና ዳኛ ጣልቃ እየገቡ ሕግና ሥነ ሥርዓት እየጠቀሱ ፣ የመሬቱን ክርክር እያነሡ ፣



በመጀመሪያ የተሰጠውን ውሳኔ እያስታወሱና "ምንዳዬ አልሞት ባይ ተጋዳይ ነው" በማለት እያሳበቡ በሚች ወገኖች ላይ ስውር የሥልጣን ጫናና ፣ "ከዚህ ወዲያ ምን ይሁን ማለታችሁ ነው" በሚል ስሜት በእርቅ ስም ገትረው ስለያዙ ፣ የሚች ወገኖች የቄስና መነኩሴዎቹና ፣ ያገር ሽማግሌዎቹ ቆሞ ልመና ስለ ከበዳቸው ፣ "እስከ ማጀቴማ ከመጣ ፣ ዞን አምባ ለመግባት ምን ቀረው ፣ ጃራን አልተሻገረምና ነው?" ቢሉም እርቁን ተቀበሉት ። የሚችና የገዳይ ወገኖች ተራ በተራ ፣ ሽማግሌዎቹም ጭምር ተሳሳሙ ። ምንዳዬም የሽማግሌዎቹን ጉልበትና ጫማ ስሞ ፣ ተሳመ ።

ከቀሳውስቱ አንዱ የብረት መስቀላቸውንና የወንጌል መጽሐፍ አውጥተው የሚቹን ልጅና የምንዳዬን እጅ መስቀሉ ላይ ካሳረፉ በኋላ ፣ "ይህን የእርቅ ገደብ አፍርሼ ብገኝ ፣

እንደ መስቀሉ ይበሳሳኝ
እንደ ወንጌሉ ይደምስሰኝ ፣
በምድር ዘርቼ አያስቅመኝ ፣
ወልጄ አያስመኝ ፣
በሰማይም ርስተ መንግሥተ ሰማያትን ይንቀለኝ" በማስኘት ሁለቱንም በየተራ አስማሏቸው ።

ከዚያ በኋላ ፣ በምንዳዬ በኩል የቀረበው የበግ ሙክት ታርዶ ፣ በትልቅ ሸክና ተሞልቶ የቀረበው ጠላ ተባርኮ ፣ ምንዳዬና የሚች የመጀመሪያ ልጅ ከሽማግሌዎቹ ፊት ቆመው ፣ ምንዳዬ ጠላውን ፉት ብሎ ፣ ለሚች ልጅ ሰጠውና ያኛውም ፉት ብሎ መለሰለት ። ተጎራረሱ ። የቀረበውንም የጥሬ ሥጋ ሙዳ ለሁለት ይዘው ከቆረጡ በኋላ ምንዳዬ በቅድሚያ ፣ የሚች ልጅም ቀጥሎ ተጎራረሱና ተሳሳሙ ። ሲበሉና ሲጠጡ ውለው መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ፣ የወረዳው ጸሐፊና ዳኛው የማታ ማታ ወደ ማጀቴ ሲያዘግሙ ፣ ምንዳዬ ለመጨረሻ ጊዜ የትውልድ መንደሩን ዞን አምባን ተሰናብቶ ተሰደደ ። ልኬለሽ ልጅዋን አዝላ እያለቀሰች ፣ እናቱ ከኋላ ኋላው እያነቡ እስከ ወይራ ውሃ ሸኝተውት ተመለሱ ።

*   *   *

ከዚያ የረጂም ጊዜ ትዝታው ብንን ሲል ፣ ከባድ ሥራ ሲሠራ እንደቆየ ሰው ድክም ቢለውም ፣ ስንቱዬ አገር ማስቆረር አለ ፣ እነዚህ ደግሞ ባንድና ሁለት ጥይት እሚፈቱም አይደሉ ፣ እንደ ሐረግ የተያያዙ ናቸው ። ሁሉንም ወዲያ በጣጥሶ አንድ መላ መምታት ነው ። አለያማ ሲነፍሩና ሲናፈሩ መኖር ነው ። ከነዚህ ጋር እርቅ አይመልሰንም ሌላ ብልሃት ይኖረዋሊ" ብሎ እነ ሠዐረን ፍለጋ ወጥቶ ሔደ።

# ምዕራፍ ሃምሳ ሰባት

ልኬለሽ ፡ የጐላ ሚካኤልን ሠፈር ኑሮ ተላመደችው ። የጐረቤቶቿ ቤት ከእርሷ የገጠር ጎጆ የሚለየው ፡ በቆርቆሮ ክዳኑና በአሠራር ቅርፁ ብቻ ሳይሆን ፡ በቤት ዕቃዎች ዐይነትና ብዛትም ስለነበር ፡ የምታየው ነገር ሁሉ ሲገርማት ሰንብቷል ። ዐይኗ አንድ ነገር ላይ ካረፈ ቶሎ አይነቀልም ። በልቧ ፡ "ይኸ ደሞ ምናቸው ይሆን ጌታዬ ?" ከማለት በቀር አፍ አውጥታ አትጠይቅም ። ያየችውን ነገር ለምንዳዬ ትነግረዋለች ። የራሱ የቀድሞ ሁኔታ ትዝ ስለሚለው ረጋ ብሎ ያብራራላታል ።

ቀስ በቀስ ጐረቤቶቿ ቤት ያየችው የቤት ዕቃ እሷም ቤት ገባ ። በመጀመሪያው ሰሞን እጅግ አውኳት የሰነበተው ግን ፡ ከየቤቱ የሚረጨው የዕቃና የልብስ እጥብጣቢ ፣ የሽንት ቤት ግንፋይና የሞቱ የቤት እንስሳት ግማት ነበር ። እንኳን ግማት መከራ ይለመዳልና ፣ ለመደችው ። ወር—በወር ላይ ሲተካ ፡ ዐይኗን ገለጠች ። ጊዜ እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰ — — — ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደረደሩ ————

*     *     *

እዚያ ላይ — — — ጠግበው ለወዙና ሞልቶ ለተረፋቸው ፣ እጃቸው ይዘግነው ፡ ገላቸው መርጦ ይለብሰው ላላጣ ፡ ለባለ ብዙ መብት ሰዎች ፣ መስከረም የጠባው ብርሃን—ተስፋውን አፍክቶና በረከት—ሲሳዩን አንዠርጎ በደስታና በፈገግታ ነበር ።

እዚያ ታች — — — ግፍና በደል ፡ ረኃብና ስደት ላሰቃያቸውሞት እያንዣበበ ጻዕረ—ሞት ለገዘገዛቸው ፣ ቤት ንብረታቸው ፈርሶ ፣ አካልና ሕሊናቸው ታርዞ ፣ የሀልውና ፀሐይ ለጠለቀችባቸው ፣ መስከረም የጠባው ፣ የመከራ አክናፉን ዘርግቶና የስቃይ ጥርሱን አግጦ ነበር ።

እናም — አቤቱታ ! እምቢታ — ግጆታ — መብት ዱላ— ጥይት—ደም—ሞት — ዐመፅና አድማ ቀጠለ ። የከተማው ሠራተኛና ሽቅሎ አዳሪ ፣ ከልመናና ከልምምጥ ወደ ይገባኛልና እምቢታ ፣ የገጠሩ

ብሶተኛና ጉስቁል ገበሬ ፣ ከጉብደዳ ወደ ግድያና አሻፈረኝ ፣ ከምን ይሻለኛል ወደ ምናባቱንስና ይለይልኝ ተሸጋገረ ። ወራት ዐለፉ ።

ነገሩ እንደ ተጎለጎለ ልቃቂት እየተወሳሰበ ፣ እንደ ጫካ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ ቀጠለ ። የካቲት ከመጠናቀቁ በፊት ግብግቡ ያረገዘው እሳት—ገሞራ ፈንድቶ ረመጡ ሲረጭ አገር ምድሩ ተቀጣጥሎ ተናወጠ ።

ምንዳዬ ፣ ከፊት ለፊቱ ሥጋት ፣ ከበስተኋላው ጥርጣሬ አልነበረበትም ። ቀኛዝማች በዐይነ—ሕሊና ሲታዩት ፣ ከነማን ጋር እንደሚያብሩ ያውቃል ። አስተሳሰብና ዓላማቸውን ከፋኛ ጠልቶ ቢጸየፈውም፣ ጭንቀታቸውን ብቻ በመገንዘብ ያዝንላቸዋል ። የሚያምኑትና የሚሔዱበት ሲያጡ ይታየዋል ። ግትር ጠባያቸው ትዝ ሲለው ደግሞ ፣ ከሕዝቡ ጋር ከመሻሻል ይልቅ ተያይዘው መቀመቅ ቢወርዱና የጠፋው ቢጠፋ እንደሚመርጡ ያውቃል ። ይህን ሲያስብ ደግሞ ውለታቸው በንኖ ጠላት ይሆኑበታል ።

ጊዜ እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰ —— ማዕበሉ እየገሠገሠ —— ቀኛዝማች የናቁት ዐመፅ እየገፋና ያላሰቡት ነገር እየደረሰ በመሔዱ፣ እንደበታቸው መፍራት ፣ ልቦናቸው መጠራጠር ጀመረ ። ከጓደኞቻቸው ጋር ሲያወሩም ከፊሉ ፣ "ከእንግዲህ ወዲያ ምን መላ አለው ! ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ" ሲል ፣ አንዳንዱ ደግሞ ፣ "ለጊዜው ነው እንጂ አንዳችም የሚያሠጋ ነገር የለም" በማለት ገደሉን ንዶና ጉራንጉሩን ደልድሎ ሲያወራላቸው የልዩ ልዩ ሐሳብ ግብስብስናላቸውን ያዞረዋል ። የሚያዩትም ሆነ የሚሰሙት አስጠላቸው ። ሁሉም የትንቅንቁ አካል በመሆኑ ገላጋይም ፣ ሸምጋይም የሚሆን አልተገኘም ። ከምንጊዜው መሸና ነጋ ሲሉ የኖሩት ሰውዬ ፣ ቀን እንደ አውሬ ታፍኖ መዋሉ ሌሊት በቅዠት ሲጨነቁ ማደሩ ሰላም ስለ ነሣቸው ፣ የጊዜ ባሕሪ የተዛባ እስኪመስላቸው ድረስ መንፈሳቸው ተሸበረ ። ወሬ ለመቃረም ወጣ ካሉም ባንዳች ፍሬ ቢስ ተስፋ ፈንድቀው ወይም በአስደንጋጭ ዜና በርግገው ይመለሳሉ ። የደነገጡ ዕለት የትካዜ ማቃቸውን ይለብሱና እንደማይነቃነቅ ዕቃ ይወዘፋሉ ። በእንደዚህ ያለው ጊዜ ፣ "ምን መሆንሁ ነው አንቱ ሰውዬ? ባገር ነውዬ ባንቱ ብቻ አልመጣ!" ይላሉ ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ። "ጃሬ ተው ተመስገን በሉት! የሌሎቹን ማየትና መስማት ነውዬ! እስተዛሬ በዚህ አልኖርን? አንቱ እጅ—እግርሁን ክርክም ካረኩ ፣ ያለው ጥሪት ሳገር አይበቃም ወይ? ያ ሁሉ እውር አህያ የሚያስጦር ርስት እያለ ይህን ያክል ማሰብና መጠበብሁ ለማን ብለሁ ነው?" በማለት ይመክሯቸዋል ። አይመልሱላቸውም ።



የአዲስ አበባ ዋና ዋና ጐዳናዎች ማንንም በማይፈሩና የተለያየ የሰሌዳ ላይ ጽሑፍ በያዙ ሠልፈኞች መጥለቅለቁን ቀጠለ ። እንዳጋጣሚ እየሆነም ቀኛዝማች ወጣ ሲሉ ያጋጥማቸዋል ። በአቅራቢያቸው የነበረው ንክም እንዲያሳብዳቸው የታዘዘ ይመስል ፣ "ፍትሕ ተጓድሏል ! ነጻነት ካገር ጠፍቷል ! ድሃ ተበድሏል ፣ የሕዝቡ መብት ተገፏል !" እያለ ሠርክ ይጮሃል ። በየጐዳናው ላይ የሚሠለፉትም ያንኑ ያስተጋባሉ ።

ያንን ያገናዝቡና ፣ "ግድየላችሁም ፣ ሕዝቡ ቀስ በቀስ ማበዱ ነው" ይላሉ ለራሳቸው ። እሳቸው ራሳቸው እጃቸውን እያወናጨፉ ብቻቸውን ሲያወሩ ፣ የቆየ ንክ ይመስላሉ ። ከቀን ወደ ቀን የማዕረግ ስማቸውን ጠሉት ። "የተከበሩ ቀኛዝማች" ሲሏቸው ፣ ሲሰርቅ እንደ ተያዘ ሰው ክፉኛ ይደነግጣሉ ።

ከሜር አምባ እስከ አዲስ አበባ የሚያውቋቸውን ሰዎች ሲያስላስሉ ምንዳዬ ዝክር ይላቸውና ፣ "አዬ ቀርቶ! እሱስ ማን ሆነና? አሁንማ ወግ—ወጉ ተይዞ ፣ እሱም አብሮ በል በለው ሲል ነው እሚውለው አሉ! አጅሬ ይቺን ታህል አግኝቶ ነው? ከንግዲህማ ምኑ ይታመናል? መተማመን ቀረ! ዛሬማ ያንን ደግ ፈረንጅ ፣ እንደ ውጋት እሚያጣድፈው እሱው ነው አሉ — ወይ መቆየት! ወይ ጊዜ!" ይላሉ እየተጨነቁ ።

ከአቶ ወርቅነህ ጋር ሲገናኙም ፣ በወ/ሮ ደጅይጥኑ ምክንያት የነበራቸውን ቅሬታ ገሸሽ ያደርጉና ፣ "እህ? እንዴት ነው ነገሩ? ዘንድሮ ምስቅልቅሉ ወጣ አይደል? እዝማሚያው ወዴት ይመስለዎታል?" ይሏቸዋል ። ፋይዳ ያለው መልስ አያገኙም ። በየራሳቸው ልቦና የፈጠሩትንና የሰሙትን እያስመሰሉ ያወራሉ ። በውሸቱም ፣ በቅጥፈቱም ይጠጋገናሉ ። ዞሮ—ዞሮ ግን ፣ በሰም ያጣበቁት ጥርስ ይሆንባቸዋል ። ከወደ ገጠር የሚሰማውም ወሬ አላማራቸውም ።

* * *

ምንዳዬ ፣ ሌት—ተቀን ይባዝናል ። ገና ለማንም አልነጋ ። በድንግዝግዙ ውስጥ ሁኔታዎች መለዋወጥ ቀጠሉ ። የሠራተኞች አቤቱታ በሁለትና በሦስት እግር ይወሰናል ። የማስማሚያ ክፍል በር ተከፍቶ ፣ የባለሥልጣን ፊት ፈክቶ ይጠብቃል ። ባለንብረቶቹም እንደ ተጠሩ ከተፍ ፣ ሳይጠየቁ መለፍለፍ ሆነ ። እንዲያውም አብዛኞዎቹ ፣ "ይኸኮ ቀላል ጉዳይ ነው ። እዚህ ድረስ መምጣትም አልነበረባችሁ ። ቀደምብላችሁ አትነግሩንም ነበር" ማለት ጀመሩ ። እርቅ ጠያቂና ስምምነት

ፈላጊው በዛ ። እያሌ ወራት የተጓተቱ የጋራ ስምምነቶች ወር በማይ ሞላ ጊዜ ተጠናቀው ተፈረሙ ። ሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ የቃጣው ሳይመታና ዛቻው ፈር ሳይዝ ፡ እያሌ ነገሮች ምስቅልቅላቸው ወጣ ። የነካርሎ የጠራራ ዱለታ ፡ ወደ ውድቅት ሲለወጥ ፡ ሠራተኞቹ ጋራዡ ግቢ እየተሰበሰቡ መወያየት ጀመሩ ። የሸሹ ጠጋ—ጠጋ ፡ የተዳከሙ ጠንከርከር አሉ ። ያችፍቻፊዎች ምላስ እየጠወለገ ወሬ እያቀበሉ ማራ ኮት ዋጋ አጣ ።

እናም ፡ ጊዜው እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰ — — ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደረደሩ — — የተነሣው ሞገድ እያፈረጠና እያላጋ ፡ ይብስ ማጥለቅለቁን ቀጠለ ። የይሁዳው አንበሳ ግርማ ሞገስ ተገፎ ፡ ሰለሞናዊው ዘውድ ሲንኮታኮት ፡ ቀኛዝማች በሽብር ተንገርግበው አናቱን እንደ ተመታ ዘንዶ ተወራጩ ።

ወራቱ ሲጨምርም ሥጋትና ብስጭታቸው በዛ ። ወርኃ—የካቲት ላይ የተሰነዘረው ግዙፍ ሰይፍ ፡ ቀኛዝማችን አወራርዶ ፡ የጭሰኞቻቸውን የድግር—እላቂ አሳከላቸው ። ሕሊናቸው እየሟሸሸ ፡ ነፍሳቸው ተንገላታች ። ከገጠር ጋር የተያያዙበት ወፍራም የጥቅም ደም ሥራቸው ድንገት ተጎመደ ። የጉማጁን እርባና ቢስ ጫፍ ከሩቁ ጨብጠው ቀሩ ።

ቀኛዝማች አውርተው ከማያባሩ ፡ ለፍልፈው ከማይሰለቹ ሰዎች ጋር ቤት ዘግቶ መዶለቱን አዘወተሩ ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፡ "ዘንድሮ እኚህ ሰውዬ እንጃላቸው ፡ ያዳሜን ወሽካታ እየሰበሰቡ ጉድ ሳያመጡብኝም አይቀሩ ፡ ከዚህ ሁሉ ያንኑ ሚኻኤላቸውን ቢለማምኑ ይሻላቸው ነበር" ይላሉ ጓዳ ለጓዳ ።

ቀኛዝማች ግን ፡ ካንዳንድ የመኝታ ቤትና የሳሎን ውይይት በኋላ ፡ ልባቸው ተስፋ ቢጤ ሲያጎነቁል ፡ "ኧረዲያ ! ምንም ቢሆን ከዘንድሮ ጎፈሬ ያንበሳ ጮላጣ ይሻላል" ይሉና ፡ ቤት ለቤት ሲንጎራደዱ ልበ—ሙሉነት ይሰማቸዋል ። በእንደዚያ ያለው ወቅት በመቶና በሺህ የሚቆጠር ጀሌ አስከትለው ፡ ጠላትና ምቀኛዬ ነው የሚሉትን ሁሉ ረፍርፈው እንደ ልባቸው ሲጎማለሉ ይታያቸዋል ።

የወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ሐሳብ ከቅናት ወደ ሥጋት ፡ "ከራሳቸው ጉዳይ ወደ ምነው ጠፉና" ፡ በመጨረሻም "እኚህ ሰውዬ አንድ ነገር ሆነው ብኝ ይሆን እምላኬ? የሣር አምባው አባቴ አትርሳኝ ፡ አታጋልጠኝ" ወደ ማለት አጋደለ ።

የሰውዬው ተለዋዋጭ ጠባይ ካንድ ውሳኔ ወደ ሌላ ውሳኔ እየተሸጋገረ ፡ አንዱ ሐሳብ በሌላ ሐሳብ እየተሻረ ቁም ስቅላቸውን አዩ ።



የኋላ ኋላ ግን ፡ ከሚመክሩት ጋር መክረውና ያዛልቃል የሚሉትን ብልሃት መርጠው ወሰኑ ። ጊዜም አሳባከኑ ። ሚስትና ልጆቻቸውን ይዘው ፡ መኪናና ቤት ንብረታቸውን ከሣር አምባ ላመጧቸው የቤት ሠራተኞችና ዘበኞች ፡ "በርትታችሁ ጠብቁ ፡ አገር—ቤት ደርሼ እመለሳለሁ" ብለው ፡ በእውቶቡስ አጣዬ ከተማ ሲገቡ ቀለል ቢላቸውም ልባቸው አላረፈም ። ስለ አካባቢው ሁኔታ ወሬ እያጠያየቁ ሁለት ቀን ዘመድ ቤት ውለው አደሩ ። ደስ ስላላላቸውም አሞታቸው ፈሰሰ ።

ሐምሌ 18 ቀን አመሻሽ ላይ ካራቆሬ እህታቸው ቤት ሲገቡ ፡ ሁሉም ነገር ቀዝቅዞና ተዳክሞ ፡ አገር ምድሩ ግርማ—ሞገሱ ተገፎ የተከዘ ስለ መሰላቸው ፡ ራሳቸውን በአዘኔታ ነቀነቁ ። የተደረገላቸው የመስተንግዶ መጠን ግን አልቀነሰም ። ይሻል ይሆናል ብለው የገመቱት አካባቢ ይብስ ፍሞ ስለ ቆያቸው ጋደም ብለው ሁኔታውን ሁሉ አሰላሰሉት ። ከማያዳፍኑት እሳትና ከማይጋፈጡት ሞገድ ፊት—ለፊት ቆመው ፡ አሻግረው ተስፋ ይዘራሉ ።

ሳይበላቸው እንዳከኩና ሳይቆረቁራቸው እንደ ተገላበጡ ነጋ ። ጧት ወደ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሲሔዱም ከአማቻቸው በቀር ሌላ ሰው አልተከተላቸውም ። ከገረገራ ውጪ ቆመው በመጸለይ ላይ እንዳሉ ፡ አንድ ድምፅ አወካቸው ። ከአብሮ አደጋቸው ዜማ ይልቅ ፡ አየሩን ሰንጥቆ የሚሰማው የሬዲዮ ድምፅ ቀልባቸውን ሰለበው ። ድምፁ ወደ ሚሰማበት ቤት ለመሔድ ልባቸው ቆመ ። አማቻቸውን አስቀድመው እየተፍገመገሙ ቁልቁል ሲወርዱ ፡ ጉልበታቸው ራደ ።

አማችዬው ፡ "እንዴት አደራችሁ እየሀ ቤቶች?" ብለው ገቡ ። ቀኛዝማች እውጪ ቆመው አሰፈሰፉ ። ወዲያው እግሩ የተጣመመ አግዳሚ ተጠርጎላቸው ገብተው ተቀመጡ ። በማርሽ እየታጀበ የሚሰገመገመውን ሙዚቃ ፡ ወደፊት ለመጥ ፡ ወደኋላ ለጠጥ ፡ ፊታቸውን ቋጠር ፡ ፈታ ፡ ቅጭም እያደረጉ በንቃት አዳመጡ ። የቤት ኪራይ ጥገታቸው ነጡፈች ። እንኳን ሰዉን ፡ የሚረግጡትን መሬት ፈሩት ። እህታቸው ቤት እንደ ደረሱም ማንንም ሳያናግሩ ፡ ሕመሙ እንዳገረሸበት ሰው ጥቅልል ብለው ተኙ ። ደፍሮ ያናገረ አልነበረም ። ቃል ሳይተነፍሱና እህል ውሃ ሳይቀምሱ ውለው አደሩ ።

ገባ ወጣ የሚለውን የጐረቤት ሰው ሁሉ ስለ ጠሉት ፡ ቤተሰባቸውን ይዘው ወደ ማጀቴ ሔዱ ። የሚያውቋቸው ሁሉ በአክብሮት ተቀበሏቸው ። ከዘመድ ቤት በተገኙ በቅሎዎች ሣር አምባ ሲገቡ ፡ መምጣታቸውን ያየና የሰማ ፡ "እንኳን ደህና መጡ" እያለ እጅ ነሣ ። መስተንግዶውም አልተጓደለ ። ደስ አላቸው ። አንዳንዶቹ ግን ፡ "ደሞ ተንግዲህ ወዲያ ለሱ ማ ጉብ—ቂጥ ይላል" እያሉ ቀሩ ።

ቀኛዝማች ዋል—አደር እንዳሉ ፣ የቀድሞዋ ሣር አምባ ፣ ያዘዙና የነዱባት ፣ የቀጡና የገረፉባት ፣ ያማሩና የተከበሩባት ፣ የተፈሩና ዓለማቸውን ያዩባት ሣር አምባ ቀረቀረቻቸው ። ይኸነዬ "ምናባቱ !" ብለው መላ መቱ ! እንደልብ በፏለሉበት አገር እንደ ሽለመጥማጥ እየተሹለከለኩ ደባ መተብተብ ያዙ ። ወኔ ለመቋጠርና ከጉልበታቸው በታች የወረደውን ሱሪያቸውን ከፍ ለማድረግ ፣ ሥር—ሥሩን መቅበዝበዝና ቢጤዎቻቸውን ማነፍነፍ ጀመሩ ። አጃቢ ጀሌአቸውን መልምለው እንዳበቁ ፣ አቅጣጫቸውን አምታተውና ዓላማቸውን ሰውረው ከሣር አምባ ወጡ ።

* * *

በዋናው የሠራተኞች ማኅበር ጽ/ቤት በኩል የለውጡን ተፃራሪዎች የሚፋለሙ ሠራተኞች ከየድርጅቱ ሲመረጡ ፣ ምንዳዬ ቦጋለና አማረ ንጋቱ በፈቃደኝነት ተመዝግበው ማሰልጠኛ ገቡ ። ከልዩ ልዩ ፋብሪካዎች የሔዱ ሠራተኞች ለ፫ ወራት ያህል ወታደራዊ ልምምድ ተሰጣቸው ። ሁለቱ ሠራተኞች በሾፌርነትና በሜካኒክነት አያሌ አውራጃና ወረዳዎችን እንዳዳረሱ ፣ ሰሜን ሸዋ ውስጥ የሚካሔደው ፍጥጫና ቁርቁስ በመካረሩ ፣ ወደዚያው አመሩ ። የነምንዳዬ ክፍል ከፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ አባላት ጋር መንዝና ግሼን ፣ ይፋትና ጥሙጋን እያሰሰና እየተዋጋ ዋናው ምሽግ ከነበረበት አካባቢ ደረሰ ።

ከአካባቢው ወረዳዎች የዘመቱ አያሌ ገበሬዎች ፣ ሠራተኞችና የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ አባላት ፣ የማጥቂያና የመከላከያ ወረዳቸውን ይዘው ፣ ለትንቅንቅ ሲዘጋጁ ፣ ልዩ ልዩ የነፍስ ወከፍና የቡድን ጦር መሣሪያ የያዙ የለውጡ ተፃራሪዎችም ጀሌዎቻቸውን አስቀድመው እያስመሸጉ አመቺ የውጊያ ቀጣናቸውን ይዘዋል ። የጉዳትን መጠን ለመቀነስ ሲባል ፣ አለአግባብ ቸኩሎ የማጥቃቱ ሁኔታ ዘግይቶ ፣ በቅድሚያ የጠላትን አቅም በሽምቅና በስለላ ስልት ማዳከም አስፈላጊ መሆኑ ስለ ታመነበት ፣ እስከዚያው የነምንዳዬ ጦር ቦታ መርጦ ሠፈረ ።

* * *

እሳቱ ባቄላ ምድር ላይ ቦግ ብሎ ነደደ ። ተራራና ገመገሙ ፣ ሸለቆና ስርጓጉጡ ፣ በተኩስ ድምፅ ተናጋ ። ጥይት እንደ በረዶ እየፈላ ቀኑ ረፍዶ ጠረረ ። ውጊያው ተጧጧፈ ። ከቀኑ ሰባት ሰዓት አካባቢ የሕዝቡ ጦር አይሎ ከፍታ መሬቶችንና ምሽጎችን ቢያስለቅቅም ፣ የለውጡ ተፃራሪዎች ጦር መሬት ልሶና ድንጋይ ነክሶ እስከ መጨረሻው



ተዋደቀ ። ፀሐይ ስታዘቀዝቅ ግን ፣ ተንዶ ተፈረካከሰ ። ወዲያው በጉርሻ የተገዛ ሎሌ ፣ በስብከት የተነዳ ጀሌ ፣ በሥጋ ዝምድና የተደለለ አሽከር ፣ ሀብት ያተበተው ባለርስትና ምኞት የቀተተው ከበርቴ ፣ በየቋጥኙ ሥር ሲረፈረፍ ፣ ቀሪው እጁን እየሰጠና እየተማረከ ገባ ።

ፀሐይ እንደ ጠለቀች ፣ ምርኮኞቹ በሙሉ ለጥበቃ ቅርብና ምቹ በሆነ ቦታ ላይ እንዲሰበሰቡ ተደረገ ። በየገደላ—ገደሉ ሲወድቁና ሲነሡ ፣ ሲዘሉና ሲንከባለሉ የዋሉት ምንዳዬና አማረ ፣ ራታቸውን በልተው ጋደም አሉ ።

ድል አድራጊዎቹ እየሸለሉ ሲያቅራሩ ፣ ተሸናፊዎቹ አንገታቸውን ሰብረው ሲተክዙ አጥቢያ ኮከብ ታየች ።

"ምነው አንተ አለመሸለልህ ምንዳ?" አለው አማረ ጐመኔ ብርድ ልብሱን ደርቦ ሜዳው ላይ በጀርባው እንደተኛ ።

"ምን እባክህ ፣ የከተማ ሰው ሆኜ ሰውነቴ ባልጎ ፣ እንደ ዱሮውማ ቢሆን አባቱ ነበርኩ— —"

"እኔስ ትንሽ ታስማኛለህ ብዬ ነበር ለጉራ እንዲመቸኝ" አለ እየሣቀ ።

"ከእንግዲህ ወዲያ ውጊያ የለም ብለህ ነው — — ያነዬ እፎክራለሁ!"

"ላንተ ቀረብህ እንጂ ፣ እኔማ እስኪበቃኝ ሰምቻለሁ ።"

"እሱስ ለኔም ለራሴ ቢሆን ጥሩ ነበር ፣ ወገን ያበረታል ፣ ወኔ መቀስቀሱስ ቢሆን ቀላል መሰለህ ? ቆይ ለወደፊቱ" ብሎ ከት ብሎ ሣቀና ፣ "አማረ ?" አለው ።

"አቤት!"

ንግግሩ በሣቅ እየተቆራረጠ ፣ "አሁን ያንን ካርሎን እዚህ ብታገኘውስ?"

"አይ አንተ! በምን ትዝ አለህ? እሱን ብቻ አልነበር? — — አለ እንጂ! ኧረ ስንቱ!"

"ባትልም ሞልተውልሃል! እንደኔ ደረስ ብለህ ባየኻቸው!" አለ ራሱን እየነቀነቀ ።

አማረና ምንዳዬ ፣ የሁለት ምርኮኞች ስም ለማስመዝገብና የማረኩትን መሣሪያ ለማስረከብ ወደ ማስመዝገቢያው ቦታ ሲጓዙ ፣ ከየት

በኩል መሆኑ የማይታወቅ ድምፅ፡“ምንዳ!” ብሎ ተጣራ አንድ ሰው ። ምንዳዬ ቆም ብሎ ግራ—ቀኙን ቃኘ ።

“እኔ ነኝ ምንዳ!” ሲለው ወዲያው ተያዩ ። የሁለቱም ፊት በደስታ ደመቀ ። አንገት ላንገት ተያይዘው ተሳሳሙ ። ከትርምሱ ውስጥ ወጣ ብለው ገለል ካለ ቦታ ቆሙ ።

“በየት በኩል መጣህ ምንዳ?” አለው አመጣጡ ገርሞት ።

“ይልቅ አንተ እንዴት እንደ መጣህ ንገረኝ? የሚገርመው ያንተ!”

“እኔማ በተራዬ የመሬት ከበርቴ ላሳድድ መጥቼ ነው” አለ ቸርነት ።

“እኔም አመጣጤ ለዚሁ ነው ።”

“መቼ ነው የገባኸው?”

“እዚህ ከደረስን አንድ ሳምንት ሆነን” አለ አማረን እያየ ።

“እኛም ከመጣን ሰነበትን ። ከላይ ያሉት ተኩስ ሲከፍቱ እናንተም ከዚህ ትጀምራላችሁ ብለውን አድፍጠን ነው የሰነበትነው ። ትላንትና ታዲያ ታያስቡትና ወፍ ቲንጫጫ ከልብስ አልንባቸው ። የዛሬ ወር ገደማ መሆኑ ነው መሰል እኛ እማናኸውን ብረት ይዘው ጉድ አፍልተውብን ነበር ። መገን ምንዳ? ጦር ሠራዊት ሆንክ እንዴ?” አለው ትከሻውን ያዝ አድርጎ ።

“አልሆንኩም ፡ በየቦታው የምንገኝ ሠራተኞች ግን አብረን እየዘመትን ነው ።”

“ያ ሁሉ ጡሃ በወንፊት ካልቀዳችሁ ሲል የኖረ የመሬት ከበርቲ ሁሉ መላ—ቅጡ ጠፍቶታል ። ኧረ እንደ ሥራቸው ከሆነስ ገና ቁናቸውን አላገኙም ። እኔማ አሁን ፡ አሁን ታስበው ሁለመናዬ ይንቀጠቀጣል! በየሀ ላይ ስንቱን ደለለው አስፈጁት — — ልኬስ? እነ አሻጋሪስ ደህና ናቸው? አገሩን ለመዱት?”

“ሁሉም ደህና ናቸው! እነ አሻጋሪም ተማሪ ቤት ገብተዋል ። ይህን ጉዳዮችንን ስናጠናቅቅ አብረን ሔደን ታያቸዋለህ ።”

“እንኳን ደህና የሆኑዬ እንሔዳለን እሳቸውስ ደህና ናቸው ወይ?”

“ማ?”

“ቀኛማች?”

“የመቼህን ነው? ከዚያ ከኛ ጋ ተሔዱ እኮ ቆይተዋል ። ቢያ ሰሞን ሔጄ አጥቻቸዋለሁ ። እናንተ ጋ የሉም እንዴ?”



“ተምርህ ነዎይ? እኛጋማ የት አሉ? ሚስትዮዋና ልጆቹ ግን አሉ ። ሰውዬው ሰንበትበት ብለው ነው የሔዱት” አለ ግር እያለው ።

“ታዲያ ወዴት ገቡ ይባላል ?”

“ባትገናኙ ይሆናሊ ፣ እያው እናንተ ጋ ናቸው ።”

“ሚስትዮዋ የሰው ከተማ አንቀው ምን ያረጋሉ እያሉ ተጨንቀዋል ፣ ዛሬማ አለቅጥ አፍ አብዝተዋል ፣ ከገባ ከወጣው ጋ ወሬ ሲያቀማቅሙ ነው እሚውሉት” አለ ዐይኑን ምንዳዬ ላይ ተክሎ ።

ምንዳዬ ዝም ብሎ ቆየና ፣ “ካንተ ሌላ የመጣ የለም እንዴ? እነ ማን አሉ?” አለው ።

“ማ ቀረ ብለህ ነው? እችላለሁ ያለ ሁሉ መጥቷል ። እነማ እነማ ልበልህ? እሸቴ ፣ ናደው ፣ አህመድና ጀማነህ ፣ አብዩ ተፈራ ፣ አፈሣ ፣ ዘነበ ፣ ይሸበሩ — —”

“የቱ አፈሣ?”

“ያው እምታኸው አፈሣ ነዋ!”

“ምን ትቀልዳለህ? አፈሣ እዚህ ድረስ መጥቶ?”

“እንዴታ! ኧረ እሱ ዋና ሞገደኛ ሆኖልሃል!”

“እንዴት?” አለና ከት ብሎ ሣቀ ።

“ዐይኑ—ጥላው ተገፎለት! ዛሬ ያ የዱሮው አፈሣ አይምሰልህ !”

“እንዴት — እንዴት ነው እምትለው?”

“ይኸውልህ እንዲህ ሆኖልሃል! ምድረ ተማሪ ነጋ ጠባ ጠላትህን እወቅ እያለ ቲነዘንዘው እንዴት ይሁን ትላለህ? እስበሳችሁ ተረዳዱ እያሉ በየስብሳቦው ሲያስተምሩን ጊዜ ፣ ምድረ—ጭሮ አዳሪ ፣ ለካ እንዲህ ኖሯል ነገሩ እያለ ፣ እስበሱ ይኳኸንልህ ይዟል” አለ ቸርነት በርጋታ ።

“አሁን አንተና አፈሣ ካንጀት ሆናችሁ ትነጋገራላችሁ ማለት ነው?” አለው ተገርሞ ።

“ምነው ወንድሜ! ዛሬማ ዋና ወዳጅ ሆነንልሃል! ያ የያነዬው አፈሣ እማደል እኮ ነው እምልህ! ያን ያለፈውን አርቲ—ቡርቲ ሁሉ ትተነዋል ። አብሶማ ይኸን ሰሞን አልተለያየንም ። ትላንትም በርታ ኅበዝ ስንባባል ነው የዋልነው ።”

"በኔ የተነሣ አይወድህም ነበር እኮ! ማን አስታረቃችሁ?"

"ማ ያስታርቀናል! እኛው እስበሳችን እያደር ነገሩ ሲገባን ፣ ተነጋገርን ።"

"እስቲ ሙት በለኝ?"

"ፍቅርህን!"

"አሁን ምንዳዬን እዚህ አገኘሁት ብትለው ምን ይላል?"

"ምን ይላል ብለህ ነው? ሰው በዋለበት ውሃ በፈሰሰበት አደል?"

"ወየ ጉድ! እንዴት እሚገርም ነገር ነው! በላ! በል ሒድ ንገረውና ከኔም ጋ አገናኘን ። ድሮውንም ቢሆን ሁላችንም ከውቀት እጦት ነው ። አሁንማ ጉዳዩ እየገባን ነው ።"

"ኸረ እሱ እሚለውን በሰማህ! አለማወቅ እያለ ፣ ሁለዜ እንደ ተንገበገበ ነው ። ከወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ጋ እማ ዐይንና ናጫ ሆነዋል! በወሬ ወሬ ያንተን ነገር ቲያነሡበት ፣ ምነው አሁን ባገኘሁትና እግሩ ላይ ወድቄ በታረእን ሲል በሰማኸው !"

"ታዲያ አብረን ሔደን እናነጋግረው እንዴ? ወይ አንተ ሔደህ ትነግረውና . . ."

—"ለማንቻውም እኔ ሔጄ ልንገረው ፣ እየሁ ቆዩኝ — —" ብሎ ሊሔድ ሲል ፣

"እኔ እንደሁ በጣም ነው ደስ ያለኝ ፣ አሁንማ ያንዳችንን ደም አንዳችን እያፈሰ እንዴት ጠላት እንሆናለን?" እንዳለ ቸርነት ሔደ ።

ልዩ ልዩ ሰዎች ምርኮኛና መሣሪያ በግንባር እያስጠሩና እያቀረቡ አስመዝግበው ሲመለሱ በነአማረ አጠገብ ያልፋሉ ።

ቸርነት ፣ አፈሣንና ሌሎች ሁለት ሰዎችን አስከትሎ ሲመለስ ፣ ምንዳዬ ገና ከሩቁ ፈገግ ብሎ ጠበቃቸው ። የሁሉም ከንፈር ተላቀ ፣ የሁሉም ፊት ፈገገ ። ምንዳዬ ያነገተውን መሣሪያ ለአማረ ሰጥቶ ሁለት እጁን ሲዘረጋ ፣ ቸርነትም የአፈሣን ጠበንጃ ተቀበለው ። እያሌ ዓመታት እንደ ተለያዩ ባልንጀሮች ተቃቅፈው ተሳሳሙ ። ከከፍተኛ የጥላቻ አዘቅት ወጥተው ፣ ፈጽሞ ይሆናል ብለው ባልጠበቁት ጊዜ በቀላሉ ሲገናኙ ፣ ሁሉንም ደነቃቸው ። ከግማሽ ሰዓት በላይ ሲያወሩ የቀድሞወን ባይረሱም ፣ አላወሱም ።



ሁሉም ባንድነት የማረኩትን መሣሪያ ለማስረከብ ፣ ወደ ማስመዝገቢያው ቦታ አመሩ ። ሠራተኞቹ አንዳንድ ፣ ገበሬዎቹ ሁለት— ሁለት ምርኮኞች አስጠርተው አስመዘገቡ ። ባካባቢው ቆመው አላፊ አግዳሚውን ሲመለከቱ ፣ የተመዘገቡ ምርኮኞች ባጠገባቸው እያለፉ በዚያው ይመለሳሉ ። አንድ መሣሪያ ያነገተ ደልዳላ ጐልማሳ ፣ ምርኮኛውን ለማስመዝገብ ጮክ ብሎ ተጣራ ። ደስ እንዳለው ከቁንጥና ጤውና ከገጽታው ያስታውቃል ።

እነ ምንዳዬ ፣ የቅርብ ወዳጁን መርዶ እንደ ሰማ ሰው ክው ብለው ደንግጠው እርስ በርስ ተያዩ ። አንድ ረዘም ያሉ ገብስማ ጸጉራቸው የተንጨበረረ አዛውንት ፣ ወፈር ያለ አካላቸውን እያርገደገዱ አቀርቅረው ባጠገባቸው ዐለፉ ። ካኪ ሱሪያቸው ከወደ ግርጌው ተተርትሮ ፣ ኮትና ሸሚዛቸው ትከሻና ጀርባቸው ላይ ተዘንጥሎ ገላቸው ይታያል ። ዐፈር መስለዋል ። ከምንዳዬ ይልቅ እነ ቸርነት ዐይናቸውን ትክል አድርገው አዩ ። ምኑን ከምን ይጠራጠሩት ። እሳቱን ውሃ ፣ ተራራውን ሜዳ አይሉት ። ያዩትም ፣ የሰሙትም እውነት ነው! አይቶ ካረጋገጠ ዐይን የበለጠ ማን ይታመን! ሁሉም ወደፊት ተጠጉ ። ሰውዬው ድንገት ቀና ብለው ዙሪያውን ሲመለከቱ ዐይናቸው እነ ቸርነት ላይ በማረፉ ከመቅፅበት ደንግጠው አቀረቀሩ ። መንፈሳቸው ተሸብሮ አካላቸው ራደ ። እንደገና ቀና ብለው ሲመለከቱ ከምንዳዬ ጋር ተያዩ ። ሕልማዊ ትዕይንት መሰላቸው ።

ትኩር ብለው ሲያዩት ፣ "የኔ ነገር በቃው ፣ ተሸንፌአለሁ ፣ ምርኮኛህ ነኝ" የሚሉት መሰለው ። ሹክክ ብለው ባቅራቢያው ሲያልፉ ፣ ትኩር ብሎ አያቸው ። እምብዛም ሳይርቁ ከምርኮኞቹ ጋር ተቀላቅለው በስተዳር ተቀመጡ ። የእምነታቸው አቅጣጫና ባሕሪ ቢለያይም ፣ የአወዳደቃቸው ፍጻሜ አሳዘነው ። ሰው ፣ ኑሮ ፣ ከፍና ዝቅ ማለት ይኸው ነው?" አለ ለራሱ ።

እነ አማረን ቆዩኝ ብሎ ሻንጣውን ወዳስቀመጠበት ሔደ ። ከሸራ ሻንጣው አንድ ኮት አውጥቶ ወደ ምርኮኞቹ አካባቢ ተመለሰና ፣

"አንድ ምርኮኛ ለማነጋገር ፈልጌ ነበር?" አለው መዝጋቢውን ።

"ለምን? ምን ልትለው ?"

"የምላቸውንማ እኔ ዐውቀዋለሁ ።"

"ምን ታነጋግረዋለህ! አዩ ! 'እርጎ መስሎሽ እርሾ ጥልቅ' እንዳይሆን! ይልቅ አትሞኝ ፣ ጠላትህን ጐርፍ ሲወስደው ምራቅህን አክልበት ይባላል ። ሲገልህ የመጣን ጠላት አትዘንለት" ብሎ ምንዳዬን በንቀት አየው ።

“እኔ ይኸን መች አጣሁት ! ያሸነፈውን የሚገል ዐውሬ ነው ! ስለ በቀሉ ግድ የለህም ! አዮ ሌላ ፣ ወዮ ሌላ !”

“ከፎከረ የጠረጠረ ብዬ ነዋ! ይኸነዬ አንተ ተማርከህ ቢሆን ፣ እግር—ተወርች ታስረህ ነበር!”

“እዬዬዬ ! ‘ለቀባሪው አረዱት’ አሉ ! ያነዬ መጥተህ ታየኛለህ !” ብሎ ያለ ፈቃድ ጥሎት ወደ ምርኮኞቹ ሲሔድ ፣ እነ ቻርነትም ተከተሉት ።

“ቀኛማች በላይነህ !” አለ ከፊት ለፊታቸው ቆሞ ።

“አቤት!” ብለው ቀና ሲሉ ፣ የያዘውን ኮት አለበሳቸው ። ትኩር ብለው አዩትና ዐይናቸው እንባ አቀረረ ።